# ሐመር

## ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ


✤ እኩሱምና ታቦተ ጽዮን
✤ እርቅ በማኅፀን ተጀመረ
✤ ምሥጢረ ጥምቀት
✤ ቤተ ክርስቲያን
✤ ስደተኞች
✤ ሃያ ሰባት ዓመታት–በሰንበት ት/ቤት አገልግሎት
✤ ዲማ ጊዮርጊስ – ትናንት እና ዛሬ
✤ ቅድስት እንባ መሪና
✤ የጅግላሌው ፈረስ (የመጨረሻ ክፍል)
✤ መንፈሳውያን በዓለማውያን መካከል
✤ ደስታና ዘፈን
✤ ቅዱሳት መጻሕፍት በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን





የአኩስም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን

የዲማ ታቦት ከዋሻ ሲወጣ →



የዲማ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን




©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## ከአንባብያን

## ለአንባብያን

ለሐመር መጽሔት አዘጋጆች እንደምን አላችሁልኝ። እስቲ ይህችን ከመጽሐፈ ጨዋታ ቀንጭቤ የላክሁላችሁን መልእክት ተቀበሉኝ።

- እግዚአብሔር ጌታ ነው – አዳኝም ገዳይም ነውና
- እግዚአብሔር ቅርብ ነው – ስንጠራው በቶሎ ይመጣልና
- እግዚአብሔር ንጉሥ ነው – በቶሎ ይፈርዳልና
- እግዚአብሔር መሐሪ ነው – ይቅር ይላልና
- እግዚአብሔር መድኃኒት ነው – ነፍስንም ሥጋንም ይፈውሳልና
- እግዚአብሔር ባለፀጋ ነው – ሁሉንም ይመግባልና
- እግዚአብሔር ረቂቅ ነው – አይጨበጥምና
- እግዚአብሔር ምሉዕ ነው – በሁሉም ቦታ ይገኛልና
- እግዚአብሔር ብርሃን ነው – በእርሱ ዘንድ ጨለማ የለምና
- እግዚአብሔር ኃይል ነው – ማንም አይቋቋመውምና
- እግዚአብሔር ፋሲካ ነው – ለሁሉ ታርዶአልና
- እግዚአብሔር ጨው ነው – ኑሮአችንን አጣፍጦታልና!

ኢየሩሳሌም ይገዙ
ከፍ.12 ቀበሌ 18 አዲስ አበባ

ለሐመር መጽሔት ደንበኞች በሙሉ
ማኅበራችን የሕትመት ውጤቶቹን
ለማከፋፈል ይችል ዘንድ
አዲስ ማከፋፈያ ሱቅ ከፍቷል።

ቦታ–ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት ካለው ሸዋ ዳቦ ቤት በስተቀኝ።

የማኅበሩ ጽ/ቤት

### አደራ እልሻለሁ

በዚያ በበረሃ ምንም በሌለበት
ተሰደሽ የኖርሽው ሳይኖርብሽ ኃጢአት
የሰው ልጆች ቤዛ የመለኮት እናት
ቅድስት እናታችን የዋኋ እመቤት
አደራ እልሻለሁ ከጐኔ አትራቂ
ወዳጅ ዘመድ የለኝ ያላንቺ ጠባቂ
አድኝኝ እናቴ ከሥጋ ፈተና
እኔማ ያላንቺ አልችልም ልፀና
ቅድስት ሆይ አትራቂኝ አንቺ የዓለም እናት
በዝቷል መከራዩ አድኚኝ ከጥፋት
ሸክሜ የከበደኝ እንግልት ሆኛለሁ
ከኔ እንዳትለይ አደራ እልሻለሁ።

ደረጀ ተሾመ – አ.አ

### ኑ ወደ ሕይወት ምንጭ

በዓለም ስመላለስ በጨለማው ሃገር
መግቢያ መውጫው ጠፍቶኝ ሲያንገላታኝ ሐሩር፤
ፍፁም ግራ ገብቶኝ ተጨንቄ ሳለሁ
ሰይጣን ብዙ ሲጥር ወጥመዱ ሊያገባኝ
ዓለም ተብለጭልጫ ስታጭበረብረኝ
ለዘለዓለም ብላ የሰጠችኝ ደስታ
ጠዋት ብልጭ ብሎ እልም ሲል ማታ
በማይታይ ማዕበል ሕይወቴ ሲመታ
በፍቅር አየኝና አዘነልኝ ጌታ
ሸክሜን አራግፎ እንዳልንገላታ
አደለኝ የማያልቅ የዘላለም ደስታ
በቤቱ አስቀመጠኝ በቅዱሳን ቦታ
ካላችሁ እንደኔ የተንገላታችሁ
ኑ ወደ ሕይወት ምንጭ ዕረፍት አለላችሁ።

(አንዱ ዓለም አድኑ – ከናዝሬት)



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ሐመር

ሁለተኛ ዓመት ቁጥር 4

ጥር 1987 ዓ.ም


## ይዘት


ከአዘጋጁ . . . . . . . . . 1

የማኅበሩ መልእክት . . . . 2

ደብዳቤዎች . . . . . . . 3

ከሰሞኑ በረከት

✣ አኩሱምና ታቦተ ጽዮን . . . . 4

✣ እርቅ በማኅፀን ተጀመረ . . . . 6

ትምህርተ ሃይማኖት

✣ ምሥጢረ ጥምቀት . . . . . . . 8

✣ ቤተ ክርስቲያን . . . . . . . . . 11

የሚጎድለን ምንድነው? . . 15

ኪነ ጥበብ

✣ ስደተኞች . . . . . . . . . . . . . 18

ዓምደ ወራዙት

✣ ሃያ ሰባት ዓመታት–በሰንበት ት/ቤት አገልግሎት . . . . . . 20

እናስተዋውቃችሁ

✣ ዲማ ጊዮርጊስ – ትናንት እና ዛሬ. . . 23

✣ ቅድስት እንባ መሪና . . . . . . 25

ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ

✣ የጅግላሌው ፈረስ (የመጨረሻ ክፍል) . . . . . . . . . . . . . 26

✣ መንፈሳውያን በዓለማውያን መካከል . . . . . . . . . . . . . 32

✣ ደስታና ዘፈን . . . . . . . . . . 27

የጥያቄዎቻችሁ መልስ . . . . . 28

ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ

✣ ቅዱሳት መጻሕፍት በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን . . . . . . . . . . 30



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማስተባበሪያ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የመዝሙርና ሥነ ጽሑፍ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ።


# ከአዘጋጁ

*በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን*

*"የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሳጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል" ፪ጢሞ. ፫ ÷ ፲፮:፲፯።*

*ቅዱሳት መጻሕፍት በኃጢአት የደነደነ ልቡናን ሰብረው ቀናውን የድኅነት መንገድ የሚያሲዙ የዘላለማዊ ሕይወት መምህራን ናቸው።*

*ሐመር ቀደምት አበው ብራና ድጠው ፣ ብዕር ቀርጸው ፣ ቀለም በጥብጠው ከጻፉአቸው ጉልቆ መሳፍርት ከሌላቸው ቅዱሳት መጻሕፍት እያውጣጣች ለትውልዱ በሚገባው ቋንቋ የቤተ ክርስቲያኑን እምነትና ሥርዓት ለማስተማር በዚህ እትምዋ የተለያዩ ትምህርቶችን አሰናድታለች። በትምህርተ ሃይማኖት ዓምድዋ ስር ካለፈው የቀጠለው ምሥጢረ ጥምቀት ፣ በኪነ ጥበብ አምድዋ ስደተኞች የሚል አዲስ ተከታታይ መንፈሳዊ ልብወለድ ፣ በእናስተዋውቃችሁ ዓምድ ስር ደግሞ ከታሪካዊ ቦታዎች የብዙ ሊቃውንት መፍለቂያ የሆነው ስመ ጥሩውን ዲማ ጊዮርጊስንና ሌሎች ትምህርት ሰጪ መጣጥፎችን ይዛ ቀርባለች። ሰላመ እግዚአብሔር ከሁላችን ጋር ይሁን። አሜን!*

*ለሥጋም ለነፍስም በረከት የሚያስጠውን ግብዣዎን እነሆ።*


ዋና አዘጋጅ – ብርሃኑ ጎበና ካሣ

ም/ዋና አዘጋጅ – ዲ. ደጀኔ ሺፈራው

✉ 80078

አዲስ አበባ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## የማኅበሩ መልዕክት

# ሁሉም ኃላፊነቱን ቢወጣ

በክርስቶስ ደም የተመሠረተችው ሐዋርያዊት፣ ታሪካዊትና ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያናችን ከመከራና ከፈተና አንዳችም ጊዜ ያረፈችበት ዘመን የለም። ከአይሁድ ሊቃነ ካህናት አንሥቶ በየጊዜው የተነሱ አረማውያን ነገሥታት ያደርሱባት የነበረው መከራ እጅግ አሰቃቂ ቢሆንም ስለተስፋ ቃሉ እስከ ዛሬ ድረስ በጽናት አለች። «ቤተክርስቲያኔን እሠራለሁ የገሃነም ደጆችም አይችሏትም» ማቴ.16፥18። ሊቁ ዮሐንስ አፈወርቅም ይህንኑ አስመልክቶ «ሰይጣን ዝናሩን ከፍቶ ቢጨርስም ቤተክርስቲያንን ግን አልጎዳትም» ብሏል። ለዚህም ከሐዋርያት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ እግዚአብሔር ያስነሳቸው የቅዱሳን አባቶችና እናቶች ተጋድሎ መሠረት ነው።

ይህም በመሆኑ በረጅሙ ታሪኳ ሁሉም ክርስቲያን በሚችለው የየራሱን ኃላፊነት እየተወጣ ድርሻውን አበርክቷል። የሚያስተምረውም በማስተማር የሚጸል የውም በጸሎቱ፣ ምዕመኑም አሥራቱን በኩራቱን እያወጣ ከዚህም ሌላ በችግር በፈተና ጊዜ ሁሉ በካህናት አባቶች ላይ ብቻ ችግሩን በመጣል ቆሞ ሳይመለከት የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ የሕይወቴ ጉዳይ ነው በማለት ታላቅ ተጋድሎውን ሲወጣ ቆይቷል። ለዚህም በአፄ ሱሱንዮስ ዘመነ መንግሥት የተፈፀሙን የእውነተኛ ምዕመናን ሰማዕትነት ማስታወስ በቂ ነው። በእነዚህ ዓይነት ሁኔታ በካህናት አባቶችና በሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ከልብና ከእውነት በመነጨ ኃላፊነትን መወጣትና በምዕመኑም ከፍተኛ ተሳትፎ ቤተክርስ ቲያናችን ዶግማዋን፣ ሥርዓቷንና ትውፊቷን እንደ ጠበቀች ካሏት ንዋያተ ቅድሳትና ታሪካዊ ቅርሶች ጋር ለዚህ ትውልድ ደርሳለች።

ነገር ግን በአሁኑ ሰዓት እንደምንመለከተው በተለያዩ አካባቢዎች በተለይም የጥንታውያን ገዳማትና አድባራት ንዋያተ ቅድሳት ዘረፋ በጣም ተጧጡፎ በመምጣቱ የአንዳንድ አብያተክርስቲያናት የግድግዳ ሥዕሎች በሙሉ ተሰርቀው ባዶ ግድግዳ ብቻ እስከመቅረት ደርሰዋል። እንዲሁም በየጊዜው የሚሰማው የቅዱሳት መጻሕፍትና ሌሎች ንዋያተ ቅድሳት እየተሰረቁ ወደ ባዕዳን አገሮች መላክ እጅግ አሳሳቢ ሆኗል። ይኸውም ቤተ ክርስቲያኒቱን ታሪክ አልባ ለማድረግ እንደሆነ ማንም ሊረዳው ይችላል። ለዚህ ደግሞ ካህናትና የቤተክርስቲያን ኃላፊዎች ብቻ ሳይሆኑ የአካባቢውም ምዕመን በሚገባ ካልጠበቀ ከታሪክ ተጠያቂነት አይድንም።

ቤተክርስቲያን እያንዳንዱ ምእመን በጥምቀት የሥላሴ ልጅነትን እንዲያገኝ ያደረገች እናት እንደመሆኗ ምን እንደሚያስፈልጋትና ምኗ እንደተጐዳ በሚገባ ማወቅ አለብን። በየጊዜውም እየመጡ እናቴ ሆይ ምን ያስፈልግሻል? ከእኔስ ከልጅሽ ምን ይጠበቃል? እያሉ መጠየቅ ያስፈልጋል። አለበለዚያ በስም ብቻ ክርስቲያን ነኝ ብሎ ከዕለታት አንድ ቀን መምጣት ዋጋ የለውም። ዛሬ አብዛኛው ምዕመን ተሳትፎውን በመዘንጋቱ የሰላም ጊዜ ክርስቲያን ነኝ ማለትን ችግር በተፈጠረ ሰዓት ደግሞ ቶሎ ብሎ ካህናት አባቶችን መወንጀሉንና በእነርሱ ላይ መፍረዱን ለምዶታል። ለዚህ ነው በዓመት 12 ብር ብቻ የሚከፈለውን የሰበካ ጉባዔ መዋጮ እንኳን ደስ እያለው አምኖበት የሚከፍል ምዕመን የጠፋው!

በሌላ በኩል አንዳንድ ካህናትና የቤተክርስቲያን ኃላፊዎችም ኃላፊነታቸውን ከመዘንጋታቸው የተነሳ የክህነት አገልግሎት የሚሰጡትና ለቤተ ክርስቲያን የሚሠሩት ለደሞዝ ብቻ እየሆነ የመጣ ይመስላል። በተለይም አንዳንዶች «በጐቼን አሠማሩ! ዮሐ.21፥17 የሚለው የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል በመዘንጋት መኖሪያቸውን ቤተክርስቲያን ልቡናቸውን ከውጪ በማድረጋቸው በአንድ ቤተክርስቲያን ችግር ተፈጠረ ተብሎ ሲነገራቸው ጆሮ ዳባ ልበስ በማለት እየሰሙ እንዳልሰሙ ይሆናሉ። የተቀመጡበትንም ኃላፊ ነት በመወጣት ፈንታ ለክብራቸውና ለግል ጥቅማቸው ብቻ ይሯሯጣሉ። ከዚህም የተነሳ የሌሎች የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች ሃሳብ መፈጸሚያ እስከ መሆን የደረሱም ይገኛሉ። ስለዚህም ነው ብዙውን ጊዜ ቤተክርስቲያኒቱ ውሳኔን እያስተላለፈች ተግባራዊነቱ ላይ ግን ባዶ የሚሆነው።

በአጠቃላይ ቤተክርስቲያኒቷ በላይዋ ላይ የሚደርሰውን ጥቃት ምንጩ ከየት እንደሆነ ማወቅ ይኖርባታል። አለበለዚያ በአንድ በኩል ሲገነባ በሌላ በኩል ማፍረስ ይሆንብናል። ስለዚህ ሁሉም የቤተ ክርስቲያን ልጅ ምዕመናንም ሆኑ መሪዎች ኃላፊነታ ቸውንና ከእነርሱ ምን እንደሚጠበቅ ተገንዝበው በመወያየት በመረዳዳትና በጸሎት በመትጋት ይህችን ከቅዱሳን አባቶቻችን የተረከብነውን ቅድስት ቤተክር ስቲያናችንን እምነትዋን፣ ሥርዓትዋን፣ ትውፊትዋን፣ እንደጠበቀች ለትውልድ ልናደርስ ይገባናል» የአባቶ ቻችን አምላክ ቤተክርስቲያናችንን ይጠብቅልን። የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነትና በረከት አይለየን። አሜን።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ደብዳቤዎች

**በስመአብ፣ ወወልድ፣ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።**

ለሐመር መጽሔት

መድኃኔዓለም በፍቅሩ ጸንታችሁ በዕድሜያችሁ እንድትቆዩ ያድርጋችሁና ፍጹም ኦርቶዶክሳዊ በሆነው መጽሔታችሁ የምታስተላልፉልን መልእክት እኛን በእምነታችን እንድንጸና እያደረገን ስለሆነ በርቱልን። በተረፈ በመጽሔቱ ውስጥ ከባድ የሆኑ የአማርኛ ቃላትንና ከትርጉሙ በስተቀር ብዙ የግዕዝ ቃላትን ባታስገቡ ሥራችሁ የበለጠ ያማረና ብዙ አንባብያንን የሚስብ ይሆናል።

አስፋ ጥላሁን – መንደር 7 (ፓዊ)

ስለአስተያየትዎ በጣም እናመሰግናለን። በተረፈ አንባብያን ከሁለቱም ዓይነት እንደሆኑ እንዳይዘነጉ እንወዳለን። ቀለል ያለ አማርኛ ብቻ ስንጠቀም ምንነካችሁ ለሕፃናት ብቻ ነው እንዴ መጽሔቷን የምታዘጋጁት የሚሉንም እንዳሉ ማለታችን ነው። ስለዚህ ነው አልፎ አልፎ ጠንከር ያሉ ቃላትን የምንጠቀመው።

✣ ✣ ✣

ይድረስ ለተከበራችሁ የሐመር መጽሔት አዘጋጆች

እንኳን ለ1987 ዓ.ም. አደረሳችሁ

ዘመኑ የሰላም፣የፍቅር፣የአገልግሎት፣ የመልካም ፍሬ መሰብሰቢያ ይሁንላችሁ እያልኩ መጽሔታችሁ ለሕትመት ደርሳ ለንባብ ከበቃችበት ቀን አንሥቶ ያለማቋረጥ በአንባቢነት ያልተለየኋችሁ ወንድማችሁ ነኝ። ለዛሬ በዚህች ደብዳቤ ስንተዋወቅ በመሐር ቁጥር ሁለት ሁለተኛ ዓመት ላይ ትውፊት በሚለው ርእስ ሥር የቀረበው ንባባችሁ አርክቶኛል። የእምነታችንን ማንነት ነግሮናል። እግዚአብሔር ይስጣችሁ በየመጽሔቱ እናስተዋውቃችሁ ዓምድ ሥር ስለቅዱሳን አበው የሕይወት ፍሬ ማቅረባችሁ ወደ ፊት እንዳያቋርጥ ምክንያቱም ከእነሱ ሕይወት እኛም እንማርበታለንና ነው። በተረፈ መጽሔታችሁ አይዘግይብን። ፈተናን ሁሉ እግዚአብሔር ያርቅላችሁ። የእመቤታችን ምልጃና ጸሎት ከእናንተ ጋር ይሁን።

ወንድማችሁ ጎርጎርዮስ ሳልስ
(ዘድንባሮ ማርያም)

አሜን። እግዚአብሔር እንኳን አብሮ አደረሰን። የላኩልን የእንኳን አደረሳችሁ የስጦታ ካርድም ደርሶናል። እግዚአብሔር ይስጥልን።

✣ ✣ ✣

**ለሐመር መጽሔት ዝግጅት ክፍል**

እንደምን አላችሁ? እግዚአብሔር ጤናውን ያድላችሁ።

መጽሔታችሁ ብዙ ቁም ነገሮችን አሳውቃናለችና ገፉበት። በተለይ አንዳንድ ታሪካዊ አብያተ ክርስቲያናትን በጽሑፋችሁ ማስጎብኘትና ማሳወቃችሁን በርቱበት።

ገብሩ ተስፋእግዚእ – (ከኤረር ጌታ)

አሜን። ስለአስተያየትም እግዚአብሔር ይስጥልን። በተረፈ እርሶም በአካባቢዎ ወይም በዝና የሚያውቋቸው ጥንታዊና ታሪካዊ አብያተ ክርስቲያን ካሉ ሊጠቁሙን ከቻሉም ጽፈው ከነፎቶግራፋቸው ቢልኩልን ደስ ይለናል።

✣ ✣ ✣

በመጽሔታችሁና በጋዜጣው በካሴቱ ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል በብዛት መነበቡና መደመጡ እግዚአብሔር ይመስገን እሰየው ያሰኛል። ነገር ግን ሐመሮች በማኅበርም ሆነ በግል ተቀርፀው ለሚወጡ መዝሙሮች ተቆጣጣሪ የላቸውምን? ዜማ ግጥምና የመሳሰሉትን የሚቆጣጠር ከሌለ ሁሉም በየግሉ የሚያወጣ ከሆነ ወደ ንግድነትና አላስፈላጊ ወደ ሆነ ፉክክር ከመግባቱም በላይ በቤተክርስቲያናችን ላይ ችግር ሊፈጥር ይችላል የሚል ሥጋት አለኝና የሚመለከተው ክፍል እንደቀላል ባይመለከተው ጥሩ ነው። እናንተም የሚቻላችሁንና የአቅማችሁን ብታደርጉ መልካም ነው። ለሁሉም የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን።

መምህር አብራራው ጫኔ – ከፍቼ

መምህር በአስተያየትዎ በጣም ተደስተናል እኛም እንዳሉን የአቅማችንን እናደርጋለን በዚሁ አጋጣሚም የሚመለከተው ክፍል እንዲያስብበት እንላለን።

✣ ✣ ✣

ውድ የሐመር መጽሔት አዘጋጆች ልዑል እግዚአብሔር ሰላምና ጤናን ያድላችሁ።

መጽሔታችሁ አልፎ አልፎ ትደርሰኛለች። በቬኒስያ አጨራረስ በጣም ነው የተደሰትኩት እናንተንም ከልቤ አመሰግናችኋለሁ ምክንያቱም ጨክናችሁ ትገሏታላችሁ ብዬ ፈርቼ ነበር። እኔም በውስጤ ዘወትር የእርሷ ዓይነት ሃሳብ ስላለኝ አጽናንቶኛል። እኔም ለመወሰን ተቃርቤአለሁ። ከእኔ ጋር ታሪኩን የተከታተለችው ትንሿ እኅቴም ምስጋናዋን አቅርባለች። በዚህ አጋጣሚ የመጀመሪያዬ ናትና አደራ ለቅርጫት እንዳትዳርጓት እያልኩ እሰናበታችኋለሁ።

ከተማሪ መቅደስ ዐወቀ –ሊሙ ገነት

እኅታችን ስለሰጡን አስተያየት እኅትዎንም እርስዎንም ከልብ እናመሰግናለን። ለአሰቡት ነገር እንዲህ ቢያደርጉ መልካም ይመስለናል።

1. በመጀመሪያ ያለመሰልቸት ደጋግመው ይጸልዩበት፣

2. ከዚህ በፊት ለዚህ ክብር የበቁትን አባቶችና እናቶች ረጋ ብለው ያወያዩዋቸው።

3. ስለዚህ ዓይነት ሕይወት የተጻፉትን መጻሕፍት (ለምሳሌ መጽሐፈ መነኮሳት) ያንብቡዋቸው።

4. እዚሁ በዓለም እያሉ የጾሙን፣ የጸሎቱን፣ የምጽዋቱንና፣ የማስቀደሱን ሕይወት ይጀምሩትና ራስዎን ይፈትኑት፣

5. ከዚህ በኋላ የሚሆነውን በፈቃደ እግዚአብሔር ላይ ተመሥርተው እርስዎ መወሰን ይችላሉ።

✣ ✣ ✣

ስማችሁ ከዚህ በታች የተዘረዘረው የመጽሔታችን ተሳታፊዎች ጽሑፎቻችሁ ደርሰውናል። ጥያቄዎቻችሁ ወደፊት በሚመለከታቸው ዓምድ ሥር ይመለሳሉ። ስለአስተያየታችሁም በጣም እናመሰግናለን። በተሳትፎአችሁ አትለዩን።

ወጣት አየለ ተፈራ (አርባምንጭ)፣ ዲያቆን ኢሳይያስ ልሳኑ (አ.አ)፣ አንዱዓለም አድኔ (ናዝሬት)፣ ዮናስ ወልደየስ (አዲስ አበባ)፣ መምህር ይኸነው መለሰ (ጂንካ)፣ ታደሰ ክፍሌ (አዋሳ)፣ አያልነሽ መገራ (አጋርጤና ማቢያ)፣ ኪዳኑ ተካ (ምዕራብ ጎጃም ቡሬ)፣ ብርሃኔ ወ/ገብርኤል (ፓዌ ሠፈራ ጣቢያ)፣ ዳንኤል ካባ (ነጆ)፣ ዲ/ሰብስቤ ማሞ (ሐረር)፣ ብሩክ ታዊት (አዲስ አበባ)፣ ብንያም አለማየሁ (ሞጆ)፣ ፍቃድ መኩንን (የካ ሚካኤል)፣ ብርሃኑ መኩንን (አ.አ)፣ ተማሪ አልዓዛር ሙሉዓለም (ደብረ ማርቆስ)፣ መምህር በላይነህ ደስታ (አጋዴን)፣ አሰፋ እሸቴ (ደቡብ እርሻ ልማት – ፍኖተ ሰላም)፣ መ/ር ጸጋዬ ማርቆስ (ነቀምት)፣ ጌትነት ጋዲሳ (ምሥራቅ ወለጋ ወህኒ ቤት)፣ ዘለዓለም ማሞ (ወለጋ–ጊምቢ)፣ ጌትነት የማርሸት (ባሕር ዳር)፣ ከደብረ ፀሐይ ቁስቋም ማርያም ሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች (አ.አ)፣ ታደለ ገ/መድኅን (መቀሌ)፣ ደረጀ ቢረሳው (ጉጃም–ቲሊሊ)፣ ተማሪ አንድነት አማረ (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ) እማዋይሽ ገ/መስቀል (አሶሳ)፣ ክርስቲያኖች በኅብረት (አ.አ)፣ ከአበባው መሸሻ (ሒርና)፣ ከዓባይነህ ደመረ (ባሌ–መና)፣ ሙሉጌታ ገርማ (አ.አ) ✣



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ከሰሞኑ በረከት

በኢትዮጵያ ታሪክ ልዩ ሥፍራ ከያዙት ቦታዎች ግንባር ቀደምትዋ የአኩስም ከተማ ናት ቢባል ማጋነን አይሆንብንም። የቤተ መንግሥቱም ሆነ የቤተ ክህነቱ ማዕከል በመሆን ለብዙ ዘመናት አገልግላለች። በተለይም ደግሞ እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠው የታቦተ ጽዮን መንበር መሆንዋ ከተማዋን ድንቅ የሆነ ክብር ያጐናጽፋታል።

በዘመነ ሐዲስም የክርስትና መዲና፣ የስብከተ ወንጌል ማዕከል የጳጳሳት መንበር ለመሆን መቻልዋም በቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ውስጥ እንደ አጥቢያ ኮከብ እንድታበራ አድርጐአታል።

የአኩስም ከተማ በታሪክ የ4000 ዓመት ዕድሜ ያላት ሲሆን ስለ ስያሜዋም በሊቃውንቱ ዘንድ አምስት የተለያዩ ምክንያቶች ቀርበዋል።

1. ከጌታችን ልደት በፊት 2000 ዓመት ገደማ በነበረውና የኩሽ የልጅ ልጅ (የኖኅ የልጅ፣ ልጅ፣ ልጅ) የሆነው አኩስማዊ ስሙን ለቆረቆሩት ከተማ ማውረሱ ይነገራል።[1] ከተማውን በቆርቋሪው መሰየም የጥንት ሰዎች ባህል ነበረ። ዘፍ.10።

2. «አኩስም» የሚለው ቃል ከሁለት ጥንታውያን ቋንቋዎች የተገኘ ነው። «አኩ» በአገውኛ ቋንቋ ውሃ ማለት ሲሆን «ሱም» ደግሞ ከሴም ቋንቋ ተወስዶአል። ትርጉሙም «ሹም» የሚለውን ይተረጉማል።

3. በሰሜን አኩስም አንድ የውኃ ጉድጓድ አለ። እሱም «ማይ ሹም» ይባላል። የከተማዋ መጠሪያ ከዚህ የተወሰደ ሳይሆን አይቀርም።

4. አኩስም (አ: ኩሽም—በዕብራይስጥ) — ጥንታዊት፣ ቀዳማዊት የነገደ ኩሽ መዲና፣ አህጉረ ኩሽ [1.ለ]

5. ‹መካነ ዕንቁ ማለት ነው› ይላል ገድለ መርቆሬዎስ ደግሞ። «ወበእንተዝ ተሰምየ ስማ ለይእቲ አኩስም እስመ ትርጓሜሃ ለአኩስም መካነ ስም ብሂል ዝውእቱ መካነ ዕንቁ።»[2]

የአኩስም ከተማ ታሪክ ይበልጥ እየገነነ የመጣው ከጌታችን ልደት በፊት 1000 ዓመት ገደማ ጀምሮ ነው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም ይህ ዘመን ንግሥተ ሳባ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ወደ ኢየሩሳሌም የተጓዘ ችበት፣ ልጅዋም ቀዳማዊ ምኒልክ ታቦተ ጽዮንን በጥበበ እግዚአብሔር ወደ ኢትዮጵያ ያመጣበት ዘመን በመሆኑ ነው።

ብሉይ ኪዳን ይህችን ኢትዮጵያዊት ንግሥት ንግሥተ ሳባ ከማለት

## አኩስምና ታቦተ ጽዮን


ከባስልዮስ ዘቂሣርያ

በቀር ቦታዋን በደንብ አልጠቀሰም[3]። ጌታችን ግን በመዋዕለ ትምህርቱ ንግሥተ አዜብ በማለት ጠርቷታል።[4] አዜብ ደቡብ ማለት ሲሆን ኢትዮጵያ በድሮው ግዛትዋ ለእሥራኤል ደቡብ ነበረች። ጌታ ንግሥተ አዜብ ያላትም ለዚህ ነበር። ይህንን ቃል ከእርስዋ በኋላ 1500 ዓመት ቆይተው የተነሡት የኢትዮጵያ ነገሥታት ሳይቀሩ ይጠቀሙበት እንደነበር የቤተ ክርስቲያን መዛግብት ያስረዳሉ።

«ወንግሠ ገብረመስቀል በጽድቅ ጣበርትዕ ወተሰምዓ መንግሥቱ ኩሉ ምድረ አዜብ»[5]

ስለንግሥተ ሳባ ኢትዮጵያዊነት የሚያስረዱ የተለያዩ ማስረጃዎች ይገኛሉ። ከጥንታውያን የታሪክ ጸሐፍት መካከል የሚቆጠረው ዮሴፍ ወልደ ኩርዮን ስለዚህችው ንግሥት «በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያና የግብፅ ንግሥት የነበረችው» በማለት ነበር የጻፈው።[6] ላዕላይ ግብፅ ከጥንት ጀምሮ የኢትዮጵያ ግዛት እንደነበር የታወቀ ነው። የግብፃውያን (ቅብጦች) ትልቁ የታሪክ መዝገብ የሆነው የፓትርያርኮች ታሪክም እንዲህ ይላል። «የታላቁ ሀገር አቢሲንያ ንግሥት እርስዋም ንግሥተ ሳባ የምትባለው የደቡብ ንግሥት፣ ወደ ዳዊት ልጅ ሰሎሞን መጣች።[7]

ከዚህም በተጨማሪ ደግሞ በኢትዮጵያችን ከንግሥተ ሳባ ጋር የተያያዙ ልዩ ልዩ የአርኪዎሎጂ (የከርሰ ምድር ጥናት) ውጤቶች ተገኝተዋል። ለምሳሌም:-



በ፲፱፻፶፯ ዓ.ም.
ሥራው ያለቀው
የአኩስም ጽዮን
ቤተ ክርስቲያን

አፄ ኃ/ሥላሴ
ያሠሩት
የአኩስም ጽዮን
ቤተ ክርስቲያን




©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

1. የንግሥተ ሳባ ትውልድ ቦታ:- በሰሜን ደንገሎ፣ በደቡብ ፎካዳ በተባሉ በሁለት ተራሮች መካከል የሚገኝ ሲሆን ስሙም ‹ጕሎ ማከዳ› ይባላል።[8]

2. የንግሥተ ሳባ መቃብር:- ከአኩስም ወደ ጐንደር በሚወስደው መንገድ ዳር በስተደቡብ 2 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሚገኝ።

3. የንጉሥ ምኒልክ 1ኛ መቃብር:- ከአኩስም ከተማ በስተ ምዕራብ 2 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሚገኝ።

በ1906 የደች ልዑካን የአርኪዎሎጂ ጥናት በሚያደርጉ ጊዜ ከምድር ውስጥ በተቀበረ ቤት ውስጥ የንጉሥ ምኒልክን ዐፅም ያገኙ ሲሆን የአኩስም ጽዮን ካህናት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በክብር እንዳሳረፉት ይታወቃል።[9]



በከፊል የሚያሳይ የአክሱም ከተማ

በ13ኛው መ/ክ/ዘ የነበሩት የአኩስሙ ንቡረ ዕድ ይስሐቅ ከተለያዩ ምንጮች ክብረ ነገሥትን ሲያዘጋጁ እጅግ ታላቅ ቦታ ከሰጡዋቸው ታሪኮች መሐል አንዱ የንግሥተ ሳባ ታሪክ ነው።

ለንግሥተ ሳባ ወደ ኢየሩሳሌም መጓዝ ምክንያት የሆናት ታሞሪን የተባለው ነጋዴ ነው። ንጉሥ ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን ለመሥራት በተነሣ ጊዜ ለመሥሪያ የሚሆን ዕቃ ከየሀገሩ ያመጡለት ዘንድ ለነጋድያን መልእክት አስተላልፎ ነበር። የኢየሩሳሌም ሰዎችም ዕንቁ፣ ወርቅና ብር በሚገኝበት በኢትዮጵያ የነገሠችው የንግሥተ ሳባ ነጋዴ ስለሆነው ታሞሪን ለንጉሥ ሰሎሞን አወሩለት: ንጉሥ ሰሎሞንም ታሞሪንን ጠርቶ አነጋገረውና ለሌሎች የሰጠውን አደራ ለእርሱም አስረከበው።

ታሞሪን ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ ያየውን፣ የሰማውንና የተላከውን ለንግሥተ ሳባ ነገራት። እርስዋም የሰሎሞንን ጥበብ በሰማች ጊዜ ታየው ዘንድ እጅግ ጓጓች። በዚህም የተነሣ በታሞሪን መሪነት ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዘች።[10]

ንግሥተ ሳባ ከኢየሩሳሌም ስትመለስ ከጠቢቡ ሰሎሞን ፀንሳ ነበር። የመጀመሪያ ልጅዋን ምንልክን የወለደችው በዛሬዋ አሥመራ ከተማ አጠገብ መሆኑ ይነገራል። ቀዳማዊ ምኒልክ ካደገ በኋላ (በ12 ዓመቱ) ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዞ ሥርዓተ አይሁድን፣ ሕገ ኦሪትን ተምሮአል። ሲመለስም በፈቃደ እግዚአብሔር ታቦተ ጽዮንን ይዞልን መጥቷል። ይህች ታቦት ለ3000 ዓመታት ያህል እስከ ዛሬ ድረስ በኢትዮጵያ በአኩስም ትገኛለች። ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው።

በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረው ታሪክ ጸሐፊው አቡሳላህ አቢሲኒያውያን በእግዚአብሔር ጣቶች አሥርቱ ቃላት የተጻፈባት፣ ሁለቱ የድንጋይ ጽላቶች ያሉባት የቃል ኪዳኑ ታቦት አለቻቸው በማለት ጽፎ ነበር።[11] ዘመናችን ይህችን ታቦት ፍለጋ ጥናት ያደረገው ግርሃም ሐንኮክም «ዘሳይን ኤንድ ዘሲል» በተሰኘው መጽሐፉ ይህንን ገልጦታል።

ዛሬ በዘመናችን ከመላ ዓለም የሚሰባሰቡ የእመቤታችን ወዳጆች ይህችን ታቦት ለመሳለም፣ ወደ አኩስም ከተማ ይጐርፋሉ። ይህ ዕለት የሚከበረው ታቦተ ጽዮን የፍልስጤማውያንን ጣዖት በአልን ያጠፋችበት፣ አምልኮ ባዕድንም ድል የነሣችበት፣ በአረማውያንም ዘንድ ክብርዋን ታላቅነትዋን የገለጠችበት በመሆኑ ነው። 1ሳሙ.5፤6፤7። ከዚህም ሌላ ደግሞ ታቦተ ጽዮን የኢትዮጵያን ምድር የረገጠችበት የመታሰቢያ ዕለትም ነው።

## የአኩስም ቤተ ክርስቲያን

በሞኩራብ ለነበረችው ለታቦተ ጽዮን የመጀመሪያውን ቤተ ክርስቲያን ያሠሩት አብርሃና አጽብሐ የተባሉት ነገሥታት ናቸው። ሁለቱ ወንድማማቾች በአቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ስብከት አምነው በተጠመቁ ጊዜ ለአኩስም ጽዮን ባለ 12 መቅደስ (አምስት፣ አምስት ክፍል ያለው) ባለ 72 አዕማድ የሆነ ቤተክርስቲያን አሠርተው ነበር።[12] ይህ ቤተ ክርስቲያን ለ600 ዓመታት ያህል ሲያገለግል ከኖረ በኋላ በዮዲት ዘመን ፈራረሰ። ቀጣዩን ቤተ ክርስቲያን አፄ አንበሳ ውድም ባለ 7 ክፍል አድርጎ ቢያሠራውም ግራኝ አፈራረሰው። በመጨረሻ አፄ ፋሲል [12ሀ] ጥንታዊውን አፄ ኃይለ ሥላሴ ደግሞ ዘመናዊውን ቤተ ክርስቲያን አሠርተውላታል።

## የአኩስም ትምህርት ቤት

በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን ከታቦተ ጽዮን ጋር ለቤተመቅደስ አገልግሎት የሚሰው ካህናተ ኦሪት መምጣታቸውን ክብረነገሥት ይነግረናል። እነዚህ ምሁራን ኦሪት ለተተኪው ትውልድ ብሉይ ኪዳንን ሥርዓተ ኦሪትን የሚያስትምሩበት የመጀመሪያውን ትምህርት ቤት በአኩስም ከተማ ከፈቱ። በአቡነ ሰላማ ዘመን የነበረው የአኩስም መምህር እንበረም ይባል ነበር።

አቡነ ሰላማ ጵጵስና ተሹመው ሲመጡ በቅድሚያ ከሠሩዋቸው ተግባራት አንዱ የአኩስሙን ትምህርት ቤት በክርስትና ትምህርት ማጠናከር ነበር። በዚህም መሠረት እንበረምን ‹ሕዝበ ቀድስ› ብለው ኤጲስ ቆጶስነት ሹመው የአኩሱሙን ት/ቤት እንዲመሩ አደረጉዋቸው። በት/ቤቱ የነበሩ ሰባት ምሁራንንም የቅስና ማዕረግ ሰጥተው ተዘዋውረው እንዲያስተምሩ ላኩዋቸው።

ከአኩስም ት/ቤት ይወጡ የነበሩት የወንጌል ልዑካን «ላዕካነ ጽዮን»



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

እየተባሉ ይጠሩ ነበር።[13] አቡነ ሰላማ ከነዚህ ምሁራን አምስት ቆሞሳትን በመሾም በዚያ ዘመን የኢትዮጵያ ግዛት ወደነበሩት ኑብያ፣ አኑይ መርዌና የመን በመላክ ስብከተ ወንጌል እንዲስፋፋ አብያተ ክርስቲያናት እንዲተከሉ ማድረጋቸውን በካይሮ የአፍሪካ ጥናት ፕሮፌሰር የሆኑት ዶ/ር ህያርድ ባቀረቡት ጥናት ገልጠው ነበር።[14]

በመላዋ ኢትዮጵያ ለተስፋፋው ትምህርተ ክርስትና መሠረት የሆነው ይህ የአኩስም መንፈሳዊ ት/ቤት ነበር። ሊቁ ቅዱስ ያሬድም የዚሁ ት/ቤት ውጤት ነው።

### ማኅበረ ጽዮን

በኢትዮጵያ ውስጥ የመጀመሪያዋ የጽዋ ማኅበር «ማኅበረ ጽዮን» ትባላለች። የመሠረቱዋት አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ሲሆኑ ጊዜውም 347 ዓ.ም ነበር[15] ጽዋው ይጠጣ የነበረው በአኩስም ጽዮን ቤተ ክርስ ቲያን ቅጽረ ግቢ ሲሆን የተቋቋ መችበት ዋና ዓላማም:-

- የቅዱሳንን በረከት ለማግኘት፣
- ድሆችን ለመርዳት፣
- ቤተ ክርስቲያን በየቦታው ለማሠራት፣
- ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋት ነበር።

እንግዲህ በአጠቃላይ የአኩስም ከተማ የብሉይም የሐዲስም ማዕከል፣ የእናታችን የጽዮን መንበር በመሆንዋ በታሪካዊነቷና በቅርሶችዋ የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ቅድስት ከተማ ለመሆን በቅታለች። ለዚህም ነው በየጊዜው በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ምእመናን ለመሳለም፣ ለመባረክ ወደ አኩስም ጽዮን የሚጐርፉት። አኩስም ጽዮን የመላ ኢትዮጵያ ክርስቲያኖች እናት ከተማ ናትና:-

- የፈረሰው ተጠግኖ፣
- ለንዋየ ቅድሳትና ቅርሶች ማስቀመጫ ቤተ መዘክር ተሠርቶ፣
- ቢቻል ቅጽርዋ ይጠበቅ ዘንድ ቅድስቲቱ ከተማ ዙርያዋ ታጥሮ፣
- ለታሪክ ማስታወሻ፣ ትውፊቱን መጠበቂያ የሚሆኑ ት/ቤቶች በሥርዋ ተቋቁመው፣

ዘወትር ሁላችንም ብንንከባከባት በእምነታችን፣ በታሪካችን፣ በአባቶ ቻችን እንድንኮራ ታስችለናለች። ❖


ዋቢ

1. (The Dictionary of Ethiopian Biography, v. 1 p. 16)
 1.ለ. ኪ.ወ.ክ መዝገበ ቃላት፣ ገጽ 219)
2. Gadla Merqorewos, Csco, Scriptores, Aethopic, Vol, XXII (1904), P.24
3. 1 ነገሥት 10:1:10ሀ: 2ዜና 9:1–12
4. ማቴ. 12፥42።
5. I. Guidi,I1, Gadla Aregawi p. 71
6. F. Josephus, Jewish Antiquities, ed. J. Thackeray and R. Maraus, (Web. Classical Library, London, 1961), vol. VIII, pp. 165-175.
7. ይህ ከፓትርያርክ ቆስሞስ (290–32) የሕይወት ታሪክ የተቀዳ ነው። (The History of the Patriarchs, ii, pt. 2, p. 118)
8. Ancien and Medival Ethiopian History, P40
9. Ibid. p. 41
10. Budge, the Queen of sheba, pp. 17-18
11. The Churches and Monastries in Egypt. Ed. and Er. Euetts, B.T.A. (oxford 1895), pp. 287-8.
12. ትንሣኤ ቁ.114/79፣ ገጽ 21
12–ለ. ትንሣኤ የ25 ዓመታት መንፈሳዊ ርምጃ፣ ገጽ 38
13. ትንሣኤ ቁ. 60/75፣ ገጽ 24
14. ትንሣኤ ቁ.60/75፣ ገጽ 23
15. ትንሣኤ ቁ.126/80ሀ: ገጽ 9


# እርቅ በማኅፀን ተጀመረ

ከወ/ት ወደር የለሽ ሀብት ይሁን

«እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወን ድም ልጅ ትወልዳለች» ኢሳ.7 ቁ.14 ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች»

እግዚአብሔር ይህንን ዓለም ካለ መኖር ወደ መኖር አምጥቶ (ፈጥሮ) የዚህ ዓለም አዛዥና ገዥም አድርጐ አዳምን ሾመው። ዘፍ.1፥1–37 ኩፋሌ 3፥1 ነገር ግን እግዚአብሔር አምላክነቱ፣ ከሃሊነቱ፣ ገዥነቱ የባሕ ሪው መሆኑን ሲያጠይቀው በገነት ካለው ዛፍ ሁሉ ፍሬውን ብላ ግን መልካምንና ክፉውንም ከምታሳው ቀው ዛፍ ግን ከፍሬዋ አትብላ። የበላህ ዕለት የሞት ሞትን ትሞታለህ ብሎ አዘዘው። ዘፍ.2፥16–17። በቀድ ሞው እባብ (በሰይጣን) ምክር ተደፋፍሮ የፈጣሪውን ፈቃድ በመተላለፉ በእግዚአብሔር ፊት ቀርቦ መርገምና ፍርድን ተቀበለ። ዘፍ.3፥1–19። ራዕ.12፥9። ይኸው መሠረተ ኃጣውዕ በሆነው መብል ምክንያት ሕግ ፈርሶ ከሚወዳት ገነት ዕፀሕይወትን በልቶ ለዘለዓለም ሕይወት እንዳያገኝ ተባረረ። በኃጢ አት በትር ተገረፈ በእግረ አጋንንት ተረገጠ። ዘፍ.3፥ 22–24።

አዳም ከበደሉ ተፀፅቶ ንሰሐ ገብቶ ምሕረትን ቢለምነው አምላካ ችን እግዚአብሔርም የቸርነት ባለቤት የይቅርታ ጌታ ነውና የጠፋውን ልጁን በፍቅሩ ሊያቀርበው ከወደቀበት በክንዱ ሊያነሣው ስለወደደ የዓለም ቤዛ የሚሆን ታላቅ መድኃኒት ይመጣል እርሱም ያሳተህን ያስፈረ ደብህን እባብ (ሰይጣን) የሚቀጠቅጥና ድል የሚነሣው ይሆናል ብሎ ተስፋ ሰጠው። «እግዚአብሔር አምላክም እባቡን አለው ይህን ስለ አደረግህ ...በአንተና በሴቲቱ መካከል በዘርህና በዘርዋ መካከል ጠላትነትን አደርጋ ለሁ እርሱም እራስህን ይቀጠቅ ጣል።...» ዘፍ.3፥14። በማለት ድኅረ ዓለም ከአዳም ከአብራኩ ከምትከፈለው ንፅሕት ድንግል ከሰማየ ሰማያት ወርዶ እንደሚወ ለድና እንደሚያድነው ነገረው «የአዳም ተስፋው አንቺነሽ» ብሎ አባ ሕርያቆስ እንደተናገረ።

ይኸው የበደል ዕዳ ለአዳም ዘር ሁሉ ተላለፈ። ሮሜ.5፥12። እነዚ ህም ከዚህ ዕዳ ነፃ አውጥቶ ወደ ጥንት ርስታቸው የሚያስገባቸውን ሲፈልጉ ለአዳም የሰጠውን የተስፋ ቃል



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

መፈፀም በተለያየ ምሳሌና ትንቢት አስቀድሞ ገልጦላቸው ነበር።

ሊቀ ነቢያት ሙሴ በሲና በረሃ እሳትና ሐመልማልን አዋሕዶ በኋላ ዘመን የሚገለጠውን የሥጋና የመለኮትን ተዋሕዶ አሳየው ዘጸ.3፥1–8። በኋላም በደብረ ሲና የእመቤታችን ምሳሌዋ የምትሆነውን ታቦተ ጽዮንን ሰጠው ዘጸ.37።

እንዲሁም የዚህን የዕርቅ ነገር በነቢያቱም አድሮ ተናግሮአል። አባታችን ነቢዩ ዳዊት «ልጄ ሆይ ስሚ ጆሮሽን አዘንብይ የወገንሽን ያባትሽን ቤት እርሺ ንጉሥ ውበትሽን ወዶአልና» መዝ.44፥10–11 ብሎ የወገኑ ልጅ የሆነች እመቤታችንን አምላክሽ የሆነ ጌታሽ ንፅሕናሽን ቅድስናሽን መርጦ ማደሪያ ሊያደርግሽ ወድዋልና ይህንን ዓለም እርሺ› ብሎ በትንቢት መስተዋት አይቶ መወለዱን ተነበየ። እንዲሁም ነቢዩ ኢሳይያስ «እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ እንደሰዶም በሆንን እንደ ገሞራም በመሰልን ነበር» ኢሳ.1፥9 በማለት ምንም እንኳ የአዳም ልጅ ብትሆንም ጥንተ አብሶ የሌለባትን ንጽሕት ዘርን ማደሪያው ትሆን ዘንድ ባያስቀርልን ኖሮ በኃጢአታቸው እንደጠፉት ሰዶምና ገሞራ እኛም በበደላችን ጠፍተን እንቀር ነበር። ይህች ንፅሕት ዘር ለእርቃችን ምክንያት ሆነች› በማለት ተናገረ።

«ጌታ እራሱ ምልክት ይሰጣችኋል እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድም ልጅ ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች» ኢሳ.7፥14 ማቴ.1፥23 በማለት ይኸው ነቢዩ ኢሳይያስ የድኅነታችን ነገር በማኅፀነ ድንግል እንደሚጀመር ሕፃን ኃያል መካር የዘለዓለም አምላክ የሁሉም አባት ነው ብሎ አስቀድሞ መሰከረ ኢሳ.9፥6። ነቢዩ ሚልክያስም ስሙን ለሚፈሩ ትዕዛዙን ለሚጠብቁ ለአባቶቻችን ለአብርሃም፣ ለይስሐቅ፣ ለያዕቆብ የሚለውን ለዳዊት ከዘርህ ለዘለዓለም የሚነግሥ ንጉሥ አስነሣለሁ ብሎ ቃል የገባውን አስቦ እውነተኛ ፀሐይ የሆነው አምላካችንን ወልደ እግዚአብሔር ሰው እንደሚሆን ተነበየ። ሚል.4፥2።

እግዚአብሔር ለሚሠራው ሥራ ጊዜ ያለውና በቀን ቀጠሮው የሚገኝ፣ እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውኃ ፈሳሽ በአጋጣሚ የማይሠራ ስለሆነ ጊዜያቱ በደረሰ ሰዓት ለአባቶቻችን በምሳሌና በትንቢት የገለጠውን ይፈጽም ዘንድ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልን ልኮ ከንጽሕት ቅድስት ድንግል ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነሥቶ በተዋሕዶ እንደሚወለድ አበሰራት። እሷም እኔን ባሪያውን አገልጋዩን ለዚህ ከመረጠኝ እንደ ቃልህ ይደረግልኝ ባለች ጊዜ ምሕረት ተጀመረ። እግዚአብሔር ወዶ በፈቃዱ ሰውን ሊምረው እርቁን በማሕፀን ጀመረ። ሉቃ.2፥26–28 ይህንንም ሐዋሪያው ቅዱስ ጳውሎስም ሲያስረዳ «የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር» ከሴት የተወለደውን ልጁን ላከ «ገላ.4፥4 ብሏል።

አባታችን ጻድቁ ዮሴፍም መልአክ በሕልሙ ጠርቶ ከድንግል ማርያም የሚወለደው ሰውን ሁሉ ከኃጢአት የሚያድን የዓለም መድኃኒት ነው ብሎ ስለነገረው እግዚአብሔር ሰውን ይቅር ማለት መጀመሩን ተረዳ። ማቴ.1 ቁ.20–21።

በዚያም ወራት ዓለሙ ሁሉ እንዲጻፍ (እንዲቆጠር) ከአውግስጦስ ቄሳር ታዞ ስለነበር እመቤታችን ድንግል ማርያም ከዳዊት ዘር በመሆንዋ ትቆጠር ዘንድ ወደትውልድ ሀገርዋ ከገሊላ ወደ ቤተልሔም ወጣች። በነቢዩ ሚክያስ የተነገረው ትንቢት ይፈፀም ዘንድ የመውለጃዋ ወራት ስለደረሰ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በከብቶች በረት በቤተልሔም ወለደችው ሚል.5፥2። ልደቱም በማኅፀን የተጀመረውን እርቅ ለመላው ዓለም በመወለድ ገለጠው። መላእክትም ይህንን ድንቅ ነገር ለእረኞች ነገሩ። ምሥጋናም በአንድነት አቀረቡ «ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ። ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጐ ፈቃድ› በማለት የእግዚአብሔር የቸርነቱን ነገር ሰውና መላእክት አብረው ዘመሩ። እረኞችም ወደ ከተማም ገብተው ይህንኑ አበሰሩ።

ይኸንኑ የእርቅ ብሥራት ለማየት የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት አለ እያሉ ሰብአ ሰገል ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጡ። ይመራቸውም የነበረው ኮከብ ሕፃኑ ባለበት ቆመ። ገብተውም ሰገዱለት። እጅ መንሻውንም አቀረቡለት። ወርቁን ንጉሠ ነገሥትነትህ የባሕሪህ ነው ሲሉ፤ ዕጣኑንም የዓለምን ኃጢአት የምታሠርይ ሊቀ ካህን ነህ ሲሉ፤ ከርቤውንም ስለኛ ኃጢአት ተገብተህ መራራ ሞትን ትቀበላለህ ሲሉ አበረከቱለት።» ማቴ.2፥1–12።

እንግዲህ እኛ ክርስቲያኖች በየዓመቱ የልደትን በዓል ስናከብር መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለኛ ሲል ከሰማየ ሰማያት ወርዶ በእመቤታችን ማኅፀን የጀመረውን የሰውን ልጅ ከራሱ ጋር የማስታረቅ ሥራ በቤተልሔም በረት በትህትና የገለጠበትን ታላቅ ዕለት ማሰባችን ነው። በዚህ ዕለት የዓለምን ኃጢአት ሊያስተሰርይ ወደኛ የመጣውን ንፁሑን የእግዚአብሔር በግዕ ሥጋውን በልተን ደሙን ጠጥተን በዓሉን በሰላምና በፍቅር እናከብር ዘንድ ይገባናል። ለዚህም እግዚአብሔር ያብቃን። ✣

## እኛ ወይስ...

እጅሽን ዘርግተሽ የሰበሰብሻቸው፣
ዘወትር ከማዕድሽ የምትመግቢአቸው፣
ሰይጣን በስንፍና ገብቶ ቢያስታቸው፣
ከቤትሽ በመግባት ተቀርቋሪ መስለው፣
ውለታሽ ይህ ሆኖ ለአንቺ የሚገባው፣
እናድስሽ አሉ ያረጀሽ መስሏቸው።
ክርስቲያኖች ሁሉ እናስተውል በእውነት፣
መታደስ ያለብን እኛ ወይስ እምነት?

ዲ. ሙሉጌታ ዓለሙ
(ከአምሃራ ሳይንት)



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ትምህርተ ሃይማኖት

ይህ ዓምድ ስለ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያናችን ትምህርተ ሃይማኖት (እምነትና ቀኖና) የምንማርበት ነው።

## ምሥጢረ ጥምቀት

ከብርሃኑ ጎበና

ካለፈው የቀጠለ

ባለፈው እትማችን በጥምቀት የሚገኘውን ልጅነትና ክብር የገለጥን ሲሆን በዛሬው እትማችን ደግሞ ቀሪውን እናስነብባችኋለን።

### አጥማቂው ማነው?

ሊያጠምቁ የሚገባቸው ሥልጣነ ክህነት ያላቸው ሰዎች ማለትም ቄስ ወይም ጳጳስ መሆን እንዳለባቸው የቤተክርስቲያን ቀኖና ያዛል። ዳሩ ግን በክርስቶስ ያመነ ሁሉ ካህን ነውና ሊያጠምቅ ሥልጣን አለው የሚለው አመለካከት የተሳሳተ ነው። ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን መፈጸም የሚገባቸው ሥልጣነ ክህነት የተሰጣቸው ብቻ እንጂ ሥልጣነ ክህነት የሌላቸው ምእመናን ሊሆኑ አይገባም። አይሆንምም። ሥልጣነ ክህነት በሌለው ሰው የተደረገ ጥምቀት አማናዊ ጥምቀት አይደለም። ከሥላሴም ልጅነትን አያሰጥም። ምክንያቱም ጌታ አጥምቁ ብሎ የላካቸው ከሌላው ሁሉ መርጦ የሾማቸውን ሐዋርያቱን እንጂ ያመኑትን ሁሉ አይደለም። ማቴ.28፥19። ማር.16፥16።

ሐዋርያት ሥልጣነ ክህነትን ከጌታ መቀበላቸው በወንጌል ተመዝግቧል። «ይህንንም ብሎ እፍ አለባቸውና መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ» ይላል። ዮሐ.20፥22። ይህም ሥልጣነ ክህነት ለመሆኑ ማረጋገጫችን ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል። የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው። ዮሐ.20፥23። በማለት ልጅነትን ሳይሆን ሥልጣነ ክህነትን እንደሰጣቸው ቅዱስ ወንጌል ያስተምረናል። ምክንያቱም ልጅነት ኃጢአት ሊያስተሠርይ ከኃጢአት ሊፈታ ሊያስር አይችልምና ነው። ሥልጣነ ክህነት ግን ኃጢአትን ሊያስተሠርይ ከኃጢአት ሊፈታና ሊያስር ይችላል።

ስለዚህ ለማጥመቅም ሆነ ሌሎችንም ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን ለመፈጸም ሥልጣኑ ያላቸው ካህናት እንጂ ሌላው ምእመን አይደለም። በዚህም የተነሣ ቤተክርስቲያን በምእመናን የሚፈጸመውን ጥምቀት እውነተኛ ጥምቀት አድርጋ አትቀበለውም።

### የጥምቀት አፈጻጸሙ

ጥምቀት አጥመቀ (አጠምቀ) ካለው ግስ የወጣ ነው። ፍቺውም በግብር መንከር፣ መድፈቅ፣ መዝፈቅ ሲሆን በተገብሮ መነከር፣ መደፈቅ፥ መዘፈቅ መላ አካልን ውኃ ውስጥ ማስገባት ማለት ነው።

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያናችን የምታጠምቀው ከላይ እንደታተተው በትርጉሙ መሠረት ተጠማቂውን ውኃ ውስጥ በማጥለቅ ነው። ይህም ማለት ውኃው የተጠማቂውን መላ ሰውነት እስኪያለብስ ድረስ መላ አካሉን ውኃ ውስጥ በመድፈቅ ወይም ከራስ ጀምሮ በሰውነት ላይ በማፍሰስ ነው።

ሥርዓተ ጥምቀቱ በዘፈቀደ የሚከናወን ሳይሆን ትርጉምና ምሳሌ ባለው ሥርዓትን በጠበቀ መልኩ ነው። በቅድሚያ ለማጥመቂያ በተዘጋጀው ውኃ ላይ ካህኑ መጽሐፈ ክርስትና (ጸሎተ ጥምቀት) ያደርስበታል። ጸሎተ ጥምቀቱን ካህኑ ሲጸልይ እጁን በተጠማቂው ላይ ጭኖ ነው።

የተጠማቂውን የክርስትና ስም ሲሰይምም እጁን በትእምርተ መስቀል በተጠማቂው ላይ አኑሮ «ይኩን ስምከ እገሌ» እያለ ስመ ጥምቀቱን ሦስት ጊዜ በመጥራት ነው።

በሚጠመቅበት ጊዜ ተጠማቂው ፊቱን ወደ ምዕራብ ይመልሳል። ወደ ምዕራብ የሚመልስበት ምክንያት አዳም ትእዛዘ እግዚአብሔርን ጥሶ ወደ ሲኦል መውረዱን ለማዘከር ነው። ሲኦል በምዕራብ ናትና።

በመቀጠል ተጠማቂው በውኃው አንፃር መቆም ይኖርበታል። ይኸውም የሚያመለክተው አዳም አባታችን የድኅነትን ተስፋ መስማቱን ለማዘከር ነው። ምክንያቱም ድኅነት በጥምቀት ነውና ማር.16፥16።

ካህኑ ካጠመቀው በኋላ የተጠማቂውን እጁን ይዞ ወደ ምሥራቅ ፊቱን የሚመልስበት ምክንያት ጌታ በጥምቀት ከጨለማ ወደ ብርሃን፣ ከሞት ወደ ሕይወት፣ ከሲኦል ወደ ገነት እንደመለሰን ለማስረዳት ነው። ምሥራቅ የገነት ዘፍ.2፥8፤ የእመቤታችን ሕዝ.44፥1–9። ምሳሌ ጌታ የተሰቀለባት መድኅኒት የተገኘባት ናትና። «እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም።» ዮሐ.3፥5።

ካህኑ በተጠማቂው ፊት ላይ «ንሣእ መንፈስ ቅዱስ» ትርጉሙ «መንፈስ ቅዱስን ተቀበል» እያለ እፍ ይልበታል። ቀጥሎ ቅብዐ ሜሮን ይቀባዋል። ካህኑ ሜሮን ሲቀባ የተጠማቂውን ሰውነት ክፍል ክፍሉን እየለየ በትእምርተ መስቀል ሠላሳ ስድስት ሕዋሳቱን ይቀባዋል። በመጽሐፈ ጥምቀት እንደተገለጠው ካህኑ ሴቷን ካደገች በኋላ አምና የምትጠመቀውን ካንገቷ በላይ ያሉትን አካላቷን ይቀባል። ካንገቷ በታች ያሉት አካላቷን ዲያቆናዊት ሴት የካህኑን እጅ ይዛ ትቀባታለች።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በጸሎተ ቡራኬና አንብሮተ እድ በተጠማቂው ላይ ይጸልያል። ከዚህ በኋላ ለክርስትና አባቱ ሲሰጠው አዲስ ልብስ ያለብሰዋል ይህም አበሳው እንደተወገደለት መታደስን እንዳገኘ ያሳያል። ዘካ.3፥1–5።

ጥምቀት በሚያጠልቅ ውኃ እንዲሆን የታዘዘበት ምክንያት የተጠማቂውን መላ አካል እንዲያጠልቀው ተብሎ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳስተማረን «ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደተጠመቅን አታውቁምን? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን»። ሮሜ.6፥34።

በጥምቀት ከጌታችንና ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አብረን መቀበራችንን ሐዋርያው አስገንዝቦናል። መቃብር ደግሞ መላ ሰውነትን የሚውጥ (የሚያለብስ) እንደመሆኑ ከጌታ ጋር አብረን የመቀበራችንን ምሥጢር የሚገልጠው ጥምቀትም መላ አካላችንን ማለትም ከራስ ጠጉራችን እስከ እግር ጥፍራችን ድረስ የሚያጠልቅ (የሚያለብስ) ውኃ መሆን አለበት።

በተጨማሪም በጥምቀት ከእግዚአብሔር በጸጋ የምንወለድ በመሆኑ መላ አካላችን ውኃ ውስጥ ጠልቆ መውጣት ይኖርበታል። የሥነ ፍጥረትን ሕግ ተከትለን ስንሄድ መወለድ ከተሰወረ ከማይታይ ጨለማ ከሆነ ክፍል ብርሃን ወደ ሆነ ዓለም መውጣት እንደሆነ ሁሉ በጥምቀትም ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ተጎናጽፈን ብርሃን ለብሰን ከእግዚአብሔር የምንወለድ በመሆኑ ተጠማቂው መላ አካሉ ውኃ ውስጥ ጠልቆ መውጣት ይኖርበታል። ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ መወለዱን ለማረጋገጥ።

ካህኑ ተጠማቂውን በውኃው ውስጥ ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ የሚያደርግበት ምክንያቱ ምንድን ነው? ብሎ ለሚጠይቅ መልሱ እንደሚከተለው ተገልጿል።

ካህኑ ተጠማቂውን በውኃው ውስጥ ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ እያደረገ ማጥመቁ ምሳሌ አለው። ቀደም ተብሎ እንደተገለጠው መጥለቅ ወደ መቃብር የመውረድ ሲሆን መውጣት (ብቅ) ማለት ደግሞ የትንሣኤ ምሳሌ ነው። ይህ ግብር ሦስት ጊዜ መፈጸሙ ደግሞ የሥላሴ ምሳሌ ሲሆን ግብሩ ደግሞ አንድ ዓይነት መሆኑ የአንድነት ምሳሌ ነው። እንዲሁም በውኃው ውስጥ ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ ማለቱ ክርስቶስ በከርሠ መቃብር 3 መዓልት 3 ሌሊት አድሮ የመነሣቱ ምሳሌ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስም ጥምቀት ውኃ ውስጥ መላ አካልን በማጥለቅ መከናወን እንዳለበት ያስረዳል። ለዚህም እንደምሳሌነት አድርገን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ጥምቀትና ቅዱስ ፊልጶስ ያጠመቀውን የኢትዮጵያ ንግሥት የሕንደኬን ጃንደረባ ልንወስድ እንችላለን። ጌታ በዮሐንስ እጅ ሲጠመቅ መላ አካሉን ውኃ ውስጥ ጠልቆ በመውጣት እንደነበር ማስተዋል ይቻላል። ይህንንም ወንጌላዊው ቅ/ማቴዎስ እንዲህ ሲል ገልጾታል። «ኢየሱስ ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃ ወጣ» ማቴ.3፥16። ማር.1፥10።

ሐዋርያው ፊልጶስም ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ባጠመቀበት ጊዜ ወደ ወንዝ አውርዶ መላ አካሉን ውኃ ውስጥ አጥልቆ እንዳጠመቀው «ከውኃ ካወጣ በኋላ» የሚለው አነጋገር ያስገነዝበናል። የሐዋ.8፥38–39።

የጥምቀት ምሥጢራዊ ትርጉሙ ከክርስቶስ ጋር አብሮ መቀበር ማለት መሆኑን ከላይ ገልጸናል። መቃብር ደግሞ ሙሉ አካልን የሚውጥ እንጂ ከፊሉን ውጦ ሌላውን የሚያስቀር አይደለም። ሁሉም አካል በመሬት ውስጥ ይዋጣል ከጌታችን ጋር አብረን መቀበራችንን ለማስመስከር ስንጠመቅም መላ አካላችን ውኃ ውስጥ ሊጠልቅ እንደሚገባውም ከላይ ተገልጾአል። ለዚህ ማጠናከሪያ የሚሆኑ ማስረጃዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ መጥቀስ ቢቻልም «ለጠቢብ ሰው አንዲት ቃል ትበቃለች» ስለ ተባለ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎች በላከው መልእክት ላይ ጥምቀትን አስመልክቶ የተናገረውን በመጥቀስ ይህን ንዑስ ርእሳችንን እናጠቃልላለን። «በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀብራችሁ በጥምቀት ደግሞ ከሙታን ለይቶ በአስነሣው በእግዚአብሔር አሠራር በማመናችሁ ከእርሱ ጋር ተነሣችሁ» ቆላ.2፥12። በተጨማሪም በጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የማጥመቂያ ገንዳዎች መገኘታቸው የመጠመቂያ ውኃ ሰውነትን ለማጥለቅ እንዲችል ሆኖ መዘጋጀት እንዳለበት ያስረዳል።

## የሕፃናት ጥምቀት

አንዳንድ ሰዎች የሕፃናትን ጥምቀት ሲነቅፉና ትክክለኛ ጥምቀትም እንዳልሆነ ሲናገሩ ይሰማሉ። ይህ ተራ ትችት ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የሌለው ነው። እነዚህ ክፍሎች ራሳቸው ከአእምሮአቸው አመንጭተው ሳስተማሩት ሐሰተኛ ትምህርት መጽሐፍ ቅዱስ ያስተማረው አስመስለው ለማቅረብ ሲሞክሩም ይስተዋላሉ። ለምሳሌ ያህል «ያመነ የተጠመቀ ይድናል» የሚለውን በመጥቀስ በመጀመሪያ እምነት ይቀድማል ለማመን ደግሞ መማር፣ ማወቅ፣ ማገናዘብና አምኜአለሁ ተቀብያለሁ ሊባል ይገባል። ሕፃናት ግን የሚያውቁት ነገር ስለሌለ አላመኑም ስለዚህ ያላመኑ ሕፃናትን ማጥመቅ ተገቢ አይደለም ይላሉ። ዳሩ ግን ቤተክርስቲያን ወንዶችን በተወለዱ በ40 ቀናቸው ሴቶችን በተወለዱ በ80 ቀናቸው የምታጠምቀው መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርጋ ነው።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ሀ. ሕፃናት የዘላለምን ሕይወት እንዲያገኙ ወላጆቻቸውና ቤተ ክርስቲያን የሚሹት ነው። ያለ ጥምቀት ደግሞ ዘላለማዊ ሕይወት አይገኝም። ጌታ እንዳስተማረው «ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም» ዮሐ.3፥5። ስለዚህ ሕፃናት በወላጆቻቸው እምነት የተነሣ የወላጆቻቸውን እምነት የእነርሱ እምነት በማድረግ ገና በሕፃንነት ጊዜያቸው ከእግዚአብሔር መንግሥት ውጭ እንዳይሆኑ ታጠምቃቸዋለች። ዳሩ ግን ሳይጠመቁ ቢሞቱ ጌታ እንደተናገረው መንግሥተ ሰማይን አያዩአትም። እንደ ጌታ ትምህርት የምንሄድ ከሆነ «ሰው» ብሎ ባጠቃላይ ሕፃናትን አዋቂዎችን ሁሉ ጨምሮ ተናገረ እንጂ «ከሕፃናት በስተቀር» አላለም። «ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም።»

ለ. ሕፃናት በመጠመቃቸው የቤተ ክርስቲያን አባል ስለሚሆኑ የእግዚአብሔር ጸጋ ተከፋዮች ይሆናሉ፤ ገና ከሕፃንነታቸው ጀምሮ የቤተ ክርስቲያንን ሕይወት ይለማመዳሉ። በዚህ ፈንታ ከሕፃንነታቸው ጊዜ ጀምረው ከእግዚአብሔር ጸጋ ተራቁተው የሚያድጉ ከሆነ ለመጥፎ ሕይወት ይዳረጋሉ።

ሐ. እንዲሁም ጌታችን «ያመነ የተጠመቀ ይድናል» ሲል በዚያን ዘመን ገና ወንጌል መስበክ በጀመረበት ላሉት ሰዎች የተነገረ ሲሆን ከክህደታቸውና ከጥርጥራቸው ተመልሰው የሚመጡ ሁሉ አምነው መጠመቅ እንዳለባቸው የሚያስገነዝብ ነው። ሕፃናት የእግዚአብሔር ልጆች ሊሆኑ እንደሚገባ ጌታችን ሲገልጽ «ሕፃናት ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተውአቸው አትከልክሏቸው መንግሥተ ሰማያት እንደ እነርሱ ላሉት ናትና» ብሏል። ማቴ.19፥14። በዚህ የጌታ ትምህርት መሠረት ቤተክርስቲያንም የመሪዋንና የመሥራችዋን የክርስቶስን ቃል መርሕ በማድረግ ወላጆች ልጆቻቸውን ታቅፈው ወደ ቤተክርስቲያን ይዘው በመምጣት ተጠምቀው የእግዚአብሔር ልጆች የቤተክርስቲያን አባላት እንዲሆኑ ሲያደርጉ እርሷ ከልካይ አትሆንም። ጌታ ተውአቸው ይምጡ ልጅነትን፣ ጸጋን፣ በረከትን ያግኙ ብሏልና።

ሕፃናት ንጹሐን አእምሮ መሆናቸውን ጌታ ሲያስተምር «እንደ ሕፃናት ካልሆናችሁ መንግሥተ ሰማይ አትገቡም ብሏል።

መ. መጽሐፍ ቅዱስ ሕፃናት መጠመቃቸውን ያስተምረናል፤ የሚከተሉት ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ ናቸው።

1. በእሥር ቤቱ በተደረገው ተአምር የተደነቀውና ወደ ክርስትና እምነት የተሳበው የወኅኒ ጠባቂ ጳውሎስና ሲላስ ካስተማሩትና ካሳመኑት በኋላ ከነቤተሰቡ መጠመቁ ተገልጾአል። እንግዲህ የተሰበከውና ያመነው የውኅኒ ጠባቂው ሲሆን የተጠመቁት ግን ሕፃናትን ጨምሮ መላው ቤተሰቡ ነው። የሐዋ.16፥33።

2. ልብዋን ጌታ የከፈተላትና ቃሉን አድምጣ ሕይወትዋን ለክርስቶስ የሰጠችው ልድያ ባመነች ጊዜ ብቻዋን ሳይሆን ከመላው ቤተሰብዋ ጋር ነው:- የተጠመቀችው ከቤተሰቡ መካከል ሕፃናት መኖራቸው የማይቀር ነው። የሐዋ. 16፥15።

3. ቅዱስ ጳውሎስ «የእስጢፋኖስንም ቤተሰቦች ደግሞ አጥምቄአለሁ» በማለት የእስጢፋኖስን መላ ቤተሰብ ማጥመቁን ገልጾአል። 1ቆሮ.1፥16። እነዚህ የእስጢፋኖስ ቤተሰቦች ሁሉ ትላልቆች ብቻ ናቸውን? ሕፃናት የሉበትም ይሆን?

4. በሐዋ.ሥራ 2 ላይ እንደተገለጸው በበዓለ ሃምሳ ከ3000 ያላነሱ ሰዎች በጴጥሮስ ተሰበኩ። ከእነዚያ ውስጥ ብዙዎቹ መጠመቃቸው ተገልጾአል። የተጠመቁት ግን ዐዋቂዎች ብቻ መሆናቸውን የሚገልጽ የለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሕፃናትን ጥምቀት የሚነቅፍ ባንዱም ክፍል ተጽፎ አናገኝም።

እስከ አሁን እንደተገለጸው መጽሐፍ ቅዱስ የሕፃናትን ጥምቀት ያልነቀፈ ሲሆን በብሉይ ኪዳን የጥምቀት ምሳሌ የነበሩትን ስንመለከት ይበልጥ የሕፃናትን ጥምቀት ትክክለኛነት ያረጋግጥልናል።

ግዝረት የጥምቀት ምሳሌ ነው። ሕፃናት በተወለዱ በስምንተኛው ቀን ይገረዙ ነበር። ዘፍ.17፥12። እንግዲህ ሕፃናቱ የሚገረዙት በወላጆቻቸው እምነት እንጂ እነርሱ ዐውቀው ግረዙን ብለው አይደለም።

የእሥራኤል ቀይ ባሕርን ማቋረጥ የጥምቀት ምሳሌ መሆኑ በ1ቆሮ.10፥2። የተገለጸ ሲሆን ባሕሩን ያቋረጡት ዐዋቂዎች ብቻ ሳይሆኑ ሕፃናትም ጭምር ናቸው። ከባርነት ከፈርዖን አገዛዝ ነፃ የወጡት ሕፃናቱ ጭምር ናቸው።

እሥራኤል ከበኩረ ሞት የዳኑበት የአንድ ዓመት ጠቦት በግ ደም ምሳሌነቱ የጌታ መሆኑ የታወቀ ሲሆን በዚያን ጊዜ በበጉ ደም አማካኝነት ከሞት የዳኑት የታዘዙትን እሺ በጄ ብለው የፈጸሙት ዐዋቂዎች ብቻ ሳይሆኑ የእነርሱ ልጆችም ጭምር ናቸው። «እንግዲህ በወላጆቻቸው እምነት ሕፃናቱ መዳናቸውን ልናስተውል ይገባናል።

ስለዚህ ሕፃናት በአእምሮ ባልበሰሉበትና ስለጥምቀታቸው አምነው ተቀብየዋለሁ ሳይሉ የሚደረገው ጥምቀት እውነተኛ ጥምቀት አይደለም የሚሉ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ከላይ እንደተገለጸው ሁሉ መሳሳታቸው የተረጋገጠ ነው።

እግዚአብሔር ሰውን ይመርጣል እንጂ ሰው እግዚአብሔርን አይመርጥም፤ እራሱ ባለቤቱ እንዳስተማረው ሁሉ «እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም» ብሏል። ዮሐ. 15፥16። ድኅነት በእግዚአብሔር ቸርነት የሚገኝ እንጂ በሰው ትምህርትና ዕውቀት የሚሸመት ወይም የሚገበይ ዕቃ አይደለም። ስለ ሆነም ቤተ ክርስቲያናችን ሕፃናትን ማጥመቅዋ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከቀደሙት አበው ባገኘችው ትምህርት መሠረት ነው።

ይቀጥላል



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ቤተ ክርስቲያን

**ከስላሜጊት**

ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል በዘይቤ ሦስት ዓይነት አወጣጥ አለው። ይኸውም:-

## 1. ማኅበረ ክርስቲያን:

ከአባታችን ከያዕቆብ የተወለደ ሁሉ እግዚአብሔር ለእርሱ በሰጠው ስም (እሥራኤል) ቤተ እሥራኤል እየተባለ ይጠራ ነበር። በምሥጢራዊ ልደት ከውኃና ከመንፈስ በተጠመቁበት ቀን ከእግዚአብሔር በጸጋ (ከሥላሴ) የተወለዱ ክርስቲያኖችም ቤተ ክርስቲያን ተብለው ይጠራሉ። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም በቀዳማዊት መልእክቱ «በባቢሎን ያለች ቤተክርስቲያን ልጄም ማርቆስ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል» 5:13። ብሏል። ይኸም በባቢሎን ያሉ ክርስቲያኖችን ማለቱ ነው። እንዲሁም ዛሬ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን፣ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ስንል በዚሁ ትርጓሜ መሠረት ነው።

## 2. የክርስቲያኖች ሰውነት:

የክርስቲያኖች ሰውነት በመንፈስ ቅዱስ የተቀደሰ በሥጋወደሙ የታተመ የክርስቶስ ቤት ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም» 1ቆሮ.6፥19–20። በማለት ያስተማረው ለዚህ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ ትምህርቱ ሁለት ነጥቦች አንሥቷል:-

### ሀ. የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ:

የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም ለበዓለ ሃምሳ ከተሰበሰቡ አይሁድ መካከል በ3000 ማኅበረ ምእመናን በቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት ስትመሠረት በዚያን ዕለት መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ ለቅዱሳን ሐዋርያት፣ በኋላም ደግሞ ለ3000ው ማኅበረ ምእመናን ተሰጥቶ ነበር። ለዚህ ነው ዮሐንስ አፈወርቅ ያችን ዕለት «የቤተክርስቲያን የልደት ቀን» ያላት።

ክርስቲያኖችም በአርባና በሰማንያ ቀናቸው ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ ይወለዳሉ። ቤተ ክርስቲያን በቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት ስትመሠረት የወረደውን መንፈስ ቅዱስ በቅብዐተ ሜሮን ያገኙታል «እናንተም ከቅዱሱ ቅባት ተቀብላችኋል» እንዳለ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ። 1ዮሐ.2፥20። ስለዚህም የክርስትያኖች ሰውነት ቤተ ክርስቲያን ይባላል።

መድኃኒተ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ዳግም ምፅዓቱ ባስተማረበት አንቀጽ ስለ አምስቱ ትጉኅን ቆነጃጅት ሲናገር እያንዳንዳቸው መብራታቸውን ይዘው እንደተገኙ በቤተ ክርስቲያን ውስጥም የእያንዳንዱ ክርስቲያን የምግባር፣ የሃይማኖትና የትሩፋት ቀንዲል አስፈላጊ ነው።

### ለ. በዋጋ ተገዝታችኋል

መድኃኒተ ዓለም ክርስቶስ እኛን የገዛበት ሊተመን የማይችል ዋጋ ያለው ቅዱስ ደሙ ነው። ቅድስት ቤተክርስቲያን መድኃኒተ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ የዋጃት ናት። የሐዋ.20፥28። ክርስቲያኖችም በክቡር ደሙ የዋጀን፥ ሥጋውን ደሙን ያደለን የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ነን። ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ እንደሆነች ሁሉ ክርስቲያኖችም እንዲሁ ናቸው። በዚህ የተነሣ የክርስቲያኖች ሕይወትም ቤተክርስቲያን ተብሏል።

ቅድስት ቤተክርስቲያን ምእመናኗ በቅዳሴ፣ በምህላ፣ በማኅሌት፣ በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ወዘተ... እንዲካፈሉ የምታደርገው ቤተክርስቲያን ማለት የእያንዳንዱ ምእመን የሕይወት መቅረዝ የሃይማኖትና የምግባር ብርሃን ውሕደት በመሆንዋ ነው።

## 3. ሕንፃ ቤተክርስቲያን

እግዚአብሔር አምላክ ሰውን በምድር ላይ ከፈጠረው በኋላ የተለየ ቦታ የሰጠበት ምክንያት ነበረው። ይኸውም ሰውና እግዚአብሔር የሚገናኙባትን መቅደስ ለመወሰን ነው። ገነት የአዳም መኖሪያ ብቻ ሳትሆን መቅደሱም ነበረች። በየጊዜው አዳምና ሔዋን ለጸሎት ይወጡባት ነበርና። እግዚአብሔር አምላክም ለጸሎት በተወሰነላቸው ሰዓት እየመጣ ያነጋግራቸዋል።

በቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት ያች ገነት ሦስት በር ነበራት። ምሥራቅ የእግዚአብሔር መምጫ፣ ሰሜን የአዳም መግቢያ፣ ደቡብ የሔዋን መግቢያ ናቸው። ዲያብሎስ በዕባብ ተመስሎ ሔዋንን ያገኛት ለጸሎት ወደ በአቷ በሄደችበት ጊዜ ነው። የተታለለችውም ጸሎት ማድረስዋን ትታ በዚያች የጸሎት ሰዓት ከዕባብ ጋር የማይረባ ወሬ በመጀመርዋ ነበር። ዛሬ በቅድስት ቤተክርስቲያናችን ያሉት በሮች የዚህን ምሳሌ የያዙ ናቸው።

አዳምና ሔዋን ከገነት ከተባረሩ በኋላ ሰውና እግዚአብሔር የሚገናኙባት መቅደስ ገነት በመቅረትዋ አባቶቻችን በተራራ ላይ መሥዋዕት በመሠዋት ከእግዚአብሔር ጋር ይገናኙ ነበር። ከአዳም እስከ ሙሴ በነበረው የሕገ ልቡና ዘመን አበው ቀደምት ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘትና መሥዋዕታቸውንም ለማቅረብ ወደ ተራራ ይወጡ ነበር። አባታችን አብርሃም ይስሐቅን ለመሠዋት ወደ ሞሪያ ተራራ የወጣው በዚህ ምክንያት ነው።

በዘመነ ኦሪት ደግሞ አስቀድሞ ለሙሴ በሰጠው በደብተራ ኦሪት በኋላም በሰሎሞን ቤተ መቅደስ



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

እሥራኤል እግዚአብሔርን ለመገና ኘት ይወጡ ነበር። በዘመነ መሳፍንት ለ400 ዓመታት ደብተራ ኦሪት በሴሎ ስትቀመጥ በዚያ ዘመን በየርስታቸው የነበሩ እሥራኤል በየዓመቱ መሥዋዕታቸውን ይዘው ወደ ሴሎ ይወጡ ነበር። የሳሙኤል እናት ሐና ከባልዋ ከሕልቃና ጋር ወደ ሴሎ የወጣችውም ለዚህ ነው። 1ሳሙ.1፥24።

1000 ዓመት ከጌታችን ልደት በፊት በጠቢቡ ሰሎሞን ቤተ መቅደስ ሲሠራ መሥዋዕት ለመሠዋትና ከእግዚአብሔር ጋር በተለየ ሁኔታ ለመገናኘት በየዓመቱ በተለይም ከበዓለ ፋሲካ እስከ በዓለ ሃምሳ (ለሃምሳ ቀናት ያህል) አይሁድ በኢየሩሳሌም ከየሃገራቸው ይሰባሰቡ ነበር። መንፈስ ቅዱስ በወረደባት ዕለት በሐዋርያው በቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት 3000 ምእመናን ያመኑትም ለዚሁ በዓል ተሰብስበው በነበሩበት ወቅት ነው።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦች ሁሉ የሚያስረዱን ነገር ቢኖር እግ ዚአብሔር ከልጆቹ ጋር የሚገናኝበት የመረጠው፣ የቀደሰው ቦታ መኖሩን ነው። ይህም የእግዚአብሔርን ምሉዕነት የሚገድበው አይደለም። እግዚአብሔር ለጠቢቡ ሰሎሞን በተገለጠለት ጊዜ ስለ ቤተ መቅደሱ ‹በዚህ ሥፍራ ለሚጸለይ ጸሎት ዓይኖቼ ይገለጣሉ ጆሮቼም ያደም ጣሉ። አሁንም ስሜ ለዘላለም በዚያ ይኖር ዘንድ ይህን ቤት መርጫለሁ። ቀድሻለሁም። ዓይኖቼና ልቤም ዘወ ትር በዚያ ይሆናሉ› 2 ዜና.7፥15–16። በማለት የተናገረው እግዚአብ ሔር የመረጠው ቦታ (ቤተ መቅደስ) እንዳለው ያሳየናል።

ነቢየ ልዑል ኢሳይያስም «እግዚ አብሔርን በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት» ኢሳ.6፡1። በማለት የገለጠው እግዚአብሔር ለወደዳቸው የሚገለጥበት የራሱ ቦታ እንዳለው ያመለክተናል። ይህም በሕዝቅኤል 1:1–28፣ ራእይ 4። ላይ ተደጋግሞ ተገልጿል።

በዘመነ ኦሪት የእግዚአብሔር ቤት በሚፈርስበት ጊዜ እርሱ እራሱ ከተማረኩበት ሀገር አውጥቶ ቤቱን ይሠሩለት ዘንድ ወደ ቅድስት ሀገር ያመጣቸው ነበር። በነህምያና ዕዝራ መጽሐፍ የምናነበውም ይኸንኑ ነው። እሥራኤል ጠግበው ተዘናግተው ሲቀ መጡም በነቢያት አድሮ ወደ ተራ ራው ውጡ እንጨትንም አምጡ፣ ቤቱንም ሥሩ፣ እኔም በርሱ ደስ ይለኛል፣ እኔም እመሰገናለሁ» እያለ ይናገራቸው ነበር። ሐጌ. 1:8–9።

አስቀድሞም ሕዝበ እሥራኤልን ከግብፅ ባርነት ሲያወጣ ፈርዖንን «ያገለግሉኝ ዘንድ ሕዝቤን ልቀቅ» ነበር ያለው። ይህም የሚገባውን መሥዋዕት ይሠውለት ዘንድ ነው። ፈርዖንም ሙሴን በግብፅ ይሠዋ ዘንድ ሲነግረው ዘጸ.8፥25 «እኛስ ለእግ ዚአብሔር ለአምላካችን እንሠዋ ዘንድ እንደሚያዝዘን የሦስት ቀን መንገድ ወደ ምድረ በዳ እንሄዳለን» አለው እንጂ አልተቀበለውም። ዘጸ.8፥27። ይኸም እግዚአብሔር በግብፅ ሀገር ስለሌለ ሳይሆን በዚያ በግብፃውያን ባርነት በፈርዖን ቅኝ ግዛት፣ በኃጢ አት ርኩሰት ባሉበት ሀገር ለእግዚአ ብሔር ቅዱስ መሥዋዕት ማቅረብ ስለማይገባ ነው። ስለዚህም አስቀድሞ ወደ መረጣት ሀገር መሄድን ፈለጉ።

በዘመነ ሐዲስ ኪዳን በጌታችን መዋዕለ ትምህርት የኢየሩሳሌሙን ቤተ መቅደስ ለሌላ ተግባር ባዋሉት ጊዜ መድኃኒታችን «ቤቱ የጸሎት ቤት ትባላለች» ማቴ.21፥13። በማለት በጅራፍ እየገረፈ ሻጮችንና ለዋጮችን ማስወጣቱ እግዚአብሔር ለመረጣት ቤቱ ቀናተኛ መሆኑንና የቀደመ ቃል ኪዳኑን ማጽናቱንም ያሳየናል።

ይህ ሁሉ እግዚአብሔር ለክብሩ መገለጫ ቦታን እንደሚመርጥ እንደ ሚገባርክም ያስረዳል። ቅዱሳን ሐዋርያት ጌታችን በሚያርግበት ጊዜ «በኢየሩሳሌም ቆዩ» ሉቃ.24፥49 ነበር የተባሉት። ምክንያቱም:-

- ኢየሩሳሌም የእግዚአብሔር ወዳጆች የዳዊት የሰሎሞን ሀገር ናት፣
- ኢየሩሳሌም የተቀደሰ መሥ ዋዕት የሚቀርብባት ቤተ መቅደስ ያለችባት ቦታ ናት፣
- ኢየሩሳሌም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋውና ደሙን የቆረሰባት፣ ክብርት ትንሣኤውን የገለጠባት ያረገ ባት መካነ ድኅነት ናት፣

ሐዋርያት በየሀገረ ስብከታቸው ቢሄዱ መንፈስ ቅዱስ ጠፍተውት የሚመለስ ሆኖ አልነበረም በኢየሩ ሳሌም ቆዩ የተባሉት። ነገር ግን የተቀ ደሰን ነገር በተቀደሰ ቦታ ማግኘት፣ ማድረግ ስለሚገባ እንጂ።

ቅዱሳን ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉም በኋላ ዘወትር ለጸሎት ወደ ቤተ መቅደስ ይሄዱ ነበር። «እነርሱም ሰገዱለትና በብዙ ደስታ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ። ዘወትርም እግዚአብሔርን እያመሰ ገኑና እየተባረኩ በመቅደስ ኖሩ።» ሉቃ.24:53። ጴጥሮስና ዮሐንስም በጸሎት ጊዜ በዘጠኝ ሰዓት ወደ መቅደስ ይወጡ ነበር። የሐዋ.3:1።

ሐዋርያት ዓለምን ዕጣ በዕጣ ተካፍለው ሲወጡም በየሄዱበት ሀገረ ስብከት ቤተ ክርስቲያንን እየመሠ ረቱ፣ ሥጋወደሙን እየፈተቱና ምእ መናንን እያስተማሩ የምሥጢራት መዝገብ በሆነችው ቤተ ክርስቲያን እንዲኖሩ ያደርጉ ነበር።

እንግዲህ ቤተክርስቲያን በክርስ ቲያኖች ቤትነትዋ የተባረከች የተቀ ደሰች ቦታ ናትና እናከብራታለን፣ እንሰግድላታለን፣ እንሳለማታማለን። ቤተክርስቲያን እግዚአብሔር የባረ ካት ጸጋ መንፈስ ቅዱስ የሚገኝባት፣ ሥጋወደሙ የሚፈተትባት በመሆንዋ ከሌሎች ቤቶች ሁሉ የከበረች የተመረጠች የተቀደሰችም ናት።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## ብሉያዊት ወሐዲሳዊት

የቤተክርስቲያን ጉዞ፣ የቤተክርስቲያን ታሪክ ስንል ከጌታችን ልደት በኋላ ያለውን የክርስትና ጉዞ ብቻ ማለታችን አይደለም። ቤተክርስቲያን አስቀድሞ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች መዳኛ ያዘጋጃት መንገድ ናትና የቤተክርስቲያናችን ሊቃውንት ቤተክርስቲያን የሚለውን ቃል ሲያመሠጥሩት «እግዚአብሔር ከግዕዛን ፍጥረታት ጋር ያለው ግንኙነት ነው» ይላሉ። ግዕዛን ያላቸው ፍጥረታት የሚባሉትም ሰውና መላእክት ናቸው።

ቅዱሳን መላእክት በፍጥረት ዕድሜ ከሰው ይቀድማሉና የመጀመርያዋን ማኅበረ ምእመናን አስገኝተዋል። እግዚአብሔር በመካከላቸው ያድራል፣ መሥዋዕት ያቀርባሉ፣ ማኅሌት ይቆማሉ፣ ዘወትር በፊቱ ያገለግላሉ። ቅዳሴ መላእክት ያደርሳሉ። ይህ በመላእክት ዓለም የተመሠረተው አንድነት የመጀመርያው የቤተክርስቲያን ዕድሜ ይባላል።

ጠላት ዲያብሎስ መናፍቅ ሆኖ ይህን አንድነት ሊበጠብጥ የተነሣውና ቅዱስ ገብርኤልም አፈ ጉባዔ ሆኖ ተከራክሮ የረታው በዚህ ጊዜ ነው። በምሥጢራዊው የቤተክርስቲያን ታሪክ የመጀመሪያው መናፍቅ ሳጥናኤል ነው። እርሱም እግዚአብሔርን የመካድ ራስንም የማምለክና የኑፋቄ ትምህርት ያመጣ ቀንደኛው የቤተክርስቲያን ፀር ነው። በዚህ የክህደት ትምህርቱ በጉባዔ መላእክት ተወግዞ ከክብሩ ተሻረ ከመንበሩ ተባረረ። የእርሱን እምነት የእርሱን የክህደት መንገድ የተከተሉ ጋሻ ጃግሬዎቹም አብረውት ተወግዘው ተሻሩ።

ሁለተኛው የቤተክርስቲያን ዕድሜ ደግሞ ከአቤል እስከ ጌታችን መወለድ የነበሩ የደጋግ አበው አንድነት ነው። በዚህ ዘመንም አስቀድሞ ቃየል በኋላም ልጆቹ ይኽንን የቅዱሳን አበው አንድነት በእኩይ ምግባራቸው ሊበክሉ ተነሥተው ነበር። ነገር ግን በጥፋት ውኃ ዘመን ከምድር ገጽ ጠፉ። በኋላም የባቢሎን ሰዎች ግንብ እንሥራ ብለው የቀደመውን ጠላት የዲያብሎስን የትዕቢት መንገድ የክህደት ትምህርት ተከትለው አምላካቸውን ሊገዳደሩ ተነሥተው ነበር። ነገር ግን ቋንቋቸው ተደበላልቆ ማኅበረ እኩያኑ ተበተኑ።

በዘመነ አብርሃም ደግሞ ይህ አንድነት በግዝረት ቃል ኪዳን ጸና። ዘፍ.17፥9–14። በይስሐቅና በያዕቆብ በኩል ተሻግሮ፣ በዘመነ ኦሪት በሙሴና በኢያሱ በኩል አልፎ በዳዊትና በሰሎሞን በኋላም በነቢያትና በደቂቀ ነቢያት እስከ ዘመነ ሥጋዌ ደርሷል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለዕብራውያን በላከው መልእክቱ እንደገለጠው ይህችን ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ያገኘናትን መንግሥቱን የመውረስ ተስፋ፣ አስቀድሞም ለአዳም የተሰጠውን እኛም ዛሬ በቅድስት ቤተክርስቲያን የምናገኘውን የሥላሴ ልጅ የመሆንን ጸጋ አላገኙምና ከሩቅ ሆነው አዩዋት ተሳለሙዋት። ዕብራ.11፥13። አማናዊቷን እስኪያገኙ ድረስ ምሳሌውን እያደረጉ አለፉ።

- እነርሱ የበግን መሥዋዕት ሰው እኛ ግን የሐዲስ ኪዳን በግዕ፣ ሕያው የእግዚአብሔር በግዕ የሆነ የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስ ቶስን ሥጋና ደም እንሠዋለን።
- እነርሱ አስቀድሠው በተራራ በኋላም በደብተራ ኦሪትና በሰሎሞን ቤተ መቅደስ ሠው። እኛ ግን በገዛ ደሙ በዋጃት የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን እንሠዋለን።
- እነርሱም ሥጋን እንጂ ነፍስን በማታተርፍ በኖኅ መርከብ ከጥፋት ውኃ ዳኑ። እኛ ግን ነፍስንም ሥጋንም ከገሃነመ እሳት በምታተርፍ በቅድስት ቤተክርስቲያን ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ እንድናለን።
- እነርሱ የምድረ ፋይድ የሲኦል ምሳሌ ከሆነች ከግብፅ በሙሴ መሪነት ወጡ፤ እኛ ግን ከገሃነመ እሳት በመድኃኒታችን ደም ተዋጅተን ወጣን።
- እነርሱ ምድራዊቷን ከነዓን ወረሱ። እኛ ግን የማታልፈውን ከነዓን ቤተክርስቲያንን (መንግሥተ ሰማያትን) ወረስን።
- እነርሱ የኤርትራን ባሕር ተሻገሩ። በባሕርም መካከል ተጠመቁ። እኛ ግን ምልዓተ ሐጢያትን ተሳገርን፣ ልጅነትን በሚያሰጥ በውኃና በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቅን።
- እነርሱ ከሞተ ነፍስ የማያድን መና በሉ። እኛ ግን ሞተ ነፍስን የሚያሸንፍ ሥጋውንና ደሙን በላን።
- እነርሱ እሥራኤል ዘሥጋ ተባሉ። እኛ ግን እሥራኤል ዘነፍስ ሆንን።
- እነርሱ ከሚጠፋ ዘር የሆነውን ክህነት ተቀበሉ። እኛ ግን ከማይጠፋ ዘር የሆነውን ሰማያዊ ሥልጣነ ክህነት አገኘን።
- እነርሱ ምድራዊት ከሆነች ደብረ ሲና ሕግን አገኙ። እኛ ግን በግብር ሰማያዊት ከሆነች ከእመ ቤታችን ሐጋጌ ሕግ ኢየሱስ ክርስቶስን አገኘን።

ሦስተኛው የቤተክርስቲያን ዕድሜ ደግሞ ከጌታችን ልደት በኋላ ያለው ነው። በቀደሙት ዘመናት ምሳሌዎች የሆኑት ሁሉ አማናውያን ሆኑ። የተተነበዩት ደረሱ፣ የተሠወሩት ተገለጡ የተመሠጠሩት ተተረጐሙ። ሦስተኛው የቤተክርስቲያን ዕድሜ የቀደምቱ ትንቢት ፍፃሜ፣ የምሳሌው ትርጓሜ፣ የምሥጢሩ ፍች እንጂ እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውኃ ፈሳሽ አይደለም።

መድኃኒተ ዓለም፣ ብርሃነ መለኮቱን በደብረ ታቦር ሲገልጥ፤ ከዐረፉት የብሉይ አበው ሙሴን፣ በብሔረ ሕያዋን ካሉት ኤልያስን፣ ከሐዲስ ኪዳን ጴጥሮስ፣ ዮሐንስ እና ያዕቆብን ያሰባሰባቸው ለዚህ ነው። ማቴ.17፥3። እነዚያ የትንቢታቸውን መድረስ የምሳሌውን መፈጸም ሊያዩ እነዚህ የተነበዩትንና የመሰሉትን ከነትርጓሜው ሊረዱ ተገኙ።

ቤተክርስቲያን ሥራዋ በብሉይ ኪዳን ፍሬዋ በሐዲስ ኪዳን የሆነች ሕያዊት ዛፍ ናት። የቀደሙትን አበው ምሳሌና ትንቢት ተርጉማ አመሥጥራ ትይዛለች እንጂ አትንቀውም። አትተወውም። እንደ አይሁድም ሐዲስ ኪዳንን ትታ በኦሪት ብቻ አትመራም። ከቀደመው ምሳሌና ትንቢት ተነሥታ የሐዲሱን ትርጓሜና ምሥጢር ትመራበታለች። ከሐዲሱ አማናዊ የክርስቲያኖች ኑሮ፣ የቤተክርስቲያን ጉዞ፣ የድኅነት መንገድ ተነሥታ ብሉይን ትተረጉማለች። ታስተምራለች። ለእኛ ብሉይ ምሳሌ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ሐዲስ ትርጓሜ፣ ብሉይ ትንቢት ሐዲስ ፍፃሜ፣ ብሉይ ምሥጢር ሐዲስ ፍቺ ነው።

ቤተክርስቲያን ለዚህ ዓለም እንግዳ የሆኑ ወደ አባታቸው ርስት የሚጓዙ ክርስቲያኖች ማደርያ ናትና ሁለቱን ዲናር ብሉይና ሐዲስን ከጌታዋ እንደተቀበለች ትጠቀምባቸ ዋለች። ሉቃ 10፥35።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን›። ኤፌ.1፥4–5 ያለውም ለዚህ ነው። ቅድስት ቤተክርስቲያን እግዚአብሔር አስቀድሞ መርጦ ያዘጋጃት በምሳሌ ለቀደሙ አበው የሰጣት ለኛም አማናዊ አድርጐ የገለጣት ናት። ቤተክርስቲያን ቅዱሳንን የምታከብረው ከቀደምት ደጋግ አበው ከነቢያትና ከደቂቀ ነቢያት ጀምራ ነው። ምክንያቱም እነዚህ ሁሉ የአንዲት ቤተክርስቲያን ልጆች ናቸውና። በሐዲስ ኪዳን የነበረው አልዓዛር በብሉይ አባት አብርሃም እቅፍ ውስጥ እንደተቀመጠ ሐዲስ ኪዳን በብሉይ ኪዳን ውስጥ ነበረ። ሉቃ.16፥19 መድኃኒታችን ሲመጣም ገለጠው የተገለጠው መሠረቱ ያልተገለጠው ነው።

## ቤተክርስቲያን ቅድስት ናት

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ቀሳውስት «በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን» የሐዋ. 20፥28። በማለት እንደተናገረው ቤተክርስቲያን በቅዱስ የእግዚአብሔር ደም የተዋጀች ቅድስት ናት።

እርስዋ ቅድስት ናትና በውስጥዋ ያሉትን ሁሉ ትቀድሳቸዋለች። አስቀድሞ አባታችን ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ ራእዩን ባየ ጊዜ «በእውነት እግዚአብሔር በዚህ ሥፍራ ነው። እኔ አላውቅም ነበር አለ። ፈራ እንዲህም አለ ይህ ሥፍራ እንዴት ያስፈራ፤ ይህ ሥፍራ የእግዚአብሔር ቤት ነው እንጂ ሌላ አይደለም፤ ይህም የሰማይ ደጅ ነው» ካለ በኋላ በማለዳ ተነሥቶ ተንተርሶት የነበረውን ድንጋይ በማንሣት ሐውልት አድርጐ አቆመው። በላዩም ዘይትን አፈሰሰበት። ያዕቆብም ያንን ሥፍራ ቤቴል ብሎ ጠራው። ዘፍ.28፥16–28።

ዛሬ በቤተክርስቲያናችን ሥርዓት እግዚአብሔር በመረጠው ሥፍራ ሕንፃ ቤተክርስቲያኑ ከመሠራቱ በፊት በኤጲስ ቆጶስ ተባርኮ የመሠረቱ ድንጋይ በቅብዓተ ሜሮን ከብሮ ይቆማል። በዚያም ላይ ቤተክርስቲያን ይመሠረታል። ቤቴል ‹የእግዚአብሔር ቤት› ተብሎም ይጠራል። በውስጡ ያሉት ሁሉም ይቀደሳሉ። ቤተ እግዚአብሔር፣ ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ናትና ቅድስት ናት። እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ እንደ አለ። 1ጴጥ.1፥15። ንዋያቷም ‹ንዋያተ ቅድሳት› ይባላሉ። የሚያገለግሉት ለእግዚአብሔር አገልግሎት ለመንፈሳዊ ሥርዓት ብቻ ነው።

የክርስቶስ ሥጋና ደምም በውስጥዋ ይፈተታል። አስቀድሞ በዘመነ ኦሪት መሥዋዕተ ኦሪቱ ከቤተ መቅደስ ውጭ እንዳይሠዋ ዛሬም በአማናዊቷ ቤተክርስቲያን የአማናዊው በግ የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋውና ደሙ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ አይፈተትም።

ቤተክርስቲያን ቅድስት ናትና ልጆቿን ቅዱሳን ታደርጋቸዋለች። በጥምቀት ወልዳ፣ በቅብዐተ ሜሮን አትማ፣ በሥጋወደሙ ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አንድ ታደርጋቸዋለች።

ቤተክርስቲያን ቅድስት ናትና መጻሕፍቷ ቅዱሳት ናቸው። የሚናገሩ፣ የሚያስተምሩት ስለ ቅዱስ እግዚአብሔር፣ ስለ ቅዱሳን ልጆቹ፣ ስለ ቅድስና ኑሮ፣ ስለ ቅድስት ሀገር ስማያዊት ኢየሩሳሌም ነውና።

ቤተክርስቲያን ቅድስት ናትና ጠበልዋ፣ አፈርዋ፣ ግንብዋ የተቀደሰ ነው። አስቀድሞ እግዚአብሔር አምላክ ለሙሴ ስለደብተራ ኦሪት «የቅብዓቱንም ዘይት ወስደህ ማደርያውን በእርሱም ያለውን ሁሉ ትቀባለህ። እርሱንም ዕቃውንም ሁሉ ትቀድሳለህ ቅዱስም ይሆናል» ዘጸ.40፥9 እንዳለው ጸጋ መንፈስ ቅዱስ በሚገኝበት በቅብዐተ ሜሮን ከብሮአልና የቤተክርስቲያን ሀብቷ ሁሉ ቅዱስ ነው።

ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ናትና፣ ሥርዓቷ፣ ባህልዋ፣ ትውፊቷ የተቀደሰ ነው። የተጀመረው፣ የተሠራው፣ የተደነገገው፣ የተሰጠው በቅዱሳን ከተቀደሰው ቤት ከቤተክርስቲያን በመሆኑ ቅዱስ ሆኖ ይቀድሳል፤ ቡሩክ ሆኖ ይባርካል።

ልጆቿም ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ የተወለዱ፣ በቅዱስ ሥጋው በክቡር ደሙ የተዋጁ፣ በተቀደሰው የወንጌል ትምህርት የሡኑ፣ አንድ ጊዜ ፈጽሞ ለቅዱሳን በተሰጠ የተቀደሰ ሃይማኖት ያመኑ፥ የተጉ ስለሆኑ ቅዱሳን ናቸው። ይሁዳ. 3፥20።

ቤተ ክርስቲያን የቅድስና ማዕከል ናት። ያለ ቤተ ክርስቲያን ኑሮ፣ ያለ ቤተ ክርስቲያን እምነት፣ ያለ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት፣ ያለ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ቅድስና አይገኝም።

ይቀጥላል

### ከቅዱሳን ብሂል

- ከመኝታህ በፊት የምታደርገውን ጸሎት ትተህ እንድትተኛ መንፈስህ ሲገፋፋህ እሺ ብለህ አትቀበለው፤ እንዲያውም መዝሙረ ዳዊት ጨምርና ሌሊቱን በሙሉ ስትጸልይ እደር።

  ቅዱስ ይስሐቅ ሶርያዊ

- አንዲት ቀዳዳ አንድን ትልቅ መርከብ ታሰጥመዋለች፣ አንዲት ኃጢአትም አንዱን ትልቅ ሰው ለውርደት ልታበቃው ትችላለች።
- አንድ የሚጾም ሰው ሁሉን ነገር ትቶ የሚወድቀውን ምግብ መተው ካልቻለ ምኑን ጾመ ይባላል።
- ኃጢአትን መደበቅ እራሱ ኃጢአት ነው።

  ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ

- ንስሐ ሥጋዊውን ፍላጎት በመንፈሳዊ ፍላጎት መተካት ነው።
- ቅዱስ ዮሐንስ ሐፂር ሰዎች ኃጢአት ሲሠሩ ባየ ጊዜ «ጠላት ዲያብሎስ ዛሬ ይኽንን ወንድሜን እንደጣለው ነገ ደግሞ እኔን ይጥለኛል። እግዚአብሔርም ይኽንን ወንድሜን ንስሐ ገብቶ ይቅር ሲለው እኔ ግን ንስሐ አልገባ ይሆናል» እያለ ያለቅስ ነበር።



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

# የሚጐድለን ምንድነው?

ዲያቆን ደጀኔ ሽፈራው

ብዙዎች በመንፈሳዊ ሕይወታችን ምን እንደጐደለን አስበን አናውቅም። በፈቃደ ሥጋ ስለምንመራ ለጊዜው የሚታየን ፍትወተ ሥጋችንና የዓይን አምሮታችን አለመሟላቱ ብቻ ነው። ሀብት፣ ቤት፣ ንብረት፣ ትዳር፣ የሥጋ ዘመድ፣ መኪና፣ ሥልጣን ወዘተ ስለሌለን በጠቅላላው በዓለም ያለውን አላፊውን ነገር ሁሉ በማጣታችን ባዶነት የሚሰማን ሰዎች ጥቂቶች አይደለንም። ኑሮአችን ከእጅ ወደ አፍ ከሆነው ጀምሮ በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ እስካላቸው ሰዎች ድረስ ከተራው ሰው እስከ ትልቁ ባለሥልጣን ሁላችንም የምናዳምጠው ሥጋችንን ነው። የሚታየንም በሥጋ የጐደለን ነገር ብቻ ነው። ይህንንም ለማሟላት የማንወጣው ዳገት የማንወርደው ቁልቁለት የለም። የቀን እረፍት የሌሊት እንቅልፍ እናጣለን። በዚህም ምክንያት ማንኛውንም ወንጀል ከመፈጸም ወደ ኋላ አንመለስም። ወደ ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣዖትን ማምለክ፣ ምዋርት፣ ጥል፣ ክርክር፣ ቅንአት፣ ቁጣ፣ አድመኛነት፣ መለያየት፣ መናፍቅነት፣ ምቀኝነት፣ መግደል፣ ስካር፣ እና ዘፋኝነት እናመራለን። ገላ.5፥19። ውጤቱም የዘላለም መከራ ነው። ምክንያቱም «በሥጋው የሚዘራ መበስበስን ያጭዳልና» ገላ.6፥8። እንደ ሥጋ ፈቃድ መኖር ሞት ነውና ሮሜ.8፥ 12። እንደ ሥጋ ፈቃድ በመኖር በሚመጣ ጠንቅ የእግዚአብሔር ቁጣ በማይታዘዙ ልጆች ላይ ይመጣልና ቆላ.3፥5–6።

አንድ ሀብታም ወጣት ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀርቦ ጌታ ሆይ የዘረዘርክልኝን ትእዛዛትማ ከሕፃንነቴ ጀምሬ ጠብቄአለሁ። ደግሞስ የሚጐድለኝ ምንድር ነው ሲል ጠየቀ። ኢየሱስም አንዲት ቀርታኻለች ፍጹም ልትሆን ብትወድ ሂድና ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ። መጥተህም ተከተለኝ አለው። ወጣቱ ባለጸጋ ግን ይህን ቃል በሰማ ጊዜ ብዙ ንብረት ስለነበረው እያዘነ ተመለሰ ማቴ.19፥16–22። ይህ ወጣት በሕይወቱ የጐደለው ነገር እንዲሟላለት ተው የተባለውን ነገር መተው አልቻለም። ከእግዚአብሔር የቁጣ ቀን የማያድነውን ብርና ወርቅ ወዶ በሕይወት ጐዳና መጓዝ አቃተው። ሶፎ. 1፥18።

የራሱን ኑሮ ከወንድሙ ምድራዊ ኑሮ ጋር እያነፃፀረ ባዶነት ይሰማው የነበረ አንድ ሰው በወንድሙ አላፊ ጠፊ ሀብት ቀንቶ መምህር ሆይ ርስቱን ከእኔ ጋር እንዲካፈል ለወንድሜ ንገረው ሲል ኢየሱስ ክርስቶስን ጠየቀ። ኢየሱስም አመጣጡን ያውቅ ስለነበር ለተከተሉት ሁሉ በአንድነት የሰው ሕይወት በገንዘቡ ብዛት አይደለምና ተጠንቀቁ ከመጐምጀትም ተጠበቁ አላቸው። ይህ ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ ብዙ የጐደለው ነገር እያለ የተመለከተው የሥጋውን ነው። ሰማያዊ ክብር ጐድሎት ሳለ የሚያስበው ምድራዊ ክብርን ብቻ ነበር። ሉቃ.12፥13

ንጉሡ ሳኦል ነቢዩ ሳሙኤል እግዚአብሔር ከአማሌቃውያን ምርኮ አትንካ ብሎኻል እያለው ቢተው የሚጐድልበት፣ የተባለውን ትቶ ምርኮውን ቢሰበስብ ደግሞ የሚያተርፍ መሰለው። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ናቀው። 1ኛ ሳሙ. 15፥11። ርኩስ መንፈስ ተቆራኝቶት የሚሰቃይ ሆነ። መንግሥቱንና ክብሩ አጣ አተርፍ ባይ አጉዳይ ይሏል ይኼ ነው።

የአልዓዛር እህት ማርታ የኩሽና ሥራዋን ለጊዜው ትታ ከኢየሱስ እግር ሥር ተቀምጣ እንደ እህፅጎአ እንደ ማርያም መማርን እንደ ጉድለት በመቁጠሯ «ማርታ ማርታ በብዙ ነገር ትጨነቂያለሽ። ትታወኪማለሽ የሚያስፈልገው ጥቂት ወይም አንድ ነገር ነው። ማርያምም መልካምን ዕድል መርጣለች። ከእርስዋም አይወሰድባትም» የተባለችው። ሉቃ.10፥38–45። ወጣቱ ዴማስ መንፈሳዊ አባቱን ቅዱስ ጳውሎስን ትቶ ወደ ዓለም የኮበለለው ዓለምን ማጣት እንደ ጉድለት ስለታየው ነው። 2ኛ ጢሞ.4፥10።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለተከታዮቹ የጐደላቸውን ነገር በየጊዜው ይነግራቸው ነበር። «አንተ እምነት የጐደለህ ስለምን ተጠራጠርህ።» ማቴ.14፥31። «እናንተ እምነት የጐደላችሁ ስለምን ትፈራላችሁ» ማቴ.8፥26። «ስለ እምነታችሁ ማነስ ነው።» ማቴ.17፥10። «እምነት ቢኖራችሁ ባትጠራጠሩም በበለሲቱ እንደሆነባት ብቻ አታደርጉም።» ማቴ.21፥21። እያለ እነርሱም ጉድለታቸውን ዐውቀው ጌታ ሆይ እምነት ጨምርልን ብለውታል።

በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የመረጣቸው አያሌ ሰዎች የጐደላቸውን ነገር እያስተዋሉ ፈጣሪያቸውን ይለምኑ ነበር። ነቢዩ ዳዊት «አቤቱ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ» ሲል ለምኗል። ምክንያቱም ንጹሕ ልብ ከሌለው እግዚአብሔርን ማየት እንደማይችል ስለሚያውቅ ነው። እግዚአብሔርን ማየት የሚችሉ ልበ ንጹሐን ብቻ ናቸውና። ማቴ.5፥8። ጠቢቡ ሰሎሞን እግዚአብሔር ተገልጦለት ልሰጥህ የምትፈልገውን ነገር ለምን ቢለው ታናሽነቱን አምኖ፣ ድካሙን አውቆ፣ የጐደለውን አስተውሎ «እኔ መውጫና መግቢያ የማላውቅ ታናሽ ብላቴና ነኝ።...ስለዚህም በሕዝብህ ላይ መፍረድ ይችል ዘንድ መልካሙንና ክፉውንም ይለይ ዘንድ ለባርያህ አስተዋይ ልቡና ስጠው። አለዚያማ በዚህ በታላቅ ሕዝብህ ላይ ይፈርድ ዘንድ ማን ይችላል።» ብሏል። 1ኛ ነገ.3፥5–9። ሰው ከእግዚአብሔር አስተዋይ ልቡና



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ካልተሰጠው በቀር በዳኝነት ወንበር በተቀመጠ ጊዜ ፍርዱ የሚያዳድል ደሀ የሚበድል የሚኾነው ነው።

ሙሴ እግዚአብሔር ወደ ፈርዖን ሊልከው በጠራው ጊዜ «ወደፈርዖን የምሄድ የእሥራኤልንም ልጆች ከግብፅ የማወጣ እኔ ማን ነኝ» አለ። ሂድ ቃሌን ተናገር በተባለም ጊዜ «ጌታ ሆይ እኔ አፌ ኮልታፋ ምላሴም ጸያፍ የሆነ ሰው ነኝ። ትናንት ከትናንት ወዲያ ባርያህንም ከተናገርኸኝ ጀምሮ አፈ ትብ ሰው አይደለሁም።» በማለቱ የጠራው እግዚአብሔር አፍን የፈጠርኩ እኔ ከአፍህ ጋር እሆናለሁ። አስትምርኻለሁ። አለው ዘጸ.3፥11፣ 4፥ 10። ኤርምያስም ወጣት ሳለ እግዚአብሔር ለአሕዛብ ነቢይ አድርጌኻለሁ። ባለው ጊዜ «ወዮ ጌታ እግዚአብሔር እነሆ ብላቴና ነኝና እናገር ዘንድ አላውቅም» በማለቱ እግዚአብሔር እጁን ዘርግቶ አፉን ዳሰሰ። ቃሉንም በአፉ አኖረለት። ኤር.1፥4–10። ነቢዩ ኢሳይያስም እኔ ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው ነኝ በማለቱ በዕደ ሱራፌል በሰማያዊ እሳት ፍም ተዳስሶ በደሉ ተወገደለት። ከለምፅ ርኩሰት ተቀደሰ። ኢሳ.6፥6።

እኛስ ከየትኛው ወገን ነን አብዛኞቻችን መንፈሳዊ ጉዞ እንጀምርና ዓለምን በመተዋችን የጐደለብን ይመስለናል። እንደ ሎጥ ሚስትም ወደ ኋላ ስንመለከት እዚያው ቆመን እንቀራለን መንፈሳዊው ጉዞአችን ከመቅጽበት ይገታል። መንፈሳዊያን የነበርን ተለውጠን ሥጋዊያን አማኞች የነበርን መናፍቃን እንሆናለን። ዓለምን መመልከት ስንጀምር ለቅዳሴና ለስብከት መትጋታችን ጊዜ እንደማባከን ብዙ ነገርም እንደማጣት እየመሰለን ይመጣል። እንደ ጓደኞቼ ብሯሯጥ ዕድሌን ብሞክር ኖሮ ማለት እንጀምራለን። ወዲያው የጉዞ አቅጣጫችንን ለውጠን በሰፊው ጐዳና መጓዝ እንጀምራለን። ጠማማው ቀና፥ ጨለማው ብርሃን፥ መራራው ጣፋጭ፣ ክህደቱ እምነት፣ ጥፋቱ ልማት፣ ገደሉ ሜዳ መስሎ ይታየናል።

በሌላ መልኩ ደግሞ ነቢዩ ዳዊት በመዝሙሩ በእግዚአብሔር ቤት ለዘላለም እኖር ዘንድ እሻለሁ። እንዳለ ወስነን በእግዚአብሔር ቤት መኖር ስንጀምር በአፍአ ያሉ ሰዎች እንደ ሥራ ፈትነት ቆጥረው ያጐደልንና የጐደለብን መስሏቸው «አንተ ደግሞ ለምን ታበዛዋለህ? በልኩ አታደርገውም እንዴ? ምንድነው ጧት ማታ ወደ ቤተክርስቲያን መሮጥ? ለምን ጾም ታበዛለህ? ለምን ሥራ ፈልገህ አትገባም? ወዘተ...» እያሉ ያዳክሙናል። በዚህን ጊዜ ሌሎች የሚጓዙበት ሰፊ ጐዳና ቅን መስላ ትታየናለች። ለጊዜው ይመስለናል እንጂ «ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች ፍጻሜዋ ግን የሞት መንገድ ነው። » ምሳ.14፥12።

ምንም እንኳን ዕለት ተዕለት ቃሉን ብንሰማም ሁኔታችን ግን ቃሉን እንዳልሰማና ተአምራቱን እንዳላየ ሰው ነው ልቡናችን ደንዳና ነው መስማት እንሰማለን ነገር ግን አናስተውልም። ማየትም እናያለን አንመለከትምም። ጆሮአችን ደንቁሮአል ዓይኖቻችንም ተጨፍኖአል። ኢሳ.6፥9። ማቴ.13፥14። ዓይነ ልቡና እና እዝነ ልቡና ይጐድለናል።

1ኛ. ከሁሉ በላይ እምነት ይጐድለናል ያለ እምነት ደግሞ እግዚአብሔርን ማገልገል አይቻልም። በሕግ በአምልኮት ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሰው አስቅድሞ ሊያምን ይገባል። አንድ ሰው እግዚአብሔር በሕግ በአምልኮት ለሚሹት ሰዎች የሚሰጣቸው እንዳለ ማመን አለበት ዕብ.11፥6፤ ኤር.5፥3፤ ሮሜ.14፥23፤ አሞ 5.4፤ ሚል. መ፥14።

እኛ ግን ተጠራጣሪዎች ወላዋዮች ነን በመሆኑም የምናገኘው ነገር የለም ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ «የሚጠራጠር ሰው በነፋስ የተገፋና የተነቃነቀ የባሕር ማዕበልን ይመስላልና ሁለት አሳብ ላለው በመንገዱም ሁሉ ለሚወላውል ለዚያ ሰው ከጌታ ዘንድ አንዳች እንዲያገኝ አይምሰለው።» ያለው ለዚህ ነው። ያዕ.1 ቁ.

2ኛ በጐ ምግባር ይጐድለናል ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ እንዳለ «ሥራ የሌለው እምነት በራሱ የሞተ ነው።» ያዕ.2፥17። የምንሠራው ለሕይወት ሳይሆን ለሚጠፋ መብል ብቻ ነው ጌታ ያለው «ለሚጠፋ መብል አትሥሩ ነገር ግን ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር መብል የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ሥሩ» ነበር። ዮሐ.6፥25።

3ኛ. ፍቅር ይጐድለናል ፍቅር ከሌለን እግዚአብሔርን አናውቅም ማለት ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር ፍቅር ነውና። 1ኛዮሐ.4፥8። በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብንናገር ትንቢትም ቢኖረን ምሥጢርንም ሁሉና ዕውቀትን ሁሉ ብናውቅ ተራሮችንም ሁሉ እስከናፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረን ድሆችንም ሁሉ ልንመግብ ያለንን ሁሉ ብናካፍል ሥጋችንንም ለእሳት መቃጠል አሳልፈን ብንሰጥ ፍቅር ግን ከሌለን ከንቱ ነን 1ኛ ቆሮ.13፥1–3። ጌታ ግን ያስተማረን «ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚረግሙአችንም መርቁ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ ስለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ...የሚወዱአችሁን ብትወዱ ምን ዋጋ

## ከቅዱሳን ሕይወት

ቅዱስ ኢሲዶር የታወቀ ካህን ነበር። በእጁ ሥርም 3000 መነኮሳት ይተዳደሩ ነበር። የታላቁ አባት የሙሴ ጸሊም የንስሐ አባት ነበር። እግዚአብሔር እምላክ ራእይ የማየትና ድንቅ ተአምራትን የማድረግ ጸጋ ሰጥቶት ነበር። ነገር ግን ዘወትር ከመራራ ለቅሶ አይለይም ነበርና አንዱ ደቀ መዝሙሩ ጠጋ ብሎ «አባቴ ሆይ ለምን ታነባለህ» ብሎ ጠየቀው አባ ኢሲዶርም «የማነባውም በኃጢአቴ የተነሣ ነው አለው፤ ያም ደቀ መዝሙር ተገርሞ» አባቴ ሆይ አንተም እንዲህ የሚያስለቅስ ኃጢአት አለብህን? አለው። እየተገረመ ልጄ ሆይ እግዚአብሔር ይቅር ይለኝ ዘንድ ከኔ ጋር 4 ሰዎች እንኳን ቢያለቅሱ ለእኔ ኃጢአት በቂው አይደለም» አለው። ያም ደቀ መዝሙር ተገርሞ እያለቀሰ ወጣ። እርሱም እንባ ጀመረ።

ጻድቅም በጭንቅ የሚድን ከሆነ ዓመፀኛውና ኃጢአተኛው ወዴት ይታይ ዘንድ አለው። 1ጴጥ.4፥18።



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

አላችሁ። ቀራጮችስ ያንኑ ያደርጉ የለምን? ወንድሞቻችሁንም ብቻ እጅ ብትነሡ ምን ብልጫ ታደርጋላችሁ። አሕዛብስ ያንኑ ያደርጉ የለምን?» የሚል ነው። ማቴ.5፥43–48።

4ኛ. ትሕትና ይጐድለናል:- በጉዞአችን ሁሉ ከእኔ በላይ ማንም የለም እንላለን፤ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ምንም እንኳን ጉልበታሞች ብንሆንም እንሸነፋለን። ሥልጣን ቢኖረንም እንሻራለን። ብንከብርም እንዋረዳለን፤ ብናገኝም እናጣለን፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ ቅዱሳት መጻሕፍትን መርምሬአለሁ። ንባቡን ከነትርጓሜው ጠንቅቄአለሁ። ከእኔ በላይ አዋቂ ለአሳር ነው የምንል ከሆነ ፍጻሜአችን መናፍቅነት ነው። ምክንያቱም ዕውቀታችንን በእምነትና በትህትና ካልያዝነው ይጐዳናል። «እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል። ለትሑታን ግን ጸጋውን ይሰጣልና» ያዕ.4፥6። እርሱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከቤተልሔም እስከ ቀራንዮ ያስተማረንና ሠርቶ ያሳየን ፍጹም ትህትናን ነው። «ከእኔም ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ። ማቴ.10፥29። ያለውን ልንረሳ አይገባም።

5ኛ. ጽናት ይጐድለናል:- ቀድሞውንም ቢሆን በቃሉ ላይ የተመሠረተ ሕይወት ስለሌለን የክህደት ነፋስ ሲነፍስ የክህደት ጐርፍ ሲጐርፍ ልክ በአሸዋ ላይ እንደ ተሠራው ቤት እንወድቃለን። አወዳደቃችንም የከፋ ይሆናል። ማቴ.7፥26። እኛ የተማርነውን ትምህርት የሚቃወም ከመጣ ጽናቱ ስለሌለ ፈጥነን እምነታችንን ሥርዓታችንን እንለውጣለን። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ግን ይህ እንዳይሆን «ነገር ግን ወንድሞች ሆይ እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙትን መለያየትንና ማሰናከያ የሚያደርጉትን ሰዎች እንዳትመለከቱ እለምናችሁአለሁ። ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ። እንዲህ ያሉት ለገዛ ሆዳቸው እንጂ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አይገዙምና በመልካምና በሚያቆላምጥም ንግግር ተንኰል የሌለባቸውን ሰዎች ልብ ያታልላሉ። ሮሜ.16፥17። ዕብ.13፥7 «ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ ለዘላለምም ያለው ነው። ልዩ ልዩ ዓይነት በሆን በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ።» በማለት አስቀድሞ ነግሮናል። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም «በዓመፀኞች ስሕተት ተስባችሁ ከራሳችሁ ጽናት እንዳትወድቁ ተጠንቀቁ» ሲል መክሮናል። 2ኛ.ጴጥ.3፥17። በተለይም ይህ ዘመን የተመረጡት እንኳ ጽናት አጥተው የሚስቱበት ዘመን ነው። ማቴ.24፥24።

6ኛ. ኃጢአትን ሠርተን የመርሳት ጠባይ አለብን። ኃጢአትን እየሠራንም አናስተውልም። ከቁጥር የማይገባ ጽድቃችን እንጂ ከራሳችን ጸጉር የበዛው ኃጢአታችን አይታየንም። ጉዞአችንም ራስን የማጽደቅ ሌላውንም የመኰነን ኑሮ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ሕይወት የጸሐፍት ፈሪሳውያን ነው። በዚህም «እናንተ ዕውሮች መሪዎች ትንኝን የምታጠሩ ግመልንም የምትውጡ ወዮላችሁ...በውጭ ለሰው እንደጻድቃን ትታያላችሁ በውስጣችሁ ግን ግብዝነትና ዓመፀኝነት ሞልቶባችኋል» ተብለው በጌታ ተወቅሰዋል። ማቴ.23፥24፤ 28። ምክንያቱም ኃጢአታቸውን አያስተውሉም ነበር። ነቢዩ ዳዊት ይህን በተመለከተ የተናገረው አለ። «ስሕተትን ማን ያስተውላታል ከተሰወረ ኃጢአት አንጻኝ የድፍረት ኃጢአት እንዳይገዛኝ ባርያህን ጠብቅ የዚያን ጊዜ ፍጹም እሆናለሁ ከታላቁም ኃጢአት እነጻለሁ።» ብሏል መዝ.18፥12።

በጠቅላላው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬያት ተብለው የተዘረዘሩት ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ ደግነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት እነዚህ ሁሉ ይጐድሉናል። ገላ.5፥ 25። ስለዚህ «ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጐድለው ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን ለእርሱም ይሰጠዋል።» ያዕ.1፥5። ምሳ.2፥3። እንደተባለ ለሁሉ አምልቶ አስፍቶ አብዝቶ ከሚሰጥ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንለምን። እርሱም ለሕይወታችን የሚያስፈልገንን ሁሉ ይሰጠናል። በእውነት የሚጐድለንን እንድናውቅ የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን አሜን። ✣

## ሁሉም ለበጎ ነው

አንድ ባላባት አሽከራቸውን አስከትለው መንገድ ሲጓዙ ይደክማቸውና በአንድ ዛፍ ሥር ከበቅሎ ወርደው ያርፋሉ። በዚያው እንዳሉ ሽለብ ያደርጋቸዋል። አሽከራቸውም እርሳቸውን ሲያይ ነው መሰል ፈዘዝ እንዳደረገው በቅሎዋ ደንብራ እግራቸውን ትረግጣቸዋለች። ደንግጠው ሲነሡ እግራቸው ተሰብሮአል።

ባላባቱ በዚህ ተናደው አሽከራቸውን ደብድበው ገደል ይለቁታል። እርሳቸውም እንደምንም በቅሎዋቸው ላይ ወጥተው ጉዞአቸውን ይቀጥላሉ።

በዚያ መንገድ በየዓመቱ ለጠንቋይ ሰው እያረዱ መገበር የለመዱ ሽፍቶች ነበሩ። ያንን ካላደረጉ ዕድላችን ይሰናከላል ብለው ይሠጋሉ። እርሱም ብዙ ጋሻ ጃግሬ ስለነበረው ሰው ባጡበት ዓመት እነርሱኑ ሊያርዳቸው ይደርስ ነበር።

በዚያን ቀን የሚገብሩት ሰው አጥተው ሲጨነቁ እኒያ ባላባት በበቅሎ መጡላቸው። ሽፍቶቹም ደስ ብሎዋቸው ሰውየውን ከነበቅሎዋ ቸው ወደ ጠንቋዩ ቤት ወሰዷ ቸው። ጠንቋዩም ከግቢው ወጥቶ ሲጠራቸው ባላባቱ እያነከሱ ቀረቡ። እርሱም እጅግ ተበሳጨ «እኔን ምን ብትንቁኝ ነው የሚያነክስ ሰው ያመጣችሁልኝ» አለና በሽፍቶቹ ላይ ደነፋባቸው። ባላባ ቱንም በቶሎ ከዚህ ይጥፉ» ብሎ አባረራቸው።

በመንገድም ላይ እንዳሉ የሆነውን ሁሉ ማሰብ ጀመሩ። «በቅሎዋ ባትደነብር እግሬም ባይሠበር አልተርፍም ነበር።» አሉና አሽከራቸው ወደ ወደቀበት ገደል መጡ። በገደሉ ጫፍ ላይም ቆመው «አንተ ልጅ ናውጣ» ብለው የደረሰባቸውንና እግራቸው በመሠበሩ ጠንቋዩም ጤነኛ ሰው በማጣቱ ከሞት እንደተረፉ ነገሩት። እርሱም «አይ ጌቶች እኔንም አልጐዱኝም አብሬ ሄጄ ቢሆን ኖሮ ጤነኛው እኔ በመሆኔ የምሞተው እኔ ነበርኩ ገደል ውስጥ በመግባቴ ግን እግዚአብሔር አተረፈኝ» አላቸው ይባላል።

ችግር ሲያጋጥመን መከራ ሲደርስብን ተስፋ ከመቁረጥ፤ እግዚአብሔርን ከማማረር ይልቅ እግዚአብሔር ያንን ያደረገልን ለምን እንደሆነ መመርመር መልካም ነው። እግዚአብሔር ለልጆቹ የሚያደርግልን ሁሉ መልካም ነውና። «እግዚአብሔርንም ለሚወዱ እንደ ሃሳቡም ለተጠሩ ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።» ሮሜ.8፥28።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ኪነ ጥበብ

## ስደተኞች

ከዳንኤል ክብረት

ዕንባው መንታ መንታ መንታ ይወርዳል። ግን ደግሞ ያለማቋረጥ ይጋልባል። ያ! ብዙ ኮረዶችን ያማለለ፣ ዕፁብ ድንቅ የተባለለት፣ አባቱ ይኮሩበት የነበረ መልኩ ወይቦአል። በተለይማ ፀጉሩ ከመንገድ ላይ አግኝቶ ከነ አቧራው በጭንቅላቱ ላይ የደፋው እንጂ የራሱ አይመስልም። ‹እባክሽ አንቺ በቅሎ ሩጪ፣ እባክሽ ፍጠኚ› አለ ሲቃ እየተናነቀው– በቅሎዋ ትሰማው ይመስል።

ጸጥ ያለ በረሃ፤ ጭው ያለ ሜዳ፤ ዛፍ አይታይበት ሰው ዝር አይልበት። አልፎ አልፎ ብቻ ከመካከለኛውና ከምሥራቃዊው አፍሪካ የተነሡ አዕዋፍ በነጠላና በኅብረት እያዜሙ በረሃውን ሲያቋርጡ ይታያሉ። ከዚያ በተረፈ አሸዋ–አሸዋ–አሸዋ–አታካች በረሃ ነው።

ከዚህ በፊት እንዲህ ያለ የበረሃ መንገድ እንኳንስ ሞክሮት አስቦትም አያውቅ። ምን በወጣው የሲረናይካው ልዑል! ከሊቢያ ምዕራባዊው ክፍል በምትገኘው የአባቱ መናገሻ ከተማ በሠረገላ ይንፈላሰሳል እንጂ! ቢበዛ ለመዝናናት ከመኳንንቱ ጋር አብሮ ከሲረናይካ ከተማ አጠገብ ባለው የፈረስ መጋለቢያ ሥፍራ ይጋልብ እንደሆን እንጂ እንዲህ ያለው ዱብ ዕዳ ደርሶበት አያውቅም።

ልዑል ማርቆስ ያንን አስደንጋጭ መርዶ ከአባቱ ከንጉሥ ሲፕሪዮን አንደበት የሰማው ትናንት ማታ ነበር። በመኝታ ቤቱ ከልዕልት ሄለን ጋር እየተጫወተ ሳለ ወደ አባቱ እልፍኝ ተጠራ። አባቱ በዙፋናቸው ላይ ጉብ ብለዋል። ከማንም ጋር ቢሆን ብርቱ ጉዳይ ሲነጋገሩ በዙፋናቸው ላይ መቀመጥ ይቀናቸዋል።

«እንግዲህ ምን ይሁን» አሉና ኮስተር ብለው ‹ዙፋኔን፣ ክብሬን፣ ጤናዬን፣ ሀብቴን ማጣት አልፈልግም። ልጅ ቢሞት ልጅ ይተካል እኔ ካለፍኩ ግን ማን ይተካልኛል?» አሉና አፈጠጡበት። ልዑል ማርቆስ ግራ ገባው። ንግግራቸው ከወትሮው ይለያል። ጤነኛ ንግግር አለመሆኑ ገባው።

«ለድራጐን ምን እንስጠው?» አሁንም በርሱ ላይ እንዳፈጠጡ ናቸው። ድራጐን የሲረናይካ አምላክ ነው። እጅግ ታላቅ ዘንዶ። ከከተማዋ 5 ምዕራፍ ያህል በስተ ምዕራብ በኩል የሚኖር። የሲረናይካ ሰዎች፣ ድምፁ ዓለምን ያናውጣል ይሉታል። እንዲያውም በዚያ ሰሞን በምሥራቅ ባሉ ከተሞች የምድር መንቅጥቀጥ ሲከሠት የድራጐን ቁጣ ነው ተብሎ 200 ሠንጋ ነበር የተቀለበው።

ድራጐን የተቆጣው ጤናው ይቃወሳል፣ ሀብቱ ይጠፋል፣ ሥልጣኑ ይናጋል፣ ክብሩ ያልፋል እየተባለ ከጥንት ዘመን ጀምሮ በየትውልዱ ስለሚነገር የማይፈራው፣ ስሙን በክብር የማይጠራው፣ የማይገብርለትም አልነበረም። ግብሩ ሁለት ዓይነት ነው። በየጊዜው የሀገሬው ሰው እንደ ዐቅሙ ከዶሮ እስከ ሠንጋ ያርድለታል። በየዓመቱ ደግሞ ለዘመን መለወጫ ዕለት በውበትዋ ተወዳዳሪ የሌላት፣ ቅንድቦቿ የተገጣጠሙ፣ አንገተ ረዥም፣ ሸንቃጣ ልጃገረድ ተፈልጋ ግብር ይጣልለታል። ይህን ካላገኘ ዓለምን ያሳልፋታል፣ ሰው ያልቃል፣ ፍጥረት የሚባል አይኖርም – የሀገሬው ሕዝብ እንደሚተርትለት።

በዚያ ዓመት ግን ያልታሰበ ነገር ደረሰ። ለድራጐን የምትስማማ ልጃገረድ በምዕራባዊው ግዛት ልትገኝ አልቻለችም– በተለይ ቅንድቦቿ የተጋጠሙ አንገተ ረዥም! የመዓት ደመና በሀገራችን አንዣበበ እያለ ሕዝቡ በጭንቀት ማጥ ውስጥ ሰጠመ። ባልቴቱና አረጋዊው በየቤቱ፣ ወጣቱና ጐልማሳው ደግሞ አሸዋ ላይ እየተንከባለለ የድራጐን አባት ነው እየተባለ ለሚነገርለት ለፀሐይ ማልቀሱን ተያያዘው።

አንዳንዱ ግን ቀስ ብሎ በሹክሹክታ በየጓዳው አንድ ነገር ያወራል። «የንጉሡ ሴት ልጅ የዓይንዋ ቅንድቦች የተጋጠመ፣ አንገተ ረዥም፣ ሸንቃጣ ናት። ለምን እርስዋን ለድራጐን አይሰጡም?»። ይሄ ሹክሹክታ ባንድ ጊዜ የሲረናይካንና የአካባቢዋን ከተሞች አጥለቀለቀው። ከዚያም አልፎ የቤተ መንግሥቱን አጥር ሰብሮ ገባ።

የሲረናይካ መኳንንት የዘመን መለወጫው ዕለት ሊደርስ 3 ቀን መቅረቱን ሲያዩ በጭንቀት ሊሞቱ ደረሱ። በዚህም የተነሣ አንድ ቀን በእልፍኝ አስከልካዩ ቤት ተሰባስበው በጉዳዩ መምከር ያዙ። ሁሉም በልቡ አንድ ነገር ቋጥሮ ነበር። «የንጉሡ ልጅ ለምን ለድራጐን አትሰጥም?» ግን ማን ደፍሮ ይንገራቸው።

በመጨረሻ እጅግ በጣም የሚቀርቧቸው መኳንንት ድራጐን በሚያመጣው መዓት ከምናልቅ በንጉሣችን ሰይፍ መሞትን እንመርጣለን› ብለው ወደ ንጉሡ እልፍኝ ገቡ።

ንጉሡ ሲፕሪዮን ነገሩን እንደ ሰሙት በድንጋጤ ሰማይ የተደፋባቸው ነበር የመሰላቸው። እየቆዩ ሲያገናዝቡት፣ ሁኔታውን ሲመረምሩት ግን አንድ እውነት ታያቸው።

ለድራጐን ማን ይቅረብ?

ንጉሥ ሲፕሪዮን በዚህ ዓለም ላይ እጅግ የሚወዱት የሚያከብሩት ነገር ቢኖር ገንዘብ ነው። «የሰው ልጅ ሰው የሚባለው ሦስት ነገሮችን ሲያሟላ ነው ነፍስ፣ ሥጋና ገንዘብን» እያሉ ደጋግመው ሲናገሩ ይሰማሉ። ከገንዘብ በላይ የሚያከብሩት ነገር ቢኖር ድራጐንን ነው። ታዲያ ገብጋባ አይደሉም። መሽቀርቀር፣ መብለጭለጭ፣ መኳኳል፣ መዋዋብ የሚወዱ ኩንስንስ አረጋዊ ንጉሥ ናቸው። ቤተ መንግሥታቸውን ለቀው ወደ ከተማው መውጣት ከፈለጉ ቢያንስ ለሦስት ሰዓት ያህል የልብስ መልበስ ዝግጅት ያደርጋሉ። «ደስታ ማለት





©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ራስን እንደፈለጉ ማድረግ ነው»
እያሉ የጥንቱን የሰሜን አፍሪካ ምሳሌ
ይጠቅሱታል።

ከዚህች ደስታ፣ ከዚህች ዓለም
መቼም መለየት አይፈልጉም። ‹ለዘለ
ዓለም የሚያኖር መድኃኒት ቢሠራ
መጀመሪያ የሚገዙት ንጉሡ ናቸው›
ይላል የሲረናይካ ሕዝብ ሲተርት
ባቸው። ዛሬ ግን አስቸጋሪ ነገር
ገጠማቸው። ያላሰቡት ዱብ ዕዳ
ወረደባቸው። የሀብቱ ጌታ የዕድሜው
ለጋሽ ድራጐን ሊቆጣ መዓትን
ሊያመጣ፣ ዓለምን ሊደበላልቃት ነው
ብለው ሠጉ። ይህ ከሆነ ደግሞ ከሚ
ወድዋት ደስታ ካልጠገቡዋት ዓለም፣
ከሚያከበሩት ገንዘብ፣ ከሚሳሱለት
ውበታቸው መለያየታቸው ነው።

ከመኳንንቶቻቸው ጋር መከሩ።
ዘከሩ። ምንም መፍትሔ አልተገ
ኘም። «እስቲ ላስብበት» አሉና
አሰናበቷቸው። እየተንጐራደዱ፤
አንዳንዴም በመስኮታቸው ድራጐን
ወዳለበት አቅጣጫ ብቅ እያሉ፤
ጭንቅ ሲላቸው ደግሞ አጠገባቸው
ካለችው ወይን እየተጐነጩ —
አወጡ። አወረዱ። ፈተሉ። ገመዱ።
ልጃቸውን ወይንም ራሳቸውን—
ፈታኝ ሰዓት።

ምሽቱን በሙሉ ሲያምሰለስሉ
ቆዩና በመጨረሻ ወሰኑ።

‹ነገ ጠዋት ሄለንን ይዘሃት...›
የዓይናቸው ኃይል እየቀነሰ መጣባ
ቸው። በወንድምዋ ላይ ማፍጠጥ፣
ጨኸው መናገር አልቻሉም። ልዑል
ማርቆስ እኅቱን ምን ያህል እንደ
ሚወዳት ያውቃሉ። አሁን እርሳቸው
ያሰቡትን ሊሰማው ቀርቶ ሊያስበው
አይፈልግም። ግን የሕይወት ጉዳይ
ነው። መሞት አይፈልጉም። ከገንዘ
ባቸው፣ ከክብራቸው፣ ከዚህች ቅን
ጦት ወዳጅ ዓለም መለየት። ገንዘብና
ዕድሜ በስተርጅና ያሳሳል።
ይጣፍጣል።

«ነገ ልዕልትን ይዘህ ወደ
ድራጐን ትሄዳለህ» ብለው ከዙፋና
ቸው ተነሡ። «ምንም ጥያቄ አልፈ
ልግም። የማዝዝህን ብቻ ትፈጽ
ማለህ! ሌላ አማራጭ የለንም። ልጅ
ቢሞት ልጅ ይተካል፣ እኔ ብሞት ግን
ማን ይተካልኛል! ጨርሻለሁ»

ልዑል ማርቆስ ከመጀመርያው
ቃላቸው በኋላ ያሉትን አላዳመጣ
ቸውም። የደም ትርታው፣ የልብ
ምቱ፤ ያቆመ መሰለው...ው— ው—
ው— የሚል ድምፅ ብቻ ይሰማዋል።
አእምሮው መሥራት አልቻለም።
እንደ ግብፁ ስፊኒክስ ሐውልት
ባለበት የቆመ መሰለው። ዓይኑ ግን
በአባቱ ላይ አፍጥጦአል። ትኩር
ብለው አዩት፤ ፊቱ ቀልቶ ዓይኑ
ደፍርሶአል።

«አባዬ ምንድነው የምትለኝ?»
ልቡ መለስ ሲልለት እነዚህ ቃላት
ብቻ ነበሩ ከአንደበቱ የወጡት።

«ያልኩትን ብያለሁ! ያንተ
ድርሻ መፈፀም ብቻ ነው። ድራጐን
ከመቆጣቱ መዓት ከማፍሰሱ በፊት
ያልኩህን ፈፅም።!

ጥለውት ወደ መኝታ ቤታቸው ገቡ።

ልዑል ማርቆስ ክርስቲያን ነው
ይህን ግን ከእግዚአብሔርና ከእኅቱ
በቀር የሚያውቅ ሌላ የለም። በሰሜን
አፍሪካ ነገሥታት ልዑላዊ ልማድ
የተነሣ ለትምህርት ወደ እስክንድርያ
በተላከ ጊዜ ነበር ከክርስቲያኖች ጋር
የተዋወቀው።

ለመጀመርያ ጊዜ ወደ ቤተ
ክርስቲያን የወሰደው ከሶርያ የመጣ
አንድ የት/ቤቱ ተማሪ ነበር።
የክርስቲያኖች ኑሮ፣ ደግነት፣ ጽናት፣
ትህትና ያስደስተዋል። ሞት ለአባቱ
ጠላት ነው። ለክርስቲያኖች ግን ክብር
ነው። ወደ ሰማያዊት ሀገራቸው
የሚሄዱበት። እርሱ በሀገሩ ቅንጦትና
ድሎት ነው የለመደው። ደስታም
የነዚያ ልጅ ነው ብሎ ነበር የሚያ
ምነው። አሁን ግን የተለየ ነገር ዓይኑ
በማየት ልቡ በመገንዘብ ላይ ነው።
በመከራም፣ በጾምም፣ በድካምም
ደስታ—ያውም የበለጠ ደስታ
ይገኛል።

ቀስ በቀስ ሥራዩ ብሎ መከታ
ተል ጀመረ። በመጨረሻ በቅድስት
ባውክልያ ቤተ ክርስቲያን ተጠመቀ።
በጥበብ መኖርን ከአበው ተምሮአልና
ወደ ሲሪናይካ ሲመለስ ለማንም
አልገለጠም። እስከ ጊዜው ድረስ።

መጀመርያ ያስተማረው እኅቱን
ነው። ሄለን የዋሕ ናት። ግልፅ።
ከወንድምዋ ሌላ ትልቅ ሰው አታው
ቅም። እናም የወንድምዋን ትምህርት
ለመቀበል ጊዜ አልፈጀባትም።

ማታ ማታ ከልዑል ማርቆስ ጋር
ትጸልያለች፣ ትማራለች፣ በቅድስት
ባውክልያ ቤተ ክርስቲያን ያጠናውን
መዝሙር ያስተምራታል።

«አንድ ቀን ከዚህ ሀገር ወጥተን
በሰላም ከእግዚአብሔር ጋር እንኖ
ራለን አንቺም ትጠመቂያለሽ፣ እስከ
ዚያው ግን ጽኚ» ይላት ነበር።

አሁን ነገሩ ሁሉ ተዘበራረቀበት።
‹ነገ ልዕልትን ይዘህ ወደ ድራጐን
ትሄዳለህ።› የሚለው የአባቱ ድምፅ
ይሰማዋል— ገዝፎ አካል ነሥቶ።
ደግሞ ቆየት ብሎ አፉ የሰማይ
መስኮት የሚያክለው የድራጐን
ጭንቅላት ወደ እኅቱ ሲጠጋ፣ ምላሱ
ሲወዛወዝ ይታየዋል። «በስመ አብ
ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ
አምላክ። አምላከ ሶስና እባክህ
ታደገን» ይላል። ዕንባ ቀደመው።
እርሱስ የእኅቱ ወንድም አይደል።

የፊቱን መቅላት፣ የዓይኑን መደ
ፍረስ የተመለከተችው ልዕልት ሄለን
ገና ስታየው ከመቀመጫዋ ተነሥታ
«ምን ሆንክ? ከአባዬ ጋር ተጣላህ?»
ስትል ጠየቀችው። አንገቱን አቀርቅሮ
በዝምታ ተዋጠ። ዓይኑ ግን ዝም ሊል
አልቻለም። ዕንባው ዱብ ዱብ አለ።

«ምን ሆንክ?» አለች ሄለን
ደግማ። የርስዋም ዕንባ ድምፅዋን
አጀበላት «እስቲ መጀመርያ እንጸ
ልይ» መኝታ ቤቱን ጥርቅም አድርጐ
ዘጋው። ጸሎት የጭንቀት ገመድ
መበጣጠሻ ሰይፍ ነው። ከጸሎት በኋላ
እንደ ጋራ የከበደው እንደ ጠጠር
ቀለለለት።

«ሄለን እንግዲህ ለኛም የክርስ
ትናው ወግ ሊደርሰን ነው መሰል።»
ፈገግታው እየጨመረ መጣ። ክርስ
ቲያን አዝኖ ይደሰታል። በለቅሶው
ውስጥ ሳቅ አለው። አባቱ ያሉትን
ነገራት። አላመነችም። የሚወድዋት
አባትዋ እንዲህ ያደርጋሉ ብላ።

«ሄለን በዚህ ዓለም ላይ
ከእግዚአብሔርና ከቅዱሳኑ በቀር
ታማኝ የለም። የሰው ሁሉ መታመኑ
ራሱን እስካልነካንበት ድረስ ነው።
ክርስቲያን ከሌላው የሚለየው ከራሱ
አብልጦ የሚወደው ሌላውን በመሆኑ
ነው። ዓለም ግን የዚህ ተቃራኒ ናት።»

«ገንዘብ ያወረው ሰው ፍቅርን
የሚያይበት ዓይን የለውም» ብሎ
ከዚህ በፊት የነገራትን አስታወሰች።
የሰማዕታት፣ የጻድቃን ታሪኮች ዛሬ
በገሐድ የምታያቸው መሰልዋት።
የቅዱሳንን ማንነትኮ መንገዳቸውን



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ያልቀመሰ አያውቀውም። አሁን የተማረችው ሁሉ ግልጥ ሆነላት። ምን ታድርግ ክርስትናኮ ሲኖሩት እንጂ ሲማሩት አይገባም።

በዚያ ሌሊት ሲመካከሩ አደሩ።

በጠዋት ልዑል ማርቆስ አባቱን ተሰናብቶ ሄለንን በበቅሎ ጭኖ ወጣ። የሀገሩ ሕዝብ በደስታ ሸኘው። ከጉድ አወጣን እያለ።

ሽምጥ ወደ ድራጐን። ሁለቱን ምዕራፍ ወደ ምዕራብ እንደተጓዘ በመንገዱ ታጠፈና ወደ ምሥራቅ ጋለበ። ጉዞ ወደ ምሥራቅ። ወደ ፀሐይ መውጫ።

«እንግዲህ እመቤቴ በማውጫሽ አውጭን» ሄለን በወንድምዋ ጀርባ ሆና ቀስ ብላ ተናገረች።

ቀኑን ሙሉ በዚያ ሐሩር ያለ አንዳች ፋታ ጋለቡ። ከባሕር የወጡ እስኪመስሉ ድረስ ላብ አጥምቋቸዋል። መዓልቱ እየገፋ ምሽቱ እየተቃረበ ሲመጣ በቅሎዋ እየደከመች እያለከለከች መጣች። ልዑል ማርቆስ በዚያ ቢላት በዚህ ምንም ማድረግ አልቻለም። የረሳው አንድ ነገር ቢኖር ማታ የሚበቃትን ያህል መመገብ እንደነበረበት ነው። አሁን በእጁ ከላበት በቀር ምንም የለም።

በቅሎዋ ተዝለፍልፋ ወደቀች። አፍዋ አረፋ ደፈቀ። ዓይንዋ ተስለመለመና እግሮችዋ ተዘረጋጉ። «ዐረፈችው ይህን የበረሃ መንገድ» አለች ሄለን ዕንባ እያነቃት። ያለዛሬ እርስዋም እንደጌታዋ ወጥታ አታውቅም።

ሄለንና ማርቆስ ዕንባ በተሞላ ዓይናቸው ሲመለከቱዋት ቆይተው ቀና ሲሉ በሩቅ አቧራው ወደሰማይ ሲያርግ አዩ። እየቀረበ የሚመጣ መንጋ ነው።

«ማርቆስ ምንድነው?» አለችው ሄለን።

«ምን ዐውቃለሁ። ምናልባት እኛን ፍለጋ የተላኩ የሲረናይካ ወታደሮች እንደሆኑ» አላት ልዑል ማርቆስ– ትክዝ ብሎ።

«እግዚአብሔር ኧረ እባክህ ታደገን» ሄለን አንገትዋን ወደ ሰማይ ቀና አደረገች።

ደግሞ ምሽቱ እየገፋ መጣ።

ይቀጥላል

# ዓምደ ወራዙት

(የወጣቶች ዓምድ)



አቶ ጥላሁን ዋቅጅራ ይባላል። በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የዓለም የምግብ ፕሮግራም የሥራ ባልደረባ ነው። በአሁኑ ሰዓት የሚገኘው ዑጋንዳ ካምፓላ ባለው የድርጅቱ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ጽ/ቤት ሲሆን ያገኘሁት ለ30ኛው ዓመት የመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የዓምደ ሃይማኖት ሰንበት ትምህርት ቤት በዓል በመጣበት ጊዜ ነው። ባለትዳርና የልጆች አባት ነው። ውይይታችንን እንዲህ ነበር የጀመርነው።

ሐመር – እስቲ በቅድሚያ ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት እንዴት እንደመጣህ አጫውተኝ?

ጥላሁን – በ1964 ዓ.ም ፍልሰታ ጾም በጽርሐ ጽዮን ሐዋርያት ጎላ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ለማስ

ጥላሁን – እኔ በሰንበት ትምህርት ቤቱ አገልግሎት ውስጥ በተለይም የአገናኝ ኮሚቴና የቁጥጥር ኮሚቴ ውስጥ በሠራሁባቸው ጊዜያት ከወላጆች ይህን መሰል ሮሮ እንሰማ ነበር። የችግሩ ምንጭ ሁለት ነው።

የሰንበት ትምህርት ቤቱ አባላት

## ሃያ ሰባት ዓመታት – በሰንበት ትምህርት ቤት አገልግሎት

ቀደስ ከሠፈር ልጆች ጋር ተሰባስበን ሄድን። ያን ጊዜ በጣም ሕፃናት ነበርን። ከቅዳሴ በፊት በአንድ ቤት ሰብስበውን ዲያቆናቱ ያስትምሩን ነበር፤ መዝሙር፣ ተረት፣ ድራማ እያቀረቡ። ይህ የእነርሱ አገልግሎት በጣም ስላስደሰተን የፍልሰታ ጾም ሲያበቃ ተመካከርንና የሚቀርበን የቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ስለነበር አንድ እሑድ ወደዚያው ሄድን። ከቅዳሴ በኋላ የሕፃናት መርሐ ግብር ስለነበር ተመዝግበን መከታተል ጀመርን። ከዚያች ሰዓት ጀምሬ ነው በሰንበት ትምህርት ቤት ሕይወት መካፈል የጀመርኩት።

ሐመር – በስንት ዓመት ዕድሜህ፣ የስንተኛ ክፍልስ ተማሪ እያለህ ነው የጀመርከው?

ጥላሁን – የ12 ዓመት ልጅ ሆኜ የ6ኛ ክፍል ተማሪ በነበርኩበት ጊዜ ነበር።

ሐመር – ብዙ ወላጆች የሚያማርሩት አንድ ነገር አለ «ልጄ ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት ማዘውተር ከጀመረ(ረች) በትምህርቱ ቀነሰ፣ አልታዘዘኝ አለ» የሚል። አንተ ይህ ችግር አልገጠመህም ነበር?

የምንዘነጋው ነገር አለ። ጠዋት ማታ ካልተጣደፍን፣ ካልተሰበሰብን፣ ካልባከንን ሥራው የሚቃና አይመስለንም። የእግዚአብሔር አገልግሎት መሆኑ ይረሳና የጥረታችን ውጤት ብቻ ይመስለናል። በዚህም የተነሣ ለአንድ ሰሞን በጋለ መንፈስ እንሠራና እየቆየን መቀዝቀዝ ቸል ማለት እናመጣለን። በትምህርታችንም እግዚአብሔር ያውቃል የሚል ፈሊጥ ስላለን አናጠናም። እግዚአብሔርኮ ጥናታችንን ይባርክልናል እንጂ አያጠናልንም። ቅዱስ ጳውሎስ ለወንጌል ሥራ ምንም ቢጣደፍ ማታ ማታ ግን ለኑሮው መደገፊያ ድንኳን ይሠፋ ነበር። ይህን እንረሳዋለን። እኔ ትዝ ይለኛል አንዳንድ አባላት በጣም ከመጨነቃቸውና እነርሱ ከሌሉ ሥራ የሚሠራ ስለማይመስላቸው ወደ ሰንበት ትምህርት ቤቱ ይመጣሉ። ነገር ግን በዚያ ሰዓት የሚሠራ ስለሌለ ተሰብስበው ሲያወሩ ይውሉ ነበር። ማሰቡ፣ መጨነቁ ባልከፋ ነበር። ነገር ግን ከኛ በላይ ለአገልግሎታችን እግዚአብሔር እንደሚያስብልን መዘንጋት የለብንም።



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

በተለይ በዚህ ሁኔታ የቆዩ አባላት በትምህርት መቀዝቀዝ፣ ከክፍል መውደቅ ሲገጥማቸው ይደነግጣሉ። «እግዚአብሔር አይረዳንም እንዴ!» ብለው ይጠራጠራሉ። ከዚህ በኋላ የነበራቸው ፍቅርና መንፈስ ቀዝቅዞ ርግፍ አድርገው እስከመተው ይደርሳሉ።

እኔ በነበርኩበት ጊዜ ከሰንበት ትምህርት ቤቱ ፕሮግራም ውጭ ያለውን ሰዓት እንድናጠና ሁል ጊዜ እንመካከር ነበር። ሥራችንን ካጠናቀቅን በቶሎ ወደ ቤት ሄደን ወደ ጥናታችንና ለወላጆቻችን ወደመታዘዝ እንመለሳለን። ይህ ሁኔታ በጣም ጠቅሞናል። ስለዚህ የሰንበት ትምህርት ቤት አባላት ለሌሎች መሰናክል እንዳንሆን፣ በሕይወታችንም የማንችለው ፈተና እንዳይመጣብን ዓላማችንን መዘንጋት የለብንም።

ሁለተኛው ደግሞ በወላጆች በኩል ነው። ልጆቻችንን እኮ በቤተክርስቲያን ትምህርት፣ በሰንበት ትምህርት ቤት ሕይወት ኮትኩተን የማሳደግ ኃላፊነት አለብን። ጢሞቴዎስን ወላጆቹ ናቸው በሃይማኖት ኮትኩተው አሳድገው ከቅዱስ ጳውሎስ እንዲገናኝ የኤፌሶንም ሊቀጳጳስ እንዲሆን ያበቁት። ዮሐንስ አፈወርቅን በእምነት በሥነ ምግባር ኮትኩታ አሳድጋ ለክብር ያበቃችው እናቱ አትናስያ ናት።

ስለዚህም በቅድሚያ ግዴታችንን እንወቅ። ከዚያ በኋላ ግዴታችንን እንዴት እንደምንወጣ እናስብ። በርግጥ ሁላችንም ወላጆች ልጆቻችን ቢያገለግሉን፣ ቢታዘዙን ተምረውም ለወግ ለማዕረግ ቢበቁልን ምኞታችንም ጥረታችንም ነው። ነገር ግን ለእግዚአብሔር የማይታዘዙ፣ እግዚአብሔርን የማያውቁ ልጆቻችን እኛን ያገለግሉናል ይጦሩናል ብሎ ማሰብ ከንቱ ነው። ለእግዚአብሔር አልታዘዝም ብሎ የማይገባ መሥዋዕት ያቀረበው ቃየል በእግዚአብሔር ላይ ዐምፆ ወንድሙን ገድሎ፣ እናት አባቱን በመረረ ኀዘን ላይ ጥሎ ሸሸ እንጂ አልጠቀማቸውም። እኛ ከዚህ ልንማር ይገባናል። በሆነ ባልሆነው ከሰንበት ትምህርት ቤት ቅሩ ከምንላቸው በትክክል ተቆጣጥረን እንዲያጠኑ እንዲታዘዙ እያደረግን የሰንበት ትምህርት ቤቱንም ሰዓት ዐውቀን ለእግዚአብሔር የሚገባቸውን ያደርጉ ዘንድ መላክ አለብን።

አንዳንዴ ችግር አለ። አንዳንድ ወጣቶች በሰንበት ትምህርት ቤት አመካኝተው አልባሌ ቦታ ሊውሉ ይችላሉ። ይህ ግን የወላጆች ቸልተኝነት የሚያመጣው ነው። ከሰንበት ትምህርት ቤቱ ጋር በቅርብ መሥራት አለብን። የመዝሙሩን፣ የትምህርቱን ሰዓት ማወቅ አለብን። የልምምዳቸውን ሰዓት መጠየቅና መረዳት አለብን። ከሰንበት ትምህርት ቤቱ ውስጥ ልጆቻችን ምን አገልግሎት ምን ውጤት አመጡ ብለን መከታተል ይገባል። ያ ከሆነ ልጆቻችንን በመንፈስም በሥጋም ለቁም ነገር እናበቃቸዋለን። ነገር ግን ድርሻችንን ረስተን በልጆቻችን አመካኝተን ከሰንበት ትምህርት ቤት ብናስቀራቸው ከእግዚአብሔር ሠርቀን ለዲያብሎስ እየሰጠናቸው መሆኑን አንርሳ።

ሐመር – ለ27 ዓመታት በሰንበት ትምህርት ቤቱ ውስጥ ስታገለግል እዚሁ ደርሰሃል። አንዳንድ ጊዜ ግን ጀምረው ያቋረጡ እንዲያውም ሕይወታቸው ተቀይሮ በአልባሌ ቦታ የሚገኙም አሉ። የዚህ ምክንያቱና መፍትሄው ምንድነው ትላለህ?

ጥላሁን– ልክ ነህ ይኼ ችግር ብዙ ጓደኞቼን አስቀርቶብኛል። ዛሬ በሌላ ቦታ ስንገናኝ የድሮውን ሳነሣባቸው ያዝናሉ። ከዘማሪነት ዘፋኝነት፣ ከፕሮግራም መሪነት ዳንሰኝነት የገቡ ዐውቃለሁ። ምን መሰለህ በቅድሚያ የሰንበት ትምህርት ቤት ሕይወት ማለት አጋንንት ሁሉ ተጠርገው ወጥተው መንገዱ የጽድቅ አስፓልት የተሠራበትና በደስታ ያለፈተና የምንጓዝበት አለመሆኑን እንዘነጋለን። አንዳንድ ወጣቶች አባል ከሆኑ በኋላ የሚያስደነግጥ ሁኔታ ያጋጥማቸዋል። ያልጠበቁትን ነገር ያያሉ። እንዴ! እነዚህም እንዲህ ያደርጋሉ» ይሉና ይሸሻሉ። የሰንበት ትምህርት ቤት ሕይወትኮ የተጋድሎ ሕይወት ነው። ኃጢአትን ለማሸነፍ፣ ዲያብሎስን ድል ለማድረግ የተሰባሰቡ ክርስቲያኖች ያሉበት እንጂ ኃጢአትን አሸንፈው የቅድስናን ማዕረግ ተቀዳጅተው ፍጹም ሆነው የሚሰባሰቡበት አይደለም። ይህን ማወቅ አለብን። አባታችን ዮሐንስ ሐፂር አንድ ወንድሙን ኃጢአት ሲያሸንፈው «ይህን ወንድሜን ያሸነፈ ዲያብሎስ ነገ ወደኔ መምጣቱ አይቀርም» እያለ ያለቅስ ነበር ይባላል። እኛ ይህን ብንማር ጥሩ ነበር። በሰንበት ትምህርት ቤት ኑሮ ፈተና አለ። መውደቅ አለ፣ መነሣት አለ። መሸነፍ አለ፣ ማሸነፍም አለ። እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ ወድቆ የሚነሣ፣ እንደቅዱስ ዮሐንስም ጸንቶ የሚዘልቅም አለ።

ሁለተኛው ችግር የሰንበት ትምህርት ቤት ሕይወት እንደ ሥጋዊ ምኞታችን አልሄድልን ሲል የምንሸሽበት ነው። በተለይም ቁጥጥሩ ጠበቅ ትምህርቱ ጠለቅ ሥነ ሥርዓቱ ያዝ ሲል ብዙዎች አንወድም። አንዳንዴ ምን መሰለህ እንደ መዝናኛ እናየዋለን። ለመርሐ ግብሩ፣ ለአገልግሎቱ ደንታ ቢስ እንሆናለን። በተለይማ ከልጆች ጋር እየተዋወቅን ከኮሚቴዎች ጋር እየተለማመድን ስንመጣ እግዚአብሔርን በእጃችን የያዝን የማይቆጣን፣ የማይቀጣን ይመስለናል። በዚህ ሰዓት ታዲያ፣ ቀልድ፣ ፌዝ፣ መናናቅ፣ ፕሮግራም አቋርጦ መግባትና መውጣት በትምህርት መቀለድ፣ ማውራት፣ መተማማት ይከተላል። ያን ጊዜ ቁጥጥሩ ሲጠብቅ ወደኋላ መሸሽ ይመጣል።

ስለዚህ የመጣንበትን ዓላማ እንወቅ፣ ምን ያህል ፍሬ እንዳፈራን እንጠይቅ ሰንበት ትምህርት ቤት መንፈሳዊ ኑሮ የሚገበይበት ት/ቤት እንጂ መዝናኛ አይደለምና።

ሌላው የመጨረሻው ደግሞ በመንፈስ ጀምረን በሥጋ መጨረሻችን ነው። ስንመጣ አለባበሳችን፣ ንግግራችን፣ ምኞታችን፣ ተግባራችን፣ ሰላምታችን መንፈሳዊ ይሆናል። እየቆየን ስንሄድ ግን ዓላማችንን እንዘነጋዋለን። በተለይ ከዓለማውያን ጋር መዋል ስንጀምር የነርሱንና የኛን ሕይወት እያነፃፀርን በብዙ ወደ ኋላ የቀረን፣ ብዙ ነገር የጎደለብን መንፈሳዊነታችን በሥጋ የጎዳን ይመስለንና የነርሱን ሕይወት እንደገና እየናፈቅን ከቤተክርስቲያን መራቅ እንጀምራለን። የሚያሳዝነው ነገር ስንመከር መንፈሳዊ ሽፋን እየሰጠን፣ ጥቅስ እየጠቀስን ለማሳመን እንሞክራለን እንጂ ስህተታችንን እሺ ብለን አለማረማችን ነው። በመሆኑም መጀመራችንን ሳይሆን መፈጸማችንን እግዚአብሔር እንደሚፈልገው እናስብ። ያለህን አጽንተህ ያዝ ይለናል ልዑል እግዚአብሔር። ራእይ 3፥11።

ሐመር – በሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ በመኖርህ ያገኘኸው ትልቅ ነገር ምንድነው?

ጥላሁን – የሰንበት ርምህርት ቤት ሕይወት ጥቅሙ በሥጋም በነፍ



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

ስም ነው። በአገልግሎት ሕይወት በኮሚቴዎች ውስጥ በመሥራቴ ብዙ የሥራ ሂደቶችን ተምሬአለሁ። ከሰዎች ጋር አብሬ ሠርቻለሁ። ችግርን ለመፍታት ተወያይቻለሁ። በተለይ በሊቀመንበርነት ስሠራ ከቤተክርስቲያን ሰዎች፣ ከመሥሪያ ቤት ኃላፊዎች፣ ከወላጆች ጋር ያገናኘኝ ነበርና የሥራን ጠባይ የማኅበራዊ ኑሮን ሁኔታ ተመልክቻለሁ። ዛሬ በሥራዬ ይህ ልምድ እጅግ ጠቅሞኛል። በሰንበት ትምህርት ቤት ያገኘሁትን ልምድ እጠቀምበታለሁ። ያንን የሥራ ልምድ በትምህርትም ሆነ በስጦታ የትም ማግኘት አልችልም ነበር።

የራሴን ሕይወት ከመጥፎ ነገሮች ለመጠበቅም ረድቶኛል። ምንም እንኳ ብወድቅና ብነሣ ኑሮዬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመሆኑ ሃሳቤ፣ ምኞቴ፣ ዓላማዬ፣ አኗኗሬ፣ ቋንቋዬ፣ ሥነ ምግባሬ የቤተክርስቲያን እንዲሆን አስችሎኛል።

ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ለዛሬው መልካም ትዳሬ መሠረቱ የሰንበት ትምህርት ቤቴ ነው። በእምነት፣ በሥርዓት፣ በሃሳብ የምንጣጣም፣ አንድ የሆንን እኅት ያገኘሁትም በሰን በት ትምህርት ቤት ሕይወት በመጓዜ ነው እላለሁ።

ርትዕት ስለሆነችው ሃይማኖቴ ጠንቅቄ እንዳውቅ ያደረገችኝ ሰንበት ትምህርት ቤቴ ናት። ዛሬ አንዳንድ ጥፋቶች ሲታዩ እንኳን ልክ አይደለም ከማለት ደረጃ የደረስኩት ሰንበት ትምህርት ቤት ትክክለኛውን መንገድ ስላስተማረችኝ ነው ባይ ነኝ።

ሐመር – ብዙ የሰንበት ትም ህርት ቤት አባላት ወደትዳሩ ዓለም ሲገቡ መርሐ ግብር መካፈላቸውንና ማገልገላቸውን ርግፍ አድርገው ይተውታል። ለምን ሲባሉ አልተመ ቸንም፣ ኑሮ ጣጣው ብዙ ነው ይላሉ አንተ ይህ ችግር አልገጠመህም።

ጥላሁን – ባለቤቴ የሰንበት ትም ህርት ቤት አባል ናት። የኔን መንፈሳዊ ሕይወት ከኔ በላይ ታውቀዋለች። ምን እንደምሠራ ማንን እንደማገለግል ታውቃለች። እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ሰንፌ ወደ ኋላ ስል እራሷ ታበረታታኛለች። እዚህ እያለሁ የሰን በት ትምህርት ቤት ሥራዎችን ለመ ሥራት ጊዜ ስለማይኖረኝ ወደ ቤት አምጥቼ በምሠራበት ጊዜ እየተጋ ገዘን ነበር የምንሠራው።

በሰንበት ትምህርት ቤቱ መርሐ ግብር ሰዓት አብረን ልጆቻችንን ይዘን እንመጣለን። አብረን ተምረን አብረን እንመለሳለን። በአጠቃላይ በመንፈ ሳዊ ሕይወቱ የባለቤቴ አጋዥነት ስላለበት ችግር አልገጠመኝም። ትዳር የመንፈሳዊ ኑሮአችን አንድ እርከን እንጂ ጡረታ መውጫ አይደለም። የተጋባንበት ዓላማ እግዚአብሔርን ለማገልገል ከሆነ ሌሎች ነገሮች ሁሉ ሁለተኛ ናቸው ማለት ነው። በርግጥ ማኅበራዊ ኑሮ አስቸጋሪ ነው። ውጣ ውረድም አለው። ነገር ግን ማሸነፍ የምንችልበትን ጥበብ ሊያስተምረን ኃይል ሊሰጠን የሚችለው እግዚአብ ሔር ስለሆነ ከርሱ መለየት የለብንም።

ሐመር – አሁን ያለኸው ከኢት ዮጵያ ውጭ ነው። ሰንበት ትምህርት ቤቱ 30ኛ ዓመቱን ሲያከብር እንዴት ለመገኘት ቻልክ። ምክንያቱም እንኳ ንስ ከውጭ ለመምጣት ከግቢው አጠገብ ሆነን መርሐ ግብር ለመሳተፍ ይቸግረናልና።

ጥላሁን – ሰንበት ትምህርት ቤቴ አሳድጋኛለች ለወግ ለማዕረግ አብቅታኛለች ይህ ያለሁበትን ሥራ ተሯሩጬ፣ ወጥቼ ወርጄ በገዛ ጥረቴ ያገኘሁት አይደለም። እግዚአብሔር መመላለሴን ቆጥሮ የለገሰኝ ነው። ስለዚህም የዓመት ፈቃዴን ስሞላ ከሰንበት ትምህርት ቤቴ ዓመታዊ በዓል ጋር እንዲሄድልኝ አደረግኹ።

እግዚአብሔር ስለፈቀደም ለመገ ኘት በቃሁ። ከልብ ካለቀሱ ዕንባ አይገድም ይባል የለ!

ሐመር – ከሀገር ውጭ ያለው ኑሮህ በመንፈሳዊ ሕይወትህ ላይ ችግር አልፈጠረብህም። ብዙዎች እኮ ከወጡ በኋላ ከሌላው ዓለም ጋር ተቀላቅለው ይቀሩብናል።

ጥላሁን – እዚህ እያለሁ አንድ ልምድ ነበረኝ። ወደ ፊልድ ስወጣ ብችል በደረስኩበት ዕለት ያለበለዚ ያም በቀጣዩ ቀን ቤተክርስቲያን ያለበትን ቦታ ፈልጌ አገኝና እዚህ በሰንበት ትምህርት ቤት አደርገው የነበረውን አገልግሎት እዚያም እቀጥላለሁ። አሁን ያለሁበት ዑጋንዳ ካምፓላ እንደደረስኩ በአካባቢው የኛ ቤተክርስቲያን መኖሯን ጠየቅኹ። ከከተማው 7 ኪ.ሜ ርቀት እንደምት ገኝ ሰማሁና ሄድኩ። አገልጋዮችም ምእመናኑም ዑጋንዳውያን ናቸው። በጣም ተገረምኩ። ሥርዓታቸውም እምነታቸውም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ነው። ሰዎችን ወደ ኢትዮጵያ ልከው በማስተማር አገል ግሎቱን ለማግኘት እንደበቁ ነግረው ኛል። የሚቀድሱትና የሚያስተምሩት ሉጋንዳ በተባለ ቋንቋ ነው። ከሄድኩ ጀምሮ እዚያ እየሄድኩ አስቀ ድሳለሁ።

በሌላ በኩል ግን የጠቀመኝ ነገር ከዚህ የወሰድኩትና የሚላክልኝ ነው። የትምህርት፣ የመዝሙር የቅዳሴ ካሴቶች ወስጄአለሁ፣ የጸሎት፣ የትምህርት የሥርዓት መጻሕፍት አሉኝ። ከዚህ በተጨማሪ ባለቤቴና የሰንበት ትምህርት ቤቱ አባላት እዚህ የሚታተሙትን መንፈሳውያን መጽሔቶች ጋዜጦችና መጻሕፍት ይልኩልኛል። እናም በአካል ብለይም በመንፈስ እዚህ ነኝ ማለት እችላለሁ። እንደኔ ዓይነት አጋጣሚ የገጠማቸው መንፈሳውያን እኅቶቼና ወንድሞቼ ወደ ውጭ ሲወጡ ለመንፈሳዊውም ሕይወታቸው በመጨነቅ ከዚሁ አስበውበት ቢነሡ ጥሩ ይመስለኛል።

ከዘጋቢው፣ የሰንበት ትምህርት ቤት ሕይወት ከልጅነት እስከ ዕለተ ሞት ብሎም በሰማያዊ ኑሮአችን የሚቀጥል እንጂ ጡረታ የሚወጣበት አለያም ችግር በገጠመው ቁጥር የሚቋረጥ አይደለም። ቦታ፣ ጊዜ፣ ምክንያት፣ ትዳር፣ ሥራ አይወስኑ ትም። ጉዞአችን መንፈሳዊ በረከት ለማግኘት ነውና። መንገዱን በመንፈስ ጀምረው በሥጋ የሚፈጽሙበት፣ በጋለ ስሜት ጀምረው በደንታ ቢስነት የሚያጠናቅቁበት፣ በትጋት ጀምረው በድካም የሚያገባድዱበት ሳይሆን እስከ መጨረሻው በጽናት የሚጓዙ በት ነውና ሁላችንም የሕይወትን አክሊል ለማግኘት እንትጋ፤ ሰንበት ትምህርት ቤት የሕፃናት ብቻ አይደ ለም። የወጣቶች የዐዋቂዎች፣ የሽማ ግሌዎች፣ የባለትዳሮች፣ የመነኮ ሳት...ወዘተ ጭምር ነው። ሁላችንም እናገለግልበታለን እንገለገልበት ማለን። ለቤተ ክርስቲያን ድርሻችንን እንወጣበታለን። ✣



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# እናስተዋውቃችሁ

## ዲማ ጊዮርጊስ ትናንት እና ዛሬ

**ክፍል 1**

**(ከሐመር ዘጋቢ)**

ዕለቱ እሑድ ነው። ጥቅምት 6/87 ብቸና ከተማ ገብቼ አድሬ ስለነበር በንጋታው ሰኞ ጉዞዮን ተያያዝኩት። ከዚህ በፊት በሐዲስ ዓለማየሁ የ«ፍቅር እስከ መቃብር» መጽሐፍ የማውቀውን ዲማ ዛሬ በአካል ተገኝቼ በዓይነ ሥጋ ላየው።

ከብቸና ወደ ደብረ ወርቅ በሚወስደው መንገድ 20 ደቂቃ ያህል ተጉዤ ከመኪና በመውረድ መጋቢ መንገዱን ተከትዬ ጉዞየን ቀጠልኩ። ከአዲስ አበባ 285 ኪ.ሜ ይሆናል። ከጠዋቱ 1:30 ፀሐይዋ አካባቢውን ወርቃማ ብርሃን አልብ ሳዋለች። የገበሬው ማሳ የደረሰው ታጭዶ የባቄላው እሸት ደግሞ ብሉኝ ብሉኝ ይላል።

ገና በማለዳው ለሥራ የተሠማሩት ገበሬዎች እንግዳ ሆኜባቸው ከአጨዳቸው ቀና እያሉ በመገረም ይመለከቱኛል።


በማሳው መካከል የሚያልፈውን መጋቢ መንገድ አገባድጄ አፋፉ ላይ ስደርስ ቁልቁል የዲማን መንደር አየሁት። ከመንደሩ በስተ ደቡብ የጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ግርማ ሞገስ ለብሶ ይታያል።

መንደሩን በስተ ግራዬ ትቼ ወደ ገዳሙ አቀናሁ። ፀጥ ረጭ ብሏል። ከአዕዋፍ ድምፅ በቀር የሚሰማ አልነበረም። በበሩ ላይ ብቻ አረጋውያን መነኮሳት ወግ ቢጤ ይዘው ተቀምጠዋል። ግቢውን ዘልቄ ተሳለምኩና ቀና ስል አጠገቤ ዱላ የያዘ አንድ ሰው ቆሞአል። ዘበኛ ኑረዋል። የመጣሁበትን ምክንያት ነግሬ የያዝኩትን ደብዳቤ ሳሳያቸው ወደ ገዳሙ ይዘውኝ ገቡ።

የገዳሙ አለቃ መ/ር ገብረ እግዚ. አብሔር በዚያ ቦታ ለብዙ ዓመታት ወደ ተቀመጡት ወደ መ/ር ተወልደ ማርያም ወስደው አስተዋወቁኝና ወዲያው የገዳሙ አለቃ ታሪኩ የተጻፈበትን ገድለ ተከሥተ ብርሃንን ይዘውልኝ መጥተው ውይይታችንን ጀመርን።

ይህን ገዳም የቆረቆሩት አባት አባ ተከሥተ ብርሃን ይባላሉ። (በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን) እኒህ አባት በታላቁ ገዳም በደብረ ሊባኖስ ይኖሩ የነበረ ሲሆን አቡነ ያዕቆብ የተባሉት ግብፃዊ ሊቀጳጳስ 12ቱን ንቡራነ ዕድ በመላው ኢትዮጵያ ሲያሰማሩ ጐጃም በዕጣ ደረሳቸው።

አባ ተከሥተ ብርሃን በመጀመሪያ በእነብሴ ነዳ ጹራ በተባለች ቦታ ስብከታቸውን ጀመሩ። ያ ቦታ አምልኮ ጣዖት የበዛበት ስለነበር ስብከተ ወንጌልን አስፋፍተው ሕዝቡን እያጠመቁ ተቀመጡ። ሕዝቡም በስብከታቸው እያመነ ጥምቀተ ክርስትናን ለማግኘት ይመጣ ጀመር። በተለይም አንድ ቀን ከሕዝቡ ብዛት የተነሣ ተጠማቂው ሳያበቃ ቀኑ መሸባቸው። እርሳቸው ግን የመዳን ቀን ዛሬ ነው እያሉ በትጋት ማጥመቃቸውን ቀጠሉ። በዚህም ሰዓት በዙሪያቸው በተሰበሰበው ተጠማቂ ላይ መንፈስ ቅዱስ ሲወርድ አካባቢው በብርሃን ተሞላ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በኪሞስ ይባል የነበረው ስማቸው ተለውጦ ተከሥተ ብርሃን (ብርሃን ተገለጠ) ተብለው መጠራታቸውን ገድላቸው ይናገራል።



ከነዳ ጹራ ተነሥተው ዛሬ ዲማ ወደሚባለው ቦታ በመምጣት በዋሻው ውስጥ ተቀመጡ። ይህ ዋሻ ከቤተ ክርስቲያኑ የ40 ደቂቃ መንገድ ያስኬዳል። ገደል ውስጥ ነው ሁለት ክፍል ያለው ሲሆን አንደኛው አባ ተከሥተ ብርሃን ታቦተ ማርያምን አስገብተው የጸለዩበት ሲሆን ሌላኛው ደግሞ በአታቸው ነበር።

የዚያን ዘመኑ ንጉሥ አፄ ዓምደ ጽዮን ብዙ ውጊያዎችን ከአረማውያን ጋር በማድረጉ ከእነርሱ የተማራቸው ብዙ ባህሎች ነበሩት። በዚህም ምክንያት የእንጀራ እናቱን እስከ ማግባት ደረሰ። ያን ጊዜ ዮሐንስ መጥምቁ ሄሮድስን እንደ ተቃወመው የደብረ ሊባኖሱ 3ኛ እጨጌ አባ ፊልጶስ ፊት ለፊት ተቃወሙት።

ንጉሡም ከስህተቱ ከመመለስ ይልቅ እጨጌ ፊልጶስን ወጅ በተባለ ከተማው ደማቸው እንደጐርፍ እስኪ ወርድ ድረስ አስደብድቦ ወደ ትግራይ አጋዛቸው። በዚህም የተነሣ ከርሳቸው ጋር ተባብራችኋል ተብለው እነ አባ ተከሥተ ብርሃንም ተጋዙ።

አፄ ዓምደ ጽዮን ሞቶ የስደቱ ዘመን ሲያበቃ አባ ተከሥተ ብርሃን በጌምድር ደብረ ግሼን በመቀመጥ ካስተማሩ በኋላ ሞጣ ደብረ ጦት በቅዱስ ሚካኤል ስም ቤተክርስቲያን ተክለው 9 ዓመት አስተምረዋል። ከዚህ ቀጥለው በአዴት፣ በሳርካ፣ በአመዳሚት (ወሰን አምባ) እየተዘዋወሩ አብያተ ክርስቲያናትን እያነጹ ሕዝቡን ካስተማሩ በኋላ በመጨረሻ ወደ ደብረ ዲማ ተመለሱ።

አባ ተከሥተ ብርሃን በዲማ ለ13 ዓመታት ሥርዓተ ምንኩስናን ሠርተው ገዳም መስርተው በመንፈሳዊ ተጋድሎ ከኖሩ በኋላ አፄ ዳዊት ዝናቸውን ሰምቶ በመምጣት ዛሬ ገድእናዛያ በሚባሉት ወንዞች መካከል ያለውን ርስት በመስጠት በ1379



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ዓ.ም ገዳሙን አጸናው። አባ ተከሥተ ብርሃን መጋቢት 10 ቀን ዐርፈው በዋሻው ውስጥ ተቀበሩ።

ከአባ ተከሥተ ብርሃን ቀጥለው የገዳሙ መምህር የነበሩት አባ ቶማስ ናቸው። እኒህ አባት መሾማቸውን ለማስታወቅ ወደ ንጉሥ ዳዊት መናገሻ ከተማ በሄዱበት ጊዜ ነበር ከኢየሩሳሌም ከግማደ መስቀሉ ጋር የመጣውን የታቦተ ቅዱስ ጊዮርጊስን ተአምር ያዩት።

ይህ ታቦት ከግማደ መስቀሉ ጋር ከመጣ በኋላ በቤተ መንግሥቱ አካባቢ ተቀመጠ። ነገር ግን አካባቢው በዐውሎ ነፋስ፣ በመብረቅና ነጐድጓድ መናወጥ ስለጀመረ ንጉሡ ከየገዳሙ ደጋግ አባቶችን ጠርተው ታቦተ ጊዮርጊስን ወደ ገዳማቸው እንዲዋስዱት ነገሩዋቸው። ነገር ግን ከመንበሩ የሚያንቀሳቅሰው ጠፋ። በዚህ ሰዓት ነበር አባ ቶማስ የደረሱት።

አባ ቶማስ ፈቃደ እግዚአብሔርን ጠይቀው ወደ መንበሩ በመቅረብ ሲያነሡት ያለምንም ችግር ተነሣላቸው። ንጉሡም በቅዱስ ጊዮርጊስ ተአምር ተገርመው ለቤተ ክርስቲያኑ ማሠሪያ የሚሆን ብዙ ሺ ወርቅና ብር በመስጠት ወደ ዲማ ሸኙዋቸው።

አባ ቶማስም የቅዱስ ጊዮርጊስን ታቦት በፊት ታቦተ ቅድስት ድንግል ማርያም በነበረችበት ዋሻ አስቀመጡት።

አባ ቶማስ መጋቢት 13 ቀን ካረፉ በኋላ ታቦተ ቅዱስ ጊዮርጊስ ለ200 ዓመታት በዋሻው ውስጥ ኑሮአል። በዚህም ጊዜ አባ ስቡሕ አምላክ፣ አባ ሠረቀ ብርሃን፣ አባ ማቴዎስ የተባሉ ደጋግ አበው ገዳሙን ያስተዳደሩት ሲሆን ከአባ ቶማስ ቀጥለው በደግነታቸው፣ በተጋድሎዋቸውና በተሰጣቸው ጸጋ የታወቁት አባት ስድስተኛው አበምኔት አባ ተክለ አልፋ ናቸው።

የአቡነ ተክለ አልፋ ቤተሰቦች ትውልዳቸው ሸዋ ሲሆን በአፄ ይስሐቅ ዘመነ መንግሥት ምሥራቅ ጐጃም ጐፍጭማ ወደተባለው ቦታ መጥተው ሠፈሩ። አባ ተክለ አልፋም የተወለዱትና ያደጉት በዚሁ ቦታ ነው። ለዐቅመ አዳም በደረሱ ጊዜ ወላጆቻቸው ሊድርዋቸው ሲዘጋጁ ጠፍተው ወደዲማ መጡ።

በዚህ ጊዜ የዲማ አበምኔት የነበሩት አባ ማቴዎስ ተቀበሏቸውና በእግራቸው ሥር ሥርዓት ምንኩስናን አስተምረው በተጋድሏቸውና በደግነታቸው ስለተደሰቱ በሕይወት እያሉ በእግራቸው ተክተው አበምኔት አደረጉዋቸው።

አባ ተክለ አልፋ ከደግነታቸው ብዛት የሚቀርብላቸውን መቁነን ሳይቀር ለተራቡት እየመጸወቱ ጦማቸውን ያድሩ ነበር። ከዚህም ሌላ ልጆቻቸውን ማሳደግ የማይችሉትን ወላጆች እየተቀበሉና እየረዱ ያሳድጉላቸው ነበር።

በዚህ መሐል የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አጥፊ የሆነው ግራኝ ተነሣ። አባታችንም ማኅበረ መነኩሳቱን ይዘው ወደ በጌምድር ተሰደዱ። ግራኝ አሕመድ ሲሞት ወደ ዲማ ተመለሱ።

ያን ጊዜ የገዳሙ መነኮሳት ስደት ስላደከመን ባንድ ቅጽር መውጣት መግባት፣ ባንድ ቤት መብላት መጠጣት አይቻለንምና መቁነናችን በየበአታችን ይምጣልን ሲሉ ጠየቁዋቸው። ከዚህ በኋላ በአንድ ማዕድ ቀርቶ ሁሉም በየበአቱ መመገብ መጀመሩን ገድላቸው ይናገራል።

ዲማ እስከ አባ ተክለ አልፋ ዘመን (15ኛ መቶ ክፍለ ዘመን) ከማኅበረ መነኮሳቱ ሌላ አልነበረባትም። ከስደት ሲመለሱ መነኮሳቱ በመድከማቸው የተነሣ አባ ተክለ አልፋ «ደበሌ» የተባለውን ሰው አስመጥተው ትዳር ካስያዙት በኋላ መሬቱን እያረሰ ገዳሙን እንዲረዳ አደረጉት። ዛሬ በዲማ የሚገኘው ሕዝብ የርሱ ልጆች መሆናቸውን አረጋዊው መ/ር ተወልደ ማርያም ይናገራሉ።

አባ ተክለ አልፋ በፊትም በኋላም የማየት ጸጋ ነበራቸው የሚሠወራቸውም ነገር አልነበረም። አንዱ ባለቅኔ «ተክለ አልፋ በሰዶምና ገሞራ ዘመን ቢኖሩ አይተርፋም ነበር» ያለውም ለዚህ ነበር። የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ከዋሻ የወጣው በርሳቸው ዘመን ነው።

እኒህ ታላቅ አባት በተጋድሎ ከኖሩ በኋላ በ75 ዓመት ዕድሜያቸው ታኅሣሥ 8 ቀን በበአታቸው ውስጥ ሲያርፉ ያያቸው አልነበረም። በትራቸውን ግን እንደ ቢታንያ ድንጋዮች አፍ አውጥታ «አባታችን አረፉ» እያለች ለማኅበረ መነኮሳቱ እየዞረች ተናገረች።

ከርሳቸው በኋላ ዲማ ለ400 ዓመታት ታላቅ ገዳምና የአብነት ትምህርት ቤት ሆኖ ይኖር ነበር። ዛሬ ግን ተጐሳቁሏል። መሬቱ ተነጥቆ ባዶ እጁን ስለቀረ መነኮሳቱ በችግር ይሰቃያሉ። የሚቀምሱት የሚልሱት የላቸውም።

እጅግ ያሳዘነኝ ነገር ቢኖር የቅኔ፣ የመጽሐፍ፣ የድጓ፣ የዜማ ትምህርት ወንበር ተዘርግቶ በሰፊ ገበታ ይሰጥበት የነበረው ዲማ የኛ ትውልድ እንኳን በፍቅር እስከ መቃብር በአለቃ ክንፉና በበዛብህ ታሪክ ታላቅነቱን የሚያውቀው የዲማ ትምህርት ቤት በአሳዛኝ ሁኔታ መገኘቱ ነው። ዕንባቸው መንታ ሆኖ እየወረደ የርሳቸውን ዘመን በትዝታ እያነፃፀሩ ያጫወቱኝ መ/ር ተወልደ ማርያም ነበሩ።

ከዚህ በፊት ለመምህራኑ ከትምህርት ሚኒስቴር 50 ብር ደመወዝ ነበራቸው። ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ግን ይህችው ገንዘብ ሆና ተቋረጠችባቸው። መምህራኑ መሬት አልባ በመሆናቸው ያለ መተዳደሪያ መኖር አልቻሉም። ለብዙ ጊዜ በትዕግሥት ቢጠባበቁም ዘወር ብሎ የሚጠይቃቸው አላገኙም። እኔ በቦታው በነበርኩኝ ጊዜም የመጽሐፍና የቅኔው መምህር «አቤት» ሊሉ አገር ጥለው ወንበር አጥፈው አዲስ አበባ መጥተዋል።

ያነጋገርኳቸው ተማሪዎችም አዝነው ተስፋ ቆርጠዋል። የቀሩት መምህራንም ቢሆኑ የረዳት ያለህ እያሉ ነው።

የዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳም የስድስት መቶ ዓመታት የታሪክ ቅርስ ማኅደር ነው። ከነገሥታት የተበረከቱ፣ ከየቦታው የተሰባሰቡ፣ የገዳሙ አበው መንፈሳዊ ጥበብ ውጤቶች የሆኑ ብርቅዬ ንዋየ ቅድሳትና ቅርሶች ይገኛሉ። የሚያሳዝነው ግን የዚያ ሁሉ ሀብት ጠባቂ የሆኑት አባት ትሰጣቸው የነበረ መተዳደሪያ 30 ብር ታግዳባቸው ባዶ መቅረታቸው ነው።

እዚህ አዲስ አበባ ከተመለስኩ በኋላ የሀገረ ስብከቱን ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ዘካርያስን ስለ ሁኔታው አነጋግሬያቸው ነበር። ብፁዕ አባታችንም ችግሩን ከቦታው ድረስ በመሄድ መመልከታቸውንና የበኩላቸውን ርዳታ ማድረጋቸውን ነግረውኛል። በሀገረ ስብከት ደረጃም አንድ ኮሚቴ ተቋቁሞ እኒህን መሰል ገዳማት



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

እንዴት እንደሚረዱ እየተጠና ነው ብለውኛል።

ይህንኑ ጥያቄ ለሰበካ ጉባዔ ማደራጃ መምሪያ ኃላፊ ለሊቀ ጉባዔ አበራ በቀለ ሳቀርብ ደግሞ ለአብነት መምህራን (በተለይም ለታላላቅ ትምህርት ቤቶች) የገንዘብ ድጐማ የተወሰነ መሆኑንና በሰበካ ጉባዔ መንፈሳዊ አስተዳደር ጠቅላላ ስብሰባ ከተደረገ ጊዜ ሁሉ የተመደበው ገንዘብ በሥራ መዋሉን ሪፖርት ሲደረ ግልኝ ቆይቷል ብለውኛል።

በዚህም ተባለ በዚያ ዛሬ በአፋጣኝ ተግባራዊ የሆነውን ርምጃ ተወስዶ ታላቁ ትምህርት ቤት ወደ ቀድሞ ደረጃው ካልተመለሰ የዲማን ትምህርት ቤት ታሪክ የምናገኘው በ«ፍቅር እስከ መቃብር» መጽሐፍ ላይ ብቻ ይሆናል ብዬ እሠጋለሁ። ቀጥየ ገዳሙን መጐብኘት ጀመርኩ። ገዳሙ የሚገኘው ከቤተክርስቲያኑ በስተ ሰሜን ሲሆን ጥቂት ጐጆ ቤቶችና የፈራረሱ ቆርቆሮ ቤቶች ይገኙበታል። በውስጡ 300 የሚያ ህሉ መነኮሳት ይተዳደራሉ። ይህኛው ደግሞ የሚያሳዝን ብቻ ሳይሆን የሚያስለቅስም ነው። ዕንባ የለም እንጂ።

ገዳሙ ርስት አልባ ሆኖአል። ያለችው የበሬ ግንባር የምታክል መሬት ናት። ለገዳሙ መነኮሳት በዓመት የሚበቃ እህል ቀርቶ ለዓይን ማረፊያ የሚሆን በቂ ምርት የለውም። በዚህ የተነሣ መነኮሳቱን የረሃብ አለንጋ ይገርፋቸዋል። ጠያቂ የላቸውም።

የዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በአቡነ ተክለሃይማኖት ብርታት በሕዝቡ ትብብር ሊታደስ ቢችልም የዕቃ ቤቱ አቀማመጥ ግን መስተካከል ገና ይገባዋል። ጠባብ በመሆኑ ዕቃዎች ይደራረባሉ። ይህ ደግሞ በቅርሶችና በንዋየ ቅድሳት ላይ ጉዳት ያስከትላል።

ዲማ ከማለዳው 1.30 እስከ 8:00 ጐበኘሁት። ወደ ዋሻው ውስጥ ከመነኮሳቱ በቀር ሌላ መግባት ስለማይችል የማየቱ ዕድል አልገጠመኝም። ገዳሙን ለቅቄ አቀበቱን ተያያዝኩት። ስመጣ አንድ ሰዓት የፈጀው መንገድ ስመለስ አጭር ሆነ። እንግዲህ ጉዞው ወደ ደብረ ወርቅ ነው። ቸር ያገናኘን። ✣

# ቅድስት እንባ መሪና

በእስክንድርያ አጠገብ ወደሚገኘው አስቄጥስ ገዳም እንባ መሪና የተባለውን ወጣት ልጁን ያስከተለ አባት ይህቺን ዓለም ትቶ መግባቱ የገዳሙን አበው ሁሉ ያስገረማቸው ነገር ነበር። ሚስቱ ከሞተች ብዙ ዓመት አልፎአታል። ልጁን ለብቻው ሲያሳድግ ከኖረ በኋላ ዛሬ ግን ቆረጠ። ልጁም ተከተለው እናም ተያይዘው ወደ ገዳመ አስቄጥስ ገቡ።

እንባ መሪና ወደ ገዳሙ ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ መነኮሳቱን በቅንነትና በትህትና ያለ ድካምና ያለመሰልቸት እየታዘዘ ያገለግላቸው ነበር። አባቱም ለ10 ዓመታት አብሮት ከቆየ በኋላ ዐረፈ። የገዳሙ አበምኔትም የእንባ መሪናን ደግነት አይቶ ስላስደሰተው አመነኮ ሰውና አባ እንባ መሪና ተባለ። እንባ መሪና ሠርቶ የማይደክመው፤ ዘወትር ለተጋድሎ የተጋ፤ ቅንና ታዛዥ ድምፅ ቀጭን መነኩሴ ነበር።

የእንባ መሪና መንፈሳዊ ተጋድሎው እን ደታላላቆቹ መነኮሳት በመ ሆኑ ድምፁ የቀጠ ነው ከጾም ከጸሎት ብዛት ነው እየተባለ ይነገራል።

አንድ ቀን እንባ መሪናና ሌሎች መነኮሳት የገዳሙን ግብር ለመሰብሰብ በአካባቢው ወዳለ መንደር ተልከው ሄዱ። የገዳሙን መሬት ከሚ ያርሱት ባላገሮች መካከልም አንዱ መነኮሳቱን በእንግድነት ተቀብሎ አሳደራቸው።

በዚያች ሌሊት አንድ ጐልማሳ ወደባላገሩ ቤት መጥቶ ከሴት ልጁ ጋር ሲጫወት አምሽቶ ንጽሕናዋን አጉድፎ በሌሊት ወጣ። እነ አባ እንባ መሪና ወደ ገዳማቸው ከተመለሱ ከአያሌ ጊዜያት በኋላ የልጅቱ ፅንስ እየታወቀ መጣ። ያም ጐልማሳ «ያስረገዘኝ አባ እንባ መሪና የተባለ ቀይ ወጣት መነኩሴ ነው ብለሽ ተናገሪ» ብሎ ስለመከራት ለአባትዋ የሆነውን ሁሉ ነገረችው።

አባትዋም «ወርቅ ላበደረ ጠጠር» እያለ በንዴት ወደገዳሙ በመሄድ ለአበምኔቱ ይኸን አሳዛኝ ታሪክ አረዳው። አበምኔቱ አላመነም። እንባ መሪናም ተጠርቶ መጣ። «ግብር ለመሰ ብሰብ በሄዳችሁ ጊዜ በዚህ ሰውዬ ቤት ስታ ድሩ ልጁን ደፍረሃል፤ ይህንንም ልጅቷ ተናግ ራብሃለች» አለና በጩኸት ተናገረው። እንባ መሪናም «አዎን አጥፍቼአለሁ ይቅርታ ይደረ ግልኝ» ብሎ ከእግራቸው ሥር ተደፍቶ አለቀሰ።

የገዳሙ አበምኔት «ገዳማችንን አዋርደሃል አሁን ከገዳሙ ለቀህ በቶሎ ውጣ፤ ነገር ግን ጥፋትህን አምነህ ይቅርታ ጠይቀሃልና ከገዳሙ ውጭ ቤት ተሠርቶልህ በዚያ ሆነህ ንስሐህን ትቀበላለህ የተወለደ ውንም ልጅ ታሳድጋለህ» ብሎ አዘዘው።

አባ እንባ መሪና ከገዳሙ ውጭ ቤት ተሠርቶለት ወጣ። ልጅቱም በወለደች ጊዜ ተቀብሎ ማሳደግ ጀመረ። ከብት ወደሚያ ግዱት ሰዎች እየሄደ ወተት እየለመነ እያጠጣው፤ በገዳሙ ክልል ለሚሠሩ ቤቶች እንጨት እያቀረበ፤ ጭቃ እየረገጠ የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ በማግኘት በትዕግሥት ጊዜውን ገፋው።

ለብዙ ዓመታት ልጁን እያሳደገ ከኖረ በኋላ በጠና ደዌ ታመመ። ዞር ብሎ የጠየቀው አልነበረም። በኃጢአቱ የመጣበት ዕዳ ነው እያሉ መነኮሳቱም ጠሉት። በታመመ በ3ኛው ቀን ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ።

ማታ የገዳሙ አበምኔት ከበአቱ ሆኖ አሻግሮ ሲመለከት በእንባ መሪና ጐጆ የብርሃን ዓምድ ተተክሎ ጫፉም እስከሰማይ ደርሶ ተመለከተ። በዚያም ብርሃን ውስጥ ነጫጭ የለበሱ መላእክት በአክናፈ እሳት ሲወጡ ሲወርዱ አየ።

በነገሩ ተገርሞ እስኪነጋ ጓጉቶ በጠዋት ገሠገሠ። እንባ መሪና አርፎአል። የገዳሙ መነኮሳትም ተጠርተው ሊገንዙት ተሰባሰቡ። ልብሰ ምንኩስናውንም ሲያወልቁለት ሁሉም መብረቅ እንደመታቸው ሁሉ ደርቀው ቀሩ። ከብዙ ድንጋጤ በኋላ መለስ ሲሉ «ወየው አባታችን ጉድ ሆንን» እያሉ እያለቀሱ ከጐጆው ወጡ። አበምኔቱም ደንግጦ ወደ ጐጆው ሮጠ። አባ እንባ መሪና ለካስ ሴት ኑሮአል! የአበምኔቱ ለቅሶና ጩኸት ከሁሉም በለጠ። ወዲያውም ያንን ባላገር አስጠርቶ «ምነው ምነው እንዲህ አስፈረድከብን» ይለው ጀመር። እኒያ ጐልማሳና ኮረዳም እየተላቀሱ ወደገዳሙ መጡና «እባካችሁ የዚህ ሁሉ ኃጢአት መነሻዎቹ እኛ ነንና እግዚአብሔር ይቅር እንዲለን ጸልዩልን ይቅር በሉን» እያሉ ጮኹ።

በዚያ ገዳም የበቁ አበው ታሪኳን ለሁሉም መሠከሩ። አባትዋ ለአቅመ ሔዋን እስከምትደርስ ካሳደጋት በኋላ ድሮአት ገዳም ሊገባ ፈለገ። እርስዋ ግን «የራስህን ነፍስ ስታድን እኔን ለዓለም ትተኸኝ ትሄዳለህን?» ብላ ተቃወመችው። እርሱም «እኔ የምገባው ወደ ወንዶች ገዳም በመሆኑ እንዴት ላድርግሽ?» አላት። «ወንድ መስዬ እገባለሁ» ብላ ቆራጥ ሀሳብዋን ስለገለጠችለት አስከትሏት ገባ።

ገዳማውያኑ ሁሉ ያን ሁሉ ዘመን በዓላማዋ ቆርጣ በትዕግሥት ጸንታ መከራን ተቀብላ ስድቡን ግልምጫ ውን ችላ ለዚህ ክብር መብቃትዋን ሲያዩ ራሳቸውን ወቀሱ «እንባ መሪና ይቅር በይን» እያሉ በአስከሬኗ ዙሪያ ይወድቁ ይነሡ ጀመር። እኛ ያደረግ ነውን በምንዋሽበት ዓለም ያልሠራ ችውን የሌላውን ኃጢያት ተሸክማ ዲያብሎ ስን በትዕግሥት ድል አደረገችው።

ነሐሴ 5 ቀን ባረፈችበት ዕለት በገዳሙ ውስጥ በክብር ተቀበረች። ላመነችበት ጸናች፤ ለሠናችበት ታገሠች፤ ለትዕግሥትዋ ተጋደ ለች፤ በተጋድሎዋ አሸነፈች። ረድኤትዋና በረከትዋ ከሁላችን ጋር ይሁን። እርስዋን ያሠና እግዚአብሔር እኛንም ያሥናን። አሜን። ✣



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ

ልብሴን እያስወለቀ ቤቴን አስትቶ እያስፈተለከ እያስጮኸ እያስጎራ ለብዙ ቀናት መከራ አሳየኝ።

አንድ ቀን የእኔ የማይመስል ግን የእኔ የሆነ ቃል ከአንደበቴ ወጣ «እሩፋኤል ውሰዱኝ ጸበል አስጠምቁኝ» በማለት ጮህኩና ወዲያው ልሳኔ ተዘጋ ዲዳ ሆንኩ። የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶችም የተናገርኩትን ሲሰሙ እንዳላመልጥ እጅ እግሬን አሥረው ወደ እሩፋኤል ቤተክርስቲያን ወሰዱኝ።

ጅግላሌ ሞኝ አልነበረም እስከ ቤተክርስቲያኑ በር ዝም አለና ቅጽረ ግቢው ሲደርስ አስፈተለከኝ፤ ማን ጀግና ሊይዘኝ፥ ግን ከእግዚአብሔር ማምለጥ አይቻልም። ያላሰብኩት መንገደኛ ሰው ከየት መጣ ሳልለው አፈፍ አደረገኝ ሲከተሉኝም በፍጥነት ደረሱብኝና ተረባርበው ወደ ቤተክርስቲያን በመውሰድ አስጠመቁኝ በዚያን እለት አጥማቂው ካህን አንድ ምክር ለእናቴ ለገሷት አዲስ አበባ ኪዳነ ምሕረት ቤተክርስቲያን ወስዳችሁ አስጠምቁት በማለት።

በጥቅምት ወር ነው ወደ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተክርስቲያን የሄድኩት፥ ጠበልተኞች ተከራይተው ከሚያድሩባቸው ቤቶች መካከል ተከራይተን ለአምስት ወራት ያኽል በትጋት ተጠመቅሁ። ጅግላሌ እስከ መጨረሻው ሰዓት መፈታተኑን አልተወኝም ነበር።

መጋቢት ሁለት ቀን ስጠመቅ መጮህ መለፍለፍ ጀመርኩ እሪታውን አቀለጥኩት ጅግላሌ አጓራ አጥማቂው ካህን በስመ ሥላሴ ሲገዝቱት ጾጥ አለ። አደብ ገዛ። ቀጥለው ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የሠራኝን፣ ያደረገኝን አስለፈለፉት በየመሐሉ «ተቃጠልኩ፣ ነደድኩ» ይላል።

«በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ስም ይገፃለሁ ካሁን በኋላ ብትደርስበት፣ የታሠርክ ሁን» ካህኑ መስቀሉን በግንባሬ ላይ አስቀምጠው ተናገሩት ያን ጊዜ ነው ከትከሻዬ ላይ እንደ ተነሣ ነገር ሲለቀኝና ቅልል ሲለኝ የታወቀኝ። ዙሪያዬን ካህኑና እናቴ ቆመዋል። ሌሎች ሰዎች ባሻገር ነው የሚታዩኝ። ነፃ ሆንኩኝ ጀግላሌ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከኔ ተላቀቀ መጋቢት ሁለት ቀን በእንጦጦ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ጠበል ከዚያ በኋላ ነው ታሪኬን እንደ አዲስ የሰማሁት አዲስ ሰው ሆኜም እንደ ሰው መኖር የጀመርኩት።

## የጅግላሌው ፈረስ

የመጨረሻው ክፍል

ጌታሁን ደበበ – ከደብረ ዘይት

ላለፈው ኑሮዬ ንስሐ በመግባት ወደገነቷ ቤቴ ወደቅድስት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተመለስኩ። ዛሬ ያንን ሁሉ መሰናክል ያሳለፈኝን እግዚአብሔርን እያመሰገንኩ በእምነቴ ጸንቼ እኖራለሁ። ዘወትር እማራለሁ። አስቀድሳለሁ። ዛሬ ሰው ሆኛለሁ። ሌሎችም ከዚሁ የመረረ ሕይወት እንዲላቀቁ ጸሎቴና ምኞቴ ነው።

ከአዘጋጁ – ዛሬም በባዕድ አምልኮ፣ በድያብሎስ አገዛዝ ተይዘው የሚሰቃዩ እጅግ ብዙ ናቸው። ለሁሉም እስከ ዛሬ ያቀረብነው የጅግላሌው ፈረስ ትልቅ ትምህርት ይሰጣል ብለን እናምናለን። ዲያብሎስ ያሰቃያል፣ ባርያው ያደርጋል፥ ከሰውነት ተራ ያወጣናል። ስለዚህም ከቀንበሩ ለመላቀቅ በእግዚአብሔር ቤት እንኑር፤ የርሱ መግቢያ የሆኑ በሮችን እንዝጋ። በርትዕት ሃይማኖታችን እንጽና።

በየአድባራቱና ገዳማቱ ያሉት ፀበላት ዛሬ ብዙዎችን ከዚህ መከራ እያላቀቁዋቸው ነውና ወደ ባለዛሩ፣ ጠንቋዩና ቃልቻው መሮጣችንን ትተን እግዚአብሔር ወዳዘጋጀልን የመዳን መንገድ እንምጣ።

ብዙ ሰዎች ዛር፣ ጨሌ፣ ቃልቻ ...ወዘተ ከመሳሰሉት የዲያብሎስ ወጥመዶች ለመላቀቅ ፍላጐት እንዳላቸው ሲገልጡ ይሰማሉ። ነገር ግን ይፈሩታል «ቢያመኝስ፣ ልጆቼን አንድ ነገር ቢያደርግብኝ ሀብቴ ቢቀነስ፣ ዕድሜዬ ቢያጥር...» እያሉ ይሠጋሉ። የረሱት ነገር ቢኖር እግዚአብሔር ከሁሉም በላይ ችግራችንን ሊፈታ የታሠርንበትን ሊበጣጥስ የሚችል ኃያል አምላክ መሆኑን ማመን ነው። በእምነት ወደርሱ እንቅረብ የዲያቢሎስ ወጥመድ ይበጣጠሳል። መጻጉዕን ያዳነ እኛንም ያድነናል። በንስሐ በቁርባን በቃለ ወንጌል ቤታችንን ካጸዳን ራሳችንንም የእግዚአብሔር መንፈስ ማደሪያ ካደረግ ነው ዲያብሎስ መግቢያ የለውም።

እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ? እኔም አሳርፋችኋለሁ ማቴ.11፥28።

እግዚአብሔር ከአምልኮ ባዕድ፣ ከርኩስ መንፈስ ቀንበር ያላቀን። ✣

አሜን

### ኃጢአት መሥራት

እግዚአብሔርን ክዶ ሰይጣንን፥
ሕይወትን ትቶ ሞትን፥
ገነትን ትቶ ሲኦልን፥
መንግሥተ ሰማያትን ጥሎ ገሃነምን፥
ብርሃንን ሸሽቶ ጨለማን፥
ልጅነትን ንቆ ባርነትን፥
ክብርን አቃሎ ውርደትን፥
ሐሴትን ጥሎ ሥቃይን፥
መላእክትን ክዶ አጋንንትን፥
ቅዱሳንን ትቶ ርኩሳንን፥
ከቀኝ ርቆ ግራን፥
ስንዴነትን ጥሎ እንክርዳድነትን፥
ምሕረትን ጠልቶ መዓትን መምረጥ ነው።



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# 2. ደስታና ዘፈን

ከግርማ ወ/ሩፋኤል

ዛሬ በዓለማችን እንደ ደስታ መግለጫነታቸውና የደስታ ምንጭነታቸው ከሚታወቁት ነገሮች መካከል ዘፈን አንዱ ነው። ከዚህም ሌላ ዘፈን ለብዙዎቹ ትልቅ የገቢ ማግኛና መተዳደሪያ ሆኗል። በዚህም የዕለት ጉሮሮውን ለማሸነፍ ከሚጥረው አንሥቶ በሀብቱ ብዛት በምድር ያለው የተንደላቀቀ ኑሮው ሰልችቶት በላይ በጠፈር ለመኖር እስከሚቃጣው ድረስ ይገኙበታል። በዚያም ሆነ በዚህ ዘፈንን የሚያዘወትሩት ሁሉ ደስታን ለማግኘትና ለመዝናናት በማሰብ ነው። ስለዚህ ብዙዎች ደስ ባላቸው ቁጥር ይዘፍናሉ። በሠርግ ጊዜ ያዘፍናሉ፤ በትልልቅ ክብረ በዓላት ላይ ይዘፍናሉ። ወዳጅ ዘመዶቻቸው በሚመረቁበት ጊዜ ይዘፍናሉ። በተለይ በዘመናችን እየተስፋፋ የመጣው የዳንስና የሙዚቃ ቤቶች መብዛት ከዚሁ በዘፈን ደስታን ለማግኘትና ለመዝናናት ከማሰብ የተነሣ ነው። ታዲያ እንደዚህ ብዙዎች በዕለት ተዕለት ኑሮአቸው የሚጠቀሙበትና የደስታ ምንጫችን ነው የሚሉት ዘፈን በክርስትናው ሕይወት እንዴት ይታያል?

ክርስቲያኖች እንደሌላው ኅብረተሰብ ሁሉ በማኅበራዊ ኑሮአችን ደስታም ሆነ ኀዘን ይገጥመናል። ነገር ግን የደስታችንም ሆነ የኀዘን መግለጫችን ተስፋ እንደሌላቸው ሃይማኖት የለሾች ሊሆን አይገባውም። በተለይም ስንደሰት ሰዎችን በትዕቢት የሚሞላውን ዝሙትን የሚቀሰቅሰውንና ራስንና ፈጣሪን የሚያስረሳውን ዓይነት ዘፈን አንጠቀምም። ስለዚህም ስንደሰት እንዘምራለን ስናዝንም እንጸልያለን። (ያዕቆ.5÷ 13)። በመሆኑም ሥጋን ብቻ ለማስደሰት የሚደረገውን ዘፈንና ዘፋኝነት በክርስትና ሕይወታችን ውስጥ ዘልቆ እንዲገባ አንፈቅድም። ምክንያቱም:-

ሀ. ዘፈን ወደ ኃጢአት የሚመራ የኃጢአት ምንጭ ነውና፤ የምንውልበት ሥፍራ፣ ዘወትር የምንመለከተውና የምንሰማው ነገር ለክርስቲያናዊ ሕይወታችን መድከምና መበርታት ወሳኝ ነው። የያዕቆብ ልጅ ዲና ክብርዋን ለማጣት የበቃችው ከሃየማኖት የለሽ አረማውያን ጋር በመዋልዋ ነበር ዘፍ.34÷1። ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊትም ይህንን አስመልክቶ «ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ በኃጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ፤ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ።» መዝ.1÷1 በማለት የምንውልበትን አካባቢ ተጽእኖ ተናግሮአል። በተለይም ለሰው ልጅ በክርስቲያናዊ ሕይወቱ እንዳይጸና እንቅፋት የሚሆኑበት ነገሮች በጣም እየጨመሩ ባሉበት ዘመናችን በኃጢአት ማቅቆ ከማልቀስ አስቀድሞ መጠንቀቅና ራስን ከክፋት መንገድ ማራቅ ይገባል።

ኃጢአት በሰዎች ልቡና ለመንገሥ ሲመጣ ከሚያቀርብልን እጅ መንሻዎች አንዱ ዘፈን ነው። በመጀመሪያ ዘፈን የሚዘወተርባቸው ሥፍራዎች በተለይም ዳንስ ቤቶች ሰዎችን ወደ ዝሙት ለመገፋፋት አመቺ ሆነው የተዘጋጁ ናቸው። አንድ ሰው በዘፈን በሚሰክርበት ሰዓት ፈጣሪውን ከመርሳትም አልፎ ኃጢአትንና ጽድቅን ለመለየት ይቸገራል። ለዚህ ነው በዳንስ ቤቶች አካባቢ የዕፅ ሱሰኞች የሚበዙት፥ ዝሙትና ስካር ታላላቅ ወንጀሎችም የሚፈጽሙት፤ ለመደሰት ሄደው ኃጢአትን ሸምተው የሚመለሱት።

ንጉሥ ሄሮድስ የልደት በዓሉን በአከበረበት ዕለት ወለተ ሄሮድያዳ (የሄሮድያዳ ልጅ) እየዘፈነች አስደሰተችው። እሱም በጣም ተደስቶ ስለነበር ምን እንደሚያደርግላት ሲጠይቃት እናቷን አማክራ ዮሐንስን ገድሎ አንገቱን እንዲሰጣት ጠየቀችው። ሄሮድስ ይህ ነገር ኃጢአት መሆኑን ቢያውቅም በዚያን ሰዓት በነበረው ፈንጠዝያ ፈጣሪውን ረስቶ ፈሪሃ እግዚአብሔርም ከልቡናው ጠፍቶ ስለነበር ዮሐንስን አስገደለ። ሥጋውን አስደስቶ ኃጢአትን ፈጸመ። ሰማያዊውን ክብር አጣ። ሕዝበ እግዚአብሔር የተባሉ እሥራኤል እግዚአብሔርን ክደው አምልኮ ጣዖትን ሲጀምሩ በእግዚአብሔር ላይ ለማመፃቸው አንዱ መግለጫ የነበረው ዘፈናቸው ነበር ዘፀ.32÷6።

ከዚህም ሌላ ዳንስ ቤትም ሳይኬድ እቤት ተቀምጦ ዘፈን የሚደመጥበት ሰዓት የዝሙት መንፈስን በኅሊና ሊቀርፅ ይችላል። በተለይም ዛሬ በሀገራችን የሚዘፈኑት ዘፈኖች የግጥም ይዘታቸው በቀጥታ ዝሙትን የሚቀሰቅሱ የዝሙት ማስታወቂያዎች እየሆኑ መጥተዋል። በዚህም የማያውቁትንና ገና ለጋ የሆኑትን ሕፃናትንና ወጣቶችን ሳይቀር ወደ ዝሙት ይገፋፋሉ።

ለ. ዘፈንና ዘፋኝነት የሥጋ ፍሬ ነው

ለገላትያ ሰዎች በተላከው የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ከተጠቀሱት የሥጋ ፍሬዎች መካከል ዘፋኝነት ይገኝበታል (ገላ.5÷16–22) «...እንደነዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።» ገላ.5÷21። እንዲሁም አስቀድሞ «ልጆቻቸውም ይዘፍናሉ...ዕድሜአቸውንም በተድላ ይፈጽማሉ። ድንገትም ወደ ሲኦል ይወርዳሉ።» ኢዮብ.21÷12–13።

ዛሬ የዓለም ሕዝብ የሚያዘወትረውን ዘፈን ሐዋርያት በትምህርታቸው ደጋግመውና አጥብቀው ተቃውመውታል። ‹እንግዲህ የጨለማውን ሥራ አውጥተን የብርሃንን ጋሻጦር እንልበስ፤ ለቀን እንደሚሆን በአግባብ እንመላለስ በዘፈንና በስካር አይሁን፣ በዝሙትና በመዳራት አይሁን፣ በክርክርና በቅናት አይሁን። ነገር ግን ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱ፣ ምኞቱንም እንዲፈጽም ለሥጋ አታስቡ።» ሮሜ.13÷13–14። እነዚህ ሐዋርያት በዚያ በመከራ ዘመን ያ ሁሉ ሥቃይና መከራ ሲደርስባቸው በደስታ ይቀበሉትና እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር። ደስታቸው ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው ደስታ ስለሆነ በመከራ ጊዜ ሁሉ አልጠፋም። ዮሐ.16÷22 ታዲያ እነዚህ ቅዱሳን አባቶቻችን ሐዋርያት የሚቃወሙትንና ሥጋን ብቻ አስደስቶ ሰማያዊውን ክብር የሚያሳጣንን ዓይነት ዘፈን ለመተው የምን ቸገረው ለምን ይሆን? በዘመናችንም ትልቁ ሰማዕትነት የሥጋን ፍላጐት ገዝቶ ራስን ለሰማያዊ ክብር ማብቃት ነው። ስለዚህ ክርስቲያኖች ሆይ ለጊዜያዊ ደስታ ብለን ሞትን ወደ ራሳችን ከመጥራት ሥጋችንን በመግዛት ከዘፈን መዝሙርን ልንመርጥ ይገባናል። ደስ የሚለው ማንም ቢኖር እርሱ ይዘምር። ያዕቆ.5÷13። ነውና! ✣



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# የጥያቄያዎቻችሁ መልስ

**• ስለ እመቤታችን ዘለዓለማዊ ድንግልና ማቴ.1፥23፤ 13፥33 ካሉት ጥቅሶች አንፃር ሠፋ አድርጋችሁ ብታብራሩልኝ።**

ከመጽሔታችሁ አንባብያን አንዱ

መልስ:- «እጮኛውንም ማርያምን ወሰደ የበኩር ልጅዋንም እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም» ማቴ.1፥25 ጥቅስ ላይ «እጮኛ፣ በኩር፣ እስክትወልድ ድረስ» የሚሉትን ቃላት በስፋትና በዝርዝር እንደሚከተለው እናያቸዋለን።

**• እመቤታችን ለዮሴፍ ስለምን ታጨች?**

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለዮሴፍ መታጨቷ በባልና ሚስት ግብር ለመገናኘት አይደለም። በእጮኝነት ስም ለዮሴፍ መሰጠትዋ ስለተለያዩ ምክንያቶች ነው። የመጀመሪያው ምክንያት ከእርሷ የሚወለደው ክርስቶስ ከይሁዳ ከዳዊት ወገን እንደሆነ በትንቢት ተነግሯል። ኢሳ.11፥1፣10። ነገር ግን በምድራዊ ልደት ከእናት ብቻ ተወለደ እንጂ አባት ስለሌለው ዮሴፍ ከዳዊት ዘር ስለሆነ ክርስቶስ እናቱ በእጮኝነት ስም በተሰጠችው በዮሴፍ የዳዊት ልጅ ተብሎ እንዲቆጠር ነው። ምነው በእናቱ የዳዊት ልጅ አይደለም ወይ ለምን በዚያ አልተቆጠረለትም? ቢባል አይሁድ በባሕላቸው ሴትን ከትውልድ ቁጥር አግብተው አይቆጥሩምና የናቱን ከትውልድ መቆጠር ስለማይቀበሉ ነው። በዚህም ምክንያት ወንጌላዊው ማቴዎስ የክርስቶስን ትውልድ ሲቆጥር በዮሴፍ በኩል ነው። ማቴ.1፥16። ይህም የሆነው እመቤታችንና አረጋዊው ዮሴፍ ዘመዳሞች በመሆናቸው ነው በማቴ.1፥15። «አልዓዛርም ማታንን ወለደ» ይላል ዳሩ ግን አልዓዛር የወለደው ማታንን ብቻ ሳይሆን ቅስራንም ወልዷል። ማታን ያዕቆብን ሲወልድ ቅስራ ደግሞ ኢያቄምን ወለደ። ያዕቆብ ዮሴፍን ሲወልድ ኢያቄም እመቤታችንን ወለደ። ስለዚህ የእመቤታችንና የሽማግሌው የዮሴፍ ዝምድና የቅርብ መሆኑን በዚህ እንረዳለን። በዚህም የተነሣ ወንጌላውያን የክርስቶስን ትውልድ ሲቆጥሩ በዮሴፍ በኩል መቁጠራቸው ይህን ስለሚያውቁ ነው።

ክርስቲያኖች ግን ክርስቶስን የዳዊት ልጅ የምንለው በአንጻረ ዮሴፍ ሳይሆን ከዳዊት ወገን በተወለደች በእውነተኛዋ እናቱ በቅድስት ድንግል ማርያም ነው። መዝ.44፥10።

ሁለተኛው ምክንያት ሴት ልጅ ናትና በአይሁድ ዘንድ ከሚመጣባት ፈተና በእጮኛ ስም እንዲጠብቃት ነው። ሦስተኛው ክርስቶስ ያለወንድ ዘር መወለዱን አይተው እናቱ ድንግል ማርያምን ከሰማይ የመጣች ኃይል ናት እንጂ የአዳም ዘር (ሰው) አይደለችም። ክርስቶስም ከመልአክ የተገኘ መልአክ ነው የሚሉ መናፍቃን እንደሚነሡ ያውቃልና ከሰማይ የመጣች ኃይል ብትሆንማ ለዮሴፍ ትታጭ ነበርን? ብሎ ነገራቸው ለማፍረስ እንዲመች አዳማዊት መሆንዋን ለማረጋገጥ በእጮኛ ስም ለዮሴፍ እንድትሰጥ ተደረገ። መልአክ ብትሆንማ ኖሮ ባልታጨች ነበር።

መታጨቷ ስለዚህ ምክንያት እንደሆነም አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ገልጾታል። «ስሙ ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደ ታጨች ድንግል በማለቱ በእውነት ሴት (ሰው) እንደሆነች አስረድቶናል ብሏል። (ሃይማኖት አበው)

አራተኛ ምክንያት አገልጋይዋ ተላኪዋ እንዲሆን ነው። ስትሰደድ አብሮ በመሰደድ ተከታይ ሆኖ እንዲረዳት።

አምስተኛው ምክንያት በድንጋይ ከመደብደብ ሊያድናት ለዮሴፍ በእጮኝነት ስም እንድትሰጥ አደረገ። ምክንያቱም በኦሪት ዘኁልቁ 5፥19 በተጠቀሰው መሠረት አንዲት ሴት ከባልዋ ሌላ ፀንሳ ብትገኝ ማየዘለፋ ያጠጥዋት ነበር። እንዲሁም አንዲት ሴት ባል ሳታገባ ብትጸንስ በሙሴ ሕግ መሠረት ደብድበው ይገድሉአት ነበር። ስለዚህ እመቤታችን ለዮሴፍ ሳትታጭ ቀርታ በቤተ መቅደስ እያለች ፀንሳ ቢሆን በአይሁድ ዘንድ ብዙ መንገላታት በገጠማት ነበር።

ከላይ በገለጽነው መሠረት ምንም እንኳን አይሁድ እመቤታችን ድንግል ማርያምን ለዮሴፍ በእጮኝነት ቢሰጡት እግዚአብሔር ባወቀ ግን እንዲጠብቃት እንዲያገለግላት ነው እንጂ ለሚስትነት አይደለም።

## በኩር ለሚለው

እዚህ ላይ ልንገነዘበው የሚገባን አንድ ነገር «የበኩር ልጅ» የሚለው ቃል የግድ ተከታይ ልጅ መኖሩን የሚያመለክት አለመሆኑን ነው። እግዚአብሔር ወልድ በቀዳሚው ልደቱ ተቀዳሚና ተከታይ እንደ ሌለው ሁሉ በደኅራዊ ልደቱም ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ እንደምናገኘው ጌታ በኩር ተብሏል። ለዚሁም የሚከተሉትን ማስረጃዎች እንመልከት።

ዕብ.1፥6 «ዳግመኛም በኩርን ወደ ዓለም በሰደደው ጊዜ» በኩር የተባለው የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

በዚህ ላይ በኩር የሚለው ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው መሆኑን የሚገልጽ እንደሆነ የተረጋገጠ ነው። ያለበለዚያ ዮሐንስ «በአባቱ እቅፍ ያለ አንድያ ልጁ ብሎ» ባልመሰከረ ነበር። ዮሐ.1፥18።

ቆላ.1፥15። «ድኅነት ያገኘንበት ኃጢአታችንም የተሠረየበት ይኸው



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

የማይመረመር እግዚአብሔርን የሚመስለው በፍጥረቱ ሁሉ ላይ የበኩር ልጅ ነው»

በዚህም ላይ ጌታ የአብ የበኩር ልጁ መሆኑ ተገልጾአል። ታዲያ አብ ከወልድ ሌላ የወለደው አለ ማለት ነው? አይደለም! ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው የአብ የባሕርይ ልጁ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ስለዚህ «የበኩር ልጁ» ሲል ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው ለማለት ነው። እንደዚህም ሁሉ በቀዳማዊ ልደቱ ተቀዳሚ ተከታይ እንደሌለው ሁሉ በሁለተኛ ልደቱ ከእመቤታችን በሥጋ በተወለደ ጊዜ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው መሆኑን የሚገልጽ ነው።

ከላይ ባየነውና በተረዳነው መልኩ በኩር የሚለው አነጋገር ለጌታ ሲነገር ለየት ያለ ትርጉምና መልእክት ያለው መሆኑን የተገነዘብን ሲሆን በተለምዶ የበኩር ልጅ የሚባሉ የግድ ተከታይ ያላቸው መሆን እንዳለባቸው የሚያስቡ ሰዎች እጅግ መሳሳታቸውን ሊያውቁት ይገባል። እግዚአብሔር ለሙሴ ‹በእስራኤል ልጆች ዘንድ ከሰውም ከእንስሳም ማኅፀንን የሚከፍት በኩር ሁሉ ለእኔ ቀድስልኝ የእኔ ነው› ብሎታል ዘጸ.13 ቁ.192።

በዚህ ቦታ እንደተገለጠው በኩር የሚባሉት ለመጀመሪያ ጊዜ ከእናታቸው ማኅፀን የወጡ መሆናቸውን እንጂ የግዴታ ተከታይ ሊኖራቸው እንደሚገባ አይገልጽም። ለምሳሌ አንድ ልጅ ብቻ የወለደች እናት የልጅዋ ለእርሷ የበኩር ልጅዋ አይባልምን? አንድም ብቻ ቢሆን የእናቱን ማኅፀን ለመጀመሪያ ጊዜ ከፍቶ የወጣ በመሆኑ ተከታይ ሳይኖረው በኩር ይባላል።

«እስከትወልድ ድረስ አላወቃትም»

ለሚለው እንደ ተቃዋሚዎቹ አነጋገር «እስከ» የሚለው ቃል ፍጻሜ ላለው ነገር ብቻ የሚገባ አድርገው ወስደው «እስከትወልድ ድረስ አላወቃትም» በማለት ጌታን ከወለደች በኋላ በግብር እንዳወቃት አድርገው ይናገራሉ።

ሎቱ ስብሐት! በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የ«እስከ»ን አገባብ ስንመለከት ብዙውን ጊዜ ፍጻሜ ለሌለውም ነገር ተገልጾ እናገኘዋለን። ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን እንጥቀስ።

1. «የሳኦል ልጅ ሚልኮል እስከ ሞተችበት ቀን ድረስ ልጅ አልወለደችም» ይላል 2ሳሙ. 6–23። እስከ የሚለው በመጠቀሱ ከሞተች በኋላ ወለደች ለማለት ተፈልጐ አይደለም። ሰው ከሞተ በኋላ እንደማይወልድ የታወቀ ነው ማቴ.22፥30። ጸሐፊው ሊናገርና ሊገልጥ የፈለገው እስከ መጨረሻው ልጅ ሳትወልድ እንደ ሞተች ለማሳወቅ ነው። ምንም እንኳን የፀሐፊው ዋና ዓላማ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ያለ ወንድ ዘር መወለድ ለማሳየት ቢሆንም እንደዚሁም ሁሉ ዮሴፍ እመቤታችን የበኩር ልጅዋን እስከትወልድ ድረስ አላወቃትም በማለት እስከመጨረሻው በሴትና በወንድ ግብር እንዳላወቃትም ያስረዳል።

2. «ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ።» ሮሜ.5፥14። ይላል ከሙሴ በኋላ የሞት ንግሥና ቀረ ማለቱ ነው? «ሞት ሆይ መውጊያህ የት አለ» የተባለው ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጐ ከተነሣ በኋላ ነው።

3. «ጌታ ጌታዬን ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው» መዝ. 109፥1፤ ማቴ.22፥44 ይላል። እንዲህ ሲባል ጠላቶቼን ካሸነፈ በኋላ በቀኝ መቀመጡ ቀረ ማለት ነው? እንዲህማ እንዳይባል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ጌታችን በመስቀሉ ድል የነሣ መሆኑን በቆላ.2፥14 ና 15 የገለጸ ሲሆን ቀዳሚ ሰማዕት እስጢፋኖስም ጌታ ሞትን ድል አድርጐ ከተነሣ በኋላ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ተቀምጦ አይቶታል የሐዋ.7፥55 ይህም ጠላቶቹን ድል ከነሣ በኋላ በመሆኑ ከላይ የተጠቀሰው «እስከ» ፍጻሜ የሌለው ነው።

4. «እነሆ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» በማለቱ ከዓለም ፍጻሜ በኋላ ከእነርሱ ይለያል ማለት ነው? አይደለም! አነጋገሩ እስከ ዘለዓለም ከእነርሱ ጋር የማይለይ መሆኑን ሲገልጽ ነው።

እንደዚሁም ሁሉ የሐዋርያውና የወንጌላዊው የማቴዎስ አነጋገርም ዮሴፍ እመቤታችንን በሴትና በወንድ ዓይነት ግንኙነት እስከ መጨረሻው እንዳላወቃት የሚገልጽ እንጂ እነርሱ እንዳሉት ሆኖ አናገኘውም።

በሌላም መልኩ ዮሴፍ እመቤታችንን በነቢያት ትንቢት የተነገረላት ድንግል የተባለችው እርስዋ መሆንዋን መጻሕፍት በኩር እያሉ የሚጠሩት ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው አንድያ ልጅዋን እስከትወልድ ድረስ ማንነትዋን አላወቀም፤ አልተረዳም ነበር። ስለዚህም ነበር በመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ በተገኘች ጊዜ በሥውር ሊተዋት ያሰበው። ማቴ.1፥19። ከእርሷ የሚወለደው ሁሉን ቻይ፣ የማይሳነው አምላክ፣ እግዚአብሔር ወልድ መሆኑን ቢያውቅ ኖሮ በሥውር ሊተዋት ባላሰበ ነበር።

ጌታን ከወለደች በኋላ ግን የአምላክ እናት መሆንዋን ነቢያት ሁሉ ትንቢት የተናገሩላት እርስዋ መሆንዋን ዐወቀ። ይህንን ለመግለጥ ነው ወንጌላዊው «የበኩር ልጅዋን እስከትወልድ ድረስ አላወቃትም» ብሎ የጻፈው።

ይቀጥላል

## ለምን ለጸሎቴ መልስ ከእግዚአብሔር አላገኘሁም?

- ጸሎትህ የቃላት ድርደራ እንጂ ልባዊ መሻት የሌለው ሆኖ ይሆናል።
- እግዚአብሔር ትዕግሥትን ሊያስተምርህ ፈልጎ ይሆናል።
- አባታችን ቅዱስ ያዕቆብ እስከ ንጋት ድረስ ታገሠ። ዘፍ.32፥24።
- ጸሎትህ ያለ ፍጹም እምነት ተደርጎ ይሆናል።
- አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔርን መዘግየት ጥቅሙን የምናውቀው ቆይተን ነው። ምክንያቱም ያለድካም ያገኘኸውን ነገር ሳትጨነቅ ታስወስደዋለህና ቅዱስ ባስልዮስ።
- ምናልባት በአፍ የምትናገረውና በልብህ የምታስበው ተለያይቶ ይሆናል።
- የለመንከው የማይበጅህ ነገር ሆኖ አባትህ እንዳትጎዳበት አስቦልህ ይሆናል።



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

# ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ

በአለፈው እትማችን ቅዱሳት መጻሕፍት ያሉበትን ጠቅላላ ሁኔታ ተመልክተናል። ዛሬ ደግሞ ወደ አከፋፈላቸውና ታሪካቸው እንመለሳለን።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳት መጻሕፍት በዚህ ጥናት መሠረት በአሥር ክፍላት ሊከፈሉ ይችላሉ።

1. <u>መጽሐፍ ቅዱስ</u>:- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በመጻሕፍት ቀኖናዋ መሠረት 46 የብሉይ ኪዳን 35 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት አሏት።

2. <u>የትርጓሜ መጻሕፍት</u> እነዚህ መጻሕፍት የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትና ሌሎች እንደ ቅዳሴ፣ ውዳሴ ማርያም፣ ፍትሐ ነገሥት፣ ወዘተ ያሉት መጻሕፍት በአንድም የትርጓሜ ስልት የተተረጐሙባቸው ናቸው።

3. <u>የነገረ ሃይማኖት መጻሕፍት</u> እነዚህ መጻሕፍት ርትዕት ስለሆነችው ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን ለማስረዳት ቅዱሳን አበው የጻፏቸው ናቸው። ይዘታቸው ሃይማኖታዊ ነው (አምስቱ አዕማደ ምሥጢራት፣ ነገረ ማርያም፣ ነገረ ቅዱሳን ...ወዘተ) ለምሳሌ፥ ሃይማኖተ አበው፣ መጽሐፈ ምሥጢር፣ ክብረ ቅዱሳን፣ መጽሐፈ ኪዳን፣ አንቀጸ አሚን፣ ውዳሴ መስቀል ወዘተ።

4. <u>የጸሎት መጻሕፍት</u> እነዚህ መጻሕፍት ለማኅበርና ለግል ጸሎት የሚያገለግሉ ናቸው። አጠቃቀማቸውም በሁለት ወገን ነው።

ሀ. <u>ለዘወትር እንደ ውዳሴ ማርያም</u>፣ ውዳሴ አምላክ፣ መልክአ ጊዮርጊስ፣ ሰዓታት አንቀጸ ብርሃን፣ መጽሐፈ ኪዳን፣ ያሉ በካህናቱና በምእመናኑ ዘንድ በየጊዜው በየሰዓቱ የሚጸለዩ።

ለ. ለተለየ አገልግሎት እነዚህ የጸሎት መጻሕፍት በራሳቸው በሁለት ይከፈላሉ።

በምሥጢራት መፈጸም ጊዜ የሚያገለግሉ ቅዳሴያት፣ መጽሐፈ ክርስትና፣ መጽሐፈ ቀንዲል፣ መጽሐፈ ተክሊል፣ ወዘተ፣

በተለያዩ ሰሞናት የሚያገለግሉ ግብረ ሕማማት፣ ድጓ፣ ጾመ ድጓ፣ መዋሥዕት ማኅሌተ ጽጌ፣ ሰቆቃ ወድንግል፣ ወዘተ ያሉ።

5. <u>የሥርዓት መጻሕፍት</u>:- እነዚህ መጻሕፍት የምሥጢራተ ቤተ




ክርስቲያንን አፈጻጸም፣ የቤተ ክርስቲያንን አሠራርና አስተዳደር፣ የካህናትና ምእመናን ክርስቲያናዊ የሆነ የኑሮ ሥርዓት የተደነገጉባቸው ቅዱሳን አበው እምነት እንዳይፋለስ፣ በቤተ ክርስቲያን ልዩነት እንዳይፈጠር፣ አንድነት እንዲጸና የሠሩዋቸው ሥርዓታት የተቀመጡባቸው ናቸው። ለምሳሌ ፍትሐ ነገሥት፣ መጽሐፈ ግፃዌ፣ መጻሕፍተ መነኮሳት፣ የቅዱስ ጳኩሚስ ሕገ ብሕትውና፣ የሚጠቀሱ ናቸው።

6. <u>የታሪክ መጻሕፍት</u>:- የቤተክርስቲያንን የረዥም ጊዜ ታሪክ፣ የየገዳማቱና አድባራቱ፣ በየዘመናቱ የገጠመን መከራ፣ ያሳለፈችው መንፈሳዊ ጉዞ ብሎም የኢትዮጵያ ታሪክ የተዘገቡባቸው ናቸው።

ለምሳሌ ክብረ ነገሥት፣ ታሪክ ነገሥት፣ የዋልድባ ገዳም ታሪክ፣ መጽሐፈ ጤፉት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

7. <u>የጥበብ መጻሕፍት</u>፣ ቅዱሳን አበው እግዚአብሔር በሰጣቸው ጸጋ መንፈሳዊውንና ለሰው የሚጠቅመውን ሥጋዊውን ዕውቀት ጭምር በፈቃደ እግዚአብሔር በማግኘት ለዚህ ትውልድ አውርሰውታል።

እነዚህ መጻሕፍት ስለ ዓለማት፣ ስለ ሥነ ፍጥረት፣ ስለዘመን አቆጣጠር፣ ወዘተ የተጻፉ ናቸው።

- አክሲማሮስ — የሥነ ፍጥረትን ነገር የሚዘረዝር
- መጽሐፈ ሥነፍጥረት — ስለ ሥነ ፍጥረት አጠቃላይ ይዞታ የሚናገር
- መጽሐፈ ማስያስ ስለ ዓለማት ሁኔታ (ሥነ ፈለክ) የሚናገር፣
- አቡሻክር የዘመን አቆጣጠርን ሁኔታ የሚናገር፣

8. <u>ገድላት</u> እነዚህ መጻሕፍት የቤተ ክርስቲ'ን መዓዛ የሆኑትን የጻድቃንና የሰማዕታትን ገድል የሚዘክሩ ናቸው። እያንዳንዱ ገድል በውስጡ አራት ዓይነት ይዘት አለው።

1. የቅዱሱ ታሪክ
2. ከጌታ ለኃጥአን የተቀበለው ኪዳን
3. በዚህ ምድር ወይንም በአፀደ ነፍስ ያደረጋቸው ተአምራት
4. ስለ ክብሩ የተደረሰለት መልክዕ።

ለምሳሌ ገድለ ጊዮርጊስ፣ ገድለ ተክለ ሃይማኖት፣ ገድለ ጻድቃን

9. <u>ድርሳናት</u> እነዚህ መጻሕፍት የቅዱሳን መላእክትን ክብርና ለሰው ልጅ ያላቸውን ተራዳኢነት የሚገልጡ ናቸው። እነርሱም 3 ዋና ዋና ይዘቶች አሏቸው።

1. ስለ ቅዱሱ መልአክ ማንነት፣ ክብር፣ ሥራ የሚገልጥ፣
2. ተአምራቱ
3. ስለ ተራዳኢነቱ፣ አማላጅነቱ የተደረሰለት መለክ።

ለምሳሌ ድርሳነ ዑራኤል፣ ድርሳነ ገብርኤል፣ ድርሳነ ሚካኤል፣ ወዘተ...



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

10. ተአምራት እነዚህ መጻሕፍት የመድኃኒታችንና የእመቤታች ንን ተአምራት የያዙ መጻሕፍት ናቸው።

ለምሳሌ ተአምረ ኢየሱስ፣ ተአምረ ማርያም

## ታሪክ መጻሕፍት

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳት መጻሕፍት የተደረሱበትን፣ የተተረጐሙበትንና ወደ ኢትዮጵያ የገቡበትን ታሪክ ለማየት እንዲያስ ችለን ዘመናቸውን በ4 መክፈል እንችላለን።

1. የቅድመ ክርስትና መጻሕፍት
2. የጥንቱ ዘመን ድኅረ ክርስትና መጻሕፍት
3. የመካከለኛው ዘመን መጻሕፍት
4. የቅርብ ዘመን መጻሕፍት ናቸው።

## 1. የቅድመ ክርስትና መጻሕፍት

ኢትዮጵያ ቅድመ ክርስትና ለብዙ ዓመታት በሕገ ኦሪት ጸንታ የኖረች ለመሆንዋ የተለያዩ ማስረ ጃዎች እስከ ዛሬ ይገኛሉ።

1. የታሪክ የታወቀው የታሪክ መጽሐፍ ክብረ ነገሥትና የሌሎች የግብፅ፣ አረብ፣ ፋርስ ታሪክ ዘጋቢዎች የጻፉት

2. ባሕላዊ–እስከ ዛሬ በሕዝቡ ሕይወት የሚገኙት

- የሚበሉና የማይበሉ እንስሳት
- ግዝረት
- ሥርዓተ ንግሥ ዘታቦት
- የአራስ ቤት ሥርዓት
- የለቅሶ፣ የኀዘን ቤት፣ ሥርዓት

## 3. የቅርስ ማስረጃዎች

በአክሱም፣ በየሃ፣ መርጡለማ ርያም፣ ጣና ቂርቆስ፣ የካ ተክለሃይማ ኖት የጥንት ምኩራባት ፍርስራሾች፣ በቁም የሚገኙ ሐውልቶችና የሥነ ሕንፃ ውጤቶች። ኢትዮጵያ በነዚህ በኦሪት ሕግ ስትመራ በነበረችባቸው ዘመናት ያገኘቻቸው ብዙ ቅዱሳት መጻሕፍት አሉ።

1. ብሉይ ኪዳን፡- ኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ያገኘችው ከጌታችን ልደት በፊት 900 ዓመት አስቀድማ ነው።

ወመክብበ መጻሕፍቲሰ ዘብሉይ ተዐልዋ እም ዕብራይስጥ ኀበ ግእዝ በመዋዕሊሃ ለንግሥተ አዜብ እንተ ሐወጸቶ ለሰሎሞን[1]

በርግጥ ሁሉም የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በዚህ ዘመን ሊገቡ አልቻሉም። ነገር ግን እስከዚያ ዘመን ድረስ የተጻፉት መጻሕፍት ገብተ ዋል። ከዚህ በኋላ ባለው ዘመን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በሦስት መንገድ ሳይገቡ እንዳልቀሩ ይገመታል።

1. ኢትዮጵያውያን አበው (ልክ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ እንዳደረ ገው) ወደ ኢየሩሳሌም ሲወጡ ያገኙ ዋቸውን መጻሕፍት አምጥተዋል።

2. አይሁድ በተለያዩ ዘመናት [2] በአሕዛብ ነገሥታት ተወርረው በስደት ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ ይዘዋቸው መጥተዋል።

3. በኢትዮጵያ ነገሥታት ጥያቄ በአሕዛብ ነገሥታት ካሉት እሥራ ኤላውያን ተቀድተው የመጡ። ለምሳሌ በቤተ ክርስቲያን ትውፊት መሠረት ትንቢተ ዳንኤል ወደ ግእዝ የተተረጐመው በዚህ መሠረት ነው።

በዚህም የተነሣ ከንጉሥ ሰሎሞን መነሣት በኋላ የተጻፉት የነቢያት መጻ ሕፍት በኢትዮጵያ ውስጥ ለመገኘት በቅተዋል። ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የኢሳይያስን መጽሐፍ ሊያገኝ የበቃውም በዚህ አጋጣሚ ነው።

ይህ ጥንታዊው ትርጉም በጥንታ ዊው ግእዝ (Classical Geez) የተተ ረጐመ በመሆኑ ወደ ሳባውያን ቋንቋ የተጠጋ ነበር። በዚህም ምክንያት የግሪኩ ቋንቋ በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት አካባቢ የዓለም መነጋገሪያ ቋንቋ (Lingua francua) እየሆነ ሲመጣ ኢትዮጵያ በመካከለኛው ምሥራቅ በዘመነ አክሱም በነበራት የንግድና የፖለቲካ የበላይነት ከሌሎች ሃገሮች ሕዝቦች ጋር የነበራት ግንኙነት ሰፊ ስለነበር የግሪኩ ቋንቋ የአክሱምና የአካባቢዋ መነጋገሪያ ሆኖ ነበር።

ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ከገባና ከተስፋፋ በኋላ በዘመነ አብርሃ አጽብሐ ከስብዐ ሊቃናት ትርጉም ጋር ተዛምዶ ወደ ዘመናዊው ግእዝ ተተርጉሞአል።[3] በመካከለኛውም ዘመን የግእዝ ሥነ ጽሑፍ እያደገ የሄደበት ጊዜ ነበርና በመጽሐፈ ስንክሳር ነሐሴ 21 እንደምናነበው አቡነ ሰላማ መተርጉም (1348–88) ከዐረብኛው ጋር በማስተያየት ትርጉ ሙን እንደ ደመደሙት ይነገራል።

## ሌሎች መጻሕፍት

በአይሁድ ትውፊት የታወቁ አዋልድ መጻሕፍትም በዚህ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ የመግባቱን ዕድል አግኝተዋል።

- ዜና ሙሴ
- መጽሐፈ መላእክትን የመሳሰሉት መጻሕፍት በሀገራችን ሊገኙ የበቁት በዚህ ምክንያት ነው።

ይቀጥላል

1. Biblo thé que national, paris, MS. Eth. 113, ff63
2. በ606፣ በ596፣ በ586 በተለያዩ ሀገሮች ሲማረኩ ።
3. (Cerulli, Storia della letteratura Ethipoia (1956), pp. 23-33

አንድ አረጋዊ አባት ልጁን ጠርቶ ደረቅ በትር ሰጠውና ይኸን በትር ተክለህ ውሃ እያጠጣህ አጽድቀው ብሎ አዘዘው። ያም ልጅ ያለምንም ማመንታት፣ መከራከር፣ መሰልቸትና መታከት ለ3 ዓመታት ሙሉ ደረቁን በትር ውኃ ማጠጣቱን ቀጠለ። እግዚ አብሔርም መታዘዙንና እምነቱን ስላየ ያን በትር አለምልሞ ዛፍ አደረገው። ያም ዛፍ «የመታዘዝ ዛፍ» ተብሎ ተሠየመ።

ለአበው መታዘዝ ማለት እንዲህ ነው በደግነት፣ በእምነትና ባለመሰልቸት፤ ያን ጊዜ ፍሬ ይገኛል።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# መንፈሳውያን – በዓለማውያን መካከል

ከኤፍሬም እሸቴ

«...ከዚህ ጠማማ ትውልድ ዳኑ...» ሐዋ.2፥40 ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ በበዓለ ሃምሳ መንፈስ ቅዱስን ተመልቶ ከመላው ዓለም ለተሰበሰቡት አይሁድ «ከዚህ ጠማማ ትውልድ ዳኑ» ብሎ ተናገረ። እግዚአብሔርን ባለማወቅ ብቻ ሳይሆን በፈቃደ ሥጋ (ገላ.5፥16–21) ከሚመላለሰው ከዚያ ትውልድ ይለዩ ዘንድ የማስጠንቀቂያ ቃሉን ሰነዘረ። የሰሙት ቃሉን አመኑ፥ ተለዩ፥ ተጠመቁ ወደ ዘለዓለም ሕይወትም ተመለሱ። ያመጹት ግን በዓመጻቸው በረቱ።

ዛሬም የቅዱስ ጴጥሮስ ቃል ሕያው ነውና። ከዚህ ጠማማ ትውልድ ዳኑ ይለናል። ይህ ማለት ግን ሁላችሁም ከዓለሙ ወጥታችሁ ከሰው የተለየ ኑሮ ጀምሩ ማለቱ አይደለም። ያንን የሚያደርጉት የተፈቀደላቸው ብቻ ናቸውና። ነገር ግን ጌታ «...ከዓለም መረጥኋችሁ እንጂ ከዓለም አይደላችሁም...» ዮሐ.15፥19 እንዳለ ክርስቲያኖች የሚኖሩት በዓለም ቢሆንም በክፉ ሥራውና በኃጢአቱ ስለማይተባበሩ ከዓለም አይደሉም። ለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ በመልእክቱ «አመንዝሮች ሆይ ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጥል እንዲሆን አታውቁምን? እንግዲህ የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖአል።» ያዕ.4፥4 ብሎ የፃፈው።

በክርስቶስ ክርስቲያን የተባልን፤ ከጐኑ በፈሰሰው ውኃ (ማየ ገቦ) የተጠመቅን፤ በቀራንዮ መካን የቆረሰውን ሥጋውን የበላን ያፈሰሰውን ደሙን የጠጣንና ወገኖቹ የሆንን እኛ በኃጢአት ልንመላለስ አልተፈቀደልንም። ስለዚህም ራሳችንን ከኃጢአት ልንለይ ይገባናል። እዚህ ላይ ልናስተውለው የሚገባን ዐቢይ ቁምነገር ግን የምንኖረው በዓለሙ (በዓለማውያኑ፤ በመናፍቃኑና በአረማውያኑ) መካከል ስለሆነ እንዴት ልንመላለስ ይገባናል? የሚለውን ነጥብ ነው። በትምህርት ቤት፥ በሥራ ቦታ፥ በንግዱ ዓለም በጉርብትና ከዓለማውያኑ ጋር እንገናኛለን። ነገር ግን ዓለማውያን መንፈሳውያኑን የሚያሟሟቸው ሳይሆን መንፈሳውያን ዓለማውያኑን የሚያጣፍጧቸው ሊሆኑ ይገባል «እናንተ የዓለም ጨው ናችሁ» ማቴ.5፥14 ተብለዋልና።

ከዚህ አንፃር ከጽድቅ ይልቅ ኃጢአት፤ ከእውነት ይልቅ ሐሰት፤ በገነነበት ዓለም ለመኖር ልንከተለው የሚገባንን መንገድ ቀጥለን እንመለከታለን።

## ሀ. ራስን መግለፅ

«መብራትንም አብርተው ከዕንቅብ በታች አይደለም እንጂ በመቅረዙ ላይ ያኖሩታል በቤት ላሉት ሁሉም ያበራል። ማቴ.5፥15። በትምህርት ቤት፥ በሥራ ቦታ፥ በንግዱ መስክ፥ በማኅበራዊው ኑሮ (በዕድር፥ በዕቁብ፥ በጉርብትና፥ ወዘተ.) ክርስቲያንነታችን ይታወቅ ዘንድ አስቀድሞ መግለፅ ተገቢ ነው። ሕይወታችንን አስቀድመን ከገለጽን ቆየት ብሎ ለኃጢአት ሊጋብዘን ለሚፈልገው በሙሉ በሩ ይዘጋበታል። መብራት እንደማይደበቅ ሁሉ መልካም ሥራችን፤ መንፈሳዊ ሕይወታችን ብርሃን ሆኖ ለሁሉም ከታየ ራሳችንን ከዓለማውያን ግብግብ ለማዳን እንችላለን። አንድ ሰው ስለሚሠራው እንዲህ ነኝ ብሎ ጥሩንባ ባያስነፋም፤ ነጋሪት ባያስመታም መልካም ሥራው ሊደበቅ ስለማይችል ሰዎች ማንነቱን ሊገነዘቡት ይችላሉ። ከዘፈን መዝሙር በመምረጡ፥ በትሕትናው፥ በአነጋገሩ፥ በአረማመዱ፥ በአለባበሱ፥ ለሰው ባለው አክብሮት፤ በቤተክርስቲያን ባለው ተሳትፎ ወዘተ ሊገለፅ ይችላል። በሰዎች ከታወቀ ደግሞ ለራሱ አጥር ያበጃል።

በተቃራኒው ግን መንፈሳዊነታቸው፥ የቤተክርስቲያን ልጅነታቸው፥ ኦርቶዶክሳውያን መሆናቸው እንዳይገለጽባቸው በመፈለግ ቀስ በቀስ የዓለማውያኑን እርሾ ያቦኩ፥ ሕይወታቸውን ያበላሹ ከመንፈሳውያንም መንደር የተለዩ፥ «ውኃ ሲወስድ አሳስቆ» ሆኖባቸው ከቤተክርስቲያን የጠፉ ብዙ ናቸው። ይህም ምናልባት ከሚከተሉት ምክንያቶች ሊሆን ይችላል።

## 1. ይሉኝታ

አንዳንዶቹ በባልደረቦቻቸው ዐላዋቂ፥ ያልሰለጠኑ፥ ከዘመኑ ጋር የማይሄድ ላለመባል ራሳቸውን በይሉኝታ ገመድ ጠፍረው በመንፈሳዊነታቸው አፍረው፥ ‹ሁሉ በልብ ነው› እያሉ ነገር ግን በዓለሙ ሰምጠው ይቀራሉ። የሚዘፈን ከሆነ ይዘፍናሉ፥ ይደንሳሉ ይጠጣሉ፥ ይሰክራሉ ወደ ሌላውም ይሸጋገራሉ። ይህንንም ሁሉ የሚያደርጉት ግን ኃጢአትነቱ ጠፍቷቸው እግዚአብሔርን ማሳዘናቸው፥ ትዕዛዙን መጣሳቸው ተረስቷቸው ሳይሆን በይሉ ኝታ ተይዘው ነው። እንደ ዮሴፍ «እንዴት በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአትን እሠራለሁ» ዘፍ.39፥10። ማለትን ቢደፍሩ የይሉኝታ ገመድ ይበጠስ ነበረ።

ሁሉንም ከፈጸሙ በኋላ ግን ነፍሳቸውና ሥጋቸው ከዚህ በፊት የሰሙት ቃልና ማንነታቸው ሙግት ይገጥማሉ የሚተርፋቸው ጭንቀት ብቻ ነው። በዚህ ወቅት ስሕተትን አምኖ ንስሐ ከመግባት ይልቅ ለሠሩት የኃጢአት ሥራ ማካካሻን (justification) በመፈለግ ወደ ሌላ የጥፋት ዓለም ይገባሉ። ይህ ደግሞ ትልቁ የሰይጣን ጥበብ ነው። መጀመሪያ ገፋፍቶ ኃጢአትን ማሠራት – ከዚያም ወደ ንስሐ እንዳይመለሱ ተስፋ ማስቆረጥና ከቤተክርስቲያን ማራቅ። በዚህ ምክንያት እምነታቸውን ቀይረው ወደ መናፍቅነት የገቡ ብሎም ፍጹም ዓለማውያን የሆኑ ብዙዎች ናቸው። ከዚህ ሁሉ በፊት ግን በክርስትና ይሉኝታ የለምና መጠንቀቁ መልካም ነው።

## 2. ፍርሃት

በበላይ አለቆች፥ በሚያከብሯቸው ሰዎች ዘንድ መንፈሳዊ መሆናቸው እንዳይታወቅ በመፍራት የጠሉትንና የተውት ኃጢአት የሚሠሩ ሰዎች አሉ። አለቃቸው ያም የማያውቅ፥ ለሕገ እግዚአብሔር ደንታ የሌለው፥ ክርስትና ትርጉሙና ሕይወቱ ያልገባው የዓለም ሰው ስለሆነ በፍርሃት እርሱን መምሰል ይጀምራሉ።

የእግዚአብሔር ሰዎች ባመኑት የሚያፍሩ፤ ለሚናገሩት እውነት የሚፈሩ፥ ሰማያዊውን በምድራዊው የሚለውጡ አይደሉም። ይልቁንም ብልሆች ጥበበኞች ናቸው። ገና ለገና ሰማይ ይወድቃል ተብሎ ማማ (ምሰሶ) ተይዞ እንደማይኖረው ሁሉ መንፈሳዊነቱ ያስጠቃኛል በሚል ፍራቻ ከእግዚአብሔር መራቅ ተገቢ አይደለም ሰው ምን ግዜም አያመሰግንም። እግዚአብሔር ግን የሰውን ጥቂት መልካም ሥራ ተመልክቶ አብዝቶ ያከብራል። ለዚህ ነው መድኃኒታችን በመዋዕለ ትምህርቱ «ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ግን ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል» ማቴ.16፥25 ያለው።

## 3. ለሰዎች ስሜት መጠንቀቅ

አንዳንዶቹ ደግሞ የሥራ ባልደረበቻቸውን፥ አብረዋቸው የሚኖሩ ደባሎቻቸውን ወይም ዘመዶቻቸውን ላለማስቀየም በሚል ሰበብ ማድረግ ያለባቸውን ሁሉ በመተው፥ ቀስ በቀስ ከመንገዳቸው በመውጣት ወደ ዓለሙ ይገባሉ። መጸለይ፥ መዝሙር ማዳመጥ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ፥ ወዘተ እንዳለባቸው እያወቁት በምትኩ ለሰዎች ስሜት ለመጠበቅ ብለው በመዝሙሩ ዘፈኑን፥ በጸሎቱ ወሬውን፥ በመጽሐፍ ቅዱስም ሌላውን በመተካት ራሳቸውን ለፈተና ያጋልጣሉ።

ይህ ሁሉ ክርስትና ምን እንደሆነ ካለማወቅ፥ ራስንም ለሌላው ካለመግለጽ የሚመጣ ችግር ነው። «ከሰው ጋር ሲኖሩ ምኝ ሆኖ አህያ ሲጭኑ ሦስት ሆኖ» የሚለው አነጋገር የሚሠራው በሌላ ሥጋዊ ሕይወት እንጂ በክርስትና አይደለምና መጠንቀቁ ተገቢ ነው።

ይቀጥላል



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ለሐመር መጽሔት አዘጋጆች:-

ይህ በፎቶ ግራፉ ላይ የምታዩት ቤተ ክርስቲያን በደብረ ታቦር አካባቢ የሚገኝ ሲሆን ከመስቀንች



መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን 45 ደቂቃ ያህል ያስኬዳል። ልዩ ስሙ ‹ወገላ› ይባላል።

ቤተ ክርስቲያኑ ገደሉን በመፈልፈል የተሠራ 3 መግቢያ በሮች ያሉት ባለ 3 ክፍል ነው።

የተሠራው በአፄ ላሊበላ ዘመነ መንግሥት መሆኑን የአካባቢው ሰዎች ነግረውኛል።

እኔ ይኼን ቤተ ክርስቲያን ሳይ ምን ታወሰኝ መሰላችሁ የቤተ ክርስቲያን ልጆች የሆንን ዛሬ ከየተቋማቱ ተመርቀን የምንወጣ ወጣቶች ሙያችንና ዕውቀታችን የት እየዋለ ነው? እኒህ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናትኮ እየፈራረሱ ነው። አበው ሠሩ ባይሆን እኛ እንጠግናቸው እባካችሁ ቅርፃቸውን፣ ውበታቸውን፣ ታሪካቸውንና ትውፊታቸውን ጠብቀው እንዲቆዩ ፊታችንን ወደነዚህ እናዙር።

ወንድማችሁ አዲስ ተፈራ


✣ ✣ ✣

ለሐመር መጽሔት አዘጋጆች እንደምን አላችሁልኝ። እግዚአብሔር አምላክ ሰላሙንና ጤናውን ለሁላችን ያድለን አሜን።

ባለፈው በ2ኛ ዓመት ቁጥር 3 የሐመር መጽሔት ዕትም ላይ የቅድስት አርሴማ ታሪክ ሲወጣ በጣም ነበር የተደሰትኩት። ሁል ጊዜ የምታወጧቸውን ገዳማትና አድባራት ታሪክ ስመለከት በዓይነ ሕሊናዬ የምትመጣው ይህችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ነበረች። የዚህች ሰማዕት ቤተ ክርስቲያን ውሎ ውስጥ ከወልዲያ ከተማ 40 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች። የተመሠረተችው በ362 ዓ.ም መሆኑ ይነገራል። ዛሬ ግን ፈራርሳ አስታዋሽ አጥታ በፎቶ ግራፉ ላይ እንደምታዩት በሚያሳዝን ሁኔታ ላይ ትገኛለች። ይህ በጋ ያለ ጥገና ካለፈ መጪውን ክረምት የሚቋቋም ሕንፃ የላትም። አያሳዝንም። ዛሬ ልባችንን ወደነዚህ ዓይነት ጥንታውያን ገዳማት ካልመለስን ነገ አናገኛቸውም። ይህች ቤተ ክርስቲያን የ1425 ዓመታት ታሪኳን እያጣች ነውና የመጽሔቷ አንባብያን ተረባርበን አንድ እንበል።

ወ/ት ፍሬሕይወት ይማም

✣ ✣ ✣



ከአዘጋጁ

አንባብያን ሆይ ከናንተ የሚላኩልን መልክቶች እጅግ ከመብዛታቸው የተነሣ ሁሉንም ማስተናገድ አልቻልንም። ይህን ችግር ለማቃለል ስንል አንባብያን እርስ በርስ የሚመካከሩበት፣ የሚተራረሙበት፣ የሚማማሩበት አዲስ ዓምድ ጀምረናል። የምትልኩልን ግጥሞች አሁን እንዳወጣናቸው አጠር፣ መጣጥፎቻችሁ እጥር ምጥን ቢሉ ብዙ አንባብያንን ለማሳተፍ እንችላለን። ጥያቄ፣ ዕንቆቅልሽ፣ ቅኔ፣ ግጥም፣ ካርቱን፣ አስተያየት፣ ተአምራት ከነ ማስረጃቸው፣ የአብያተ ክርስቲያናት ፎቶዎች...ወዘተ እናስተናግዳለን። ዓምዱ ለናንተ ክፍት ነው።

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org




©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

©ማኅበረ ቅዱሳን

ይህን መጽሔት ያለ ማኅበረ ቅዱሳን ፈቃድ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማሳተም ፣እንዲሁም በማንኛውም መልኩ ለሽያጭ ማዋል በህግ የተከለከለ ነው፡፡